# አባቴ ያቺን ሰዓት

## ሜጀር ጀነራል ደምሴ ቡልቶ እና
## የግንቦት 81 መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ

ደረጀ ደምሴ

© 2009 BY DEREGE DEMISSIE

ABATE YACHIN SEA'T

ALL RIGHTS RESERVED

EXCEPT AS PERMITTED UNDER THE COPYRIGHT ACT OF THE UNITED STATES OF AMERICA, NO PART OF THIS PUBLICATION MAY BE REPRODUCED OR DISTRIBUTED IN ANY FORM OR BY ANY MEANS, OR STORED IN A DATABASE OR RETRIEVAL SYSTEM, WITHOUT THE PRIOR WRITTEN PERMISSION OF THE AUTHOR.

Aesop Publishers & Distributors
T: 202-386-3037

Signature Book Printing, www.sbpbooks.com

## ምስጋና

ይህ ጽሁፍ ለሕትመት የበቃው በብዙ ሰዎች እርዳታና ድጋፍ ነው። በተለያየ ጊዜ የረዱኝን ሁሉ እዚህ ዘርዝሬ መግለጽ አልችልም። ትንሽም ሆነ ትልቅ እርዳታ ላደረጉልኝ ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ስማቸውን ሳልጠቅስ ከማላልፋቸው ውስጥ ቀዳሚውን ምስጋናዬን የማቀርበው ወደር ለሌላት ለእናቴ ወ/ሮ አስቴር አዳሙ ነው። የአባቴን ጽሑፎች ላለፉት ሃያ አንድ ዓመታት በጥንቃቄ በማስቀመጥዋ የታሪክም ባለውለታ ናት። የልጅነት ጓደኛዬ ነአምን ዘለቀ ያደረገው አስተዋጾ በጽሁፍ ብቻ የሚገለጽ አይደለም። ወንድሞቼ እስክንድር እና ዮናስ እንዲሁም እሕቶቼ ቅድስት እና ሔዋን የረሳኋቸውን ብዙ ነጥቦች በማስታወስ፤ መረጃ በማሰባሰብ፤ ሃሳብ በማካፈል ረድተውኛል።

መጽሃፉን ጨርሼ እንዳሳትም ያበረታቱኝን ሁሉ አመሰግናለሁ። የዶ/ር ዳኛቸው ደስታ...የማበረታቻ ቃላቶችህ ረድተውኛል። ኮ/ግርማ ተሰማ፤ ሜ/ጀ ቁምላቸው ደጀኔ፤ ብ/ጀ ውበቱ ጸጋዬ፤ ኮ/መንገሻ ሁንዴ ብዙ ጥያቄዎች መልሰውልኛል። ሻ/ንጋቱ ተፈሪ እና ሻ/ካሳዬ ማዘንጊያ በትግራይ ስለተደረገው ዘመቻ ዝርዝር መረጃ ሰጥተውኛል። በተለያየ ጊዜ ብዙ ሰዎች የተለያዩ መረጃዎችን አካፍለውኛል። የቅዱስ ዮሴፍ ት/ቤት እያለሁ አማርኛ አስተማሪዬ የነበሩት አቶ ሙሉጌታ ቱሉ የሰጡኝ ገንቢ ሃሳብ በጣም ጠቅሞኛል። ባለቤቴ ሱዛን በማበረታታት፤ ልጆቼ ማያ እና ሊዮ ደግሞ ሁሉን ለማወቅ በሚያደርጉት ጥረት የአያታቸውን ታሪክ ጽፌ እንድጨርስ ገፋፍተውኛል። ለሁሉም ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ደረጀ ደምሴ

# አባቱ፡ ያቺን ሰዓት

ደረጀ ደምሴ

## መታሰቢያ

ይህ መጽሃፍ መታሰቢያነቱ የአንድን ሰው አምባገነንነት አስወግደው ለኢትዮጵያ ህዝብ ሰላም ፣ ፍትህና ዴሞክራሲ ለማምጣት በግንቦት 81 የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወቅት መስዋእትነት ለከፈሉት የኢትዮጵያ ሠራዊት አባሎች ነው።

-1-

በእጇ የማሻት ብርትኳን ውስጧ ሟሙቶ እንደተነፈሰ የላስቲክ ኳስ ቆዳዋን ሲነኩት ወደ ውስጥ ይጎረብጣል። አንዳንዴም ወደላይ ወርወር አደርጋትና እቀልባታለሁ። በአንድ እጇ ነበር የማሻት። ከአባቴ ጋር ከቦሌ አዲስ ባንክ፣ ወደ ቦሌ አየር ማረፊያ አቅጣጫ በዝግታ እየተራመድን ነው። ከእህቴ ቤት ነበር የምንመለሰው። አባቴ በእግር መሔድ ደስ ይለዋል። በተለይ እሁድ ወደ ማምሻው አካባቢ፤ ቀጥ ብሎ አንገቱን ቀና አድርጎ ነው የሚራመደው።

"በጦርነት ላይ እንዴት ነው መድፍ የሚመታበትን ቦታ አስተካክሎ የሚመታው?" በማለት ጠየቅኩት።

"አስተኳሽ አለ፣ እሱ የርቀቱን መጠን ለክቶ በሚሠጠው ምልክት መሠረት ነው የሚተኮሰው።" አለኝ፤ ለኔ ሊገባኝ በሚችል መልክ ለማስረዳት እየሞከረ።

"ርቀት ሳይለካ እንዴት ማወቅ ይችላል?" አልኩት።

"መንገድ አለው፣ ትምህርት ይሰጠዋል። አንዳንድ ጊዜም ግምት መጠቀም የሚገደድበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል" ብሎ መለሰ።





"ርቀት መገመት አስቸጋሪ ነው። በተለይ በጦርነት መሃል" አልኩና "አሁን አንተ ከዚህ መብራት እስከዚያ ፎቅ ድረስ ያለውን ርቀት መገመት ትችላለህ?" ብዬ ጠየቅኩት ፊታችን ያለውን የመንገድ መብራትና አልፍ ብሎ የሚታየውን ባለ ሰማያዊ ቀለም ፎቅ እያመለከትኩ።

"በሚገባ!"

"ስንት ሜትር ይሆናል?"

"መቶ ሃምሳ"

"አይሆንም መቶም ከሞላ ይገርመኛል።"

"ትወራረዳለህ?" አለኝ፣ ከመንገዱ መብራት ጎን ስንደርስ ቆም ብሎ በፈገግታ እየተመለከተኝ።

"እሺ. እንወራረድ!" አልኩ እኔም በእርምጃ እንደምንለካ ስለገመትኩ ከምንጀምርበት ቦታ ቆም ብዬ።

"በምን ትወራረዳለህ?" አለኝ ሳቅ እያለ፣

"እእእ....በኩርኩም" አልኩ እያሳቅኩ።

"በፈለግኩት ሰዓት ጠርቼ ልኮረኩምህ ስችል ለምን በኩርኩም እወራረዳለሁ?"

"እሺ..በምን?"

"እንግዳው ከተሸነፍክ የያዝካትን ብርትኳን እበላብሃለሁ፣ ካሸነፍኩ ትኮረኩመኛለህ "

"እሺ!"

አባቴ እያንዳንዱ እርምጃ ወደ አንድ ሜትር እንዲደርስ ረዘም እያደረገ "ቁ ጠ ር!" ብሎ ከቆምንበት ቦታ ርምጃውን እየሳቀ ጀመረ...

ቤታችን ለመድረስ ትንሽ ቀርቶናል። አባቴ ለብዙ ሰዓት ያሚሟሁዋትን ብርትኳን ከአንድ በኩል ቆዳውን ልጦ እየመጠጠ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ በማብሸቅ መልክ ፈገግ ብሎ እየተመለከተኝ፣ መንገዱን ተሻግረን ወደ ቤታችን ገባን።

ከአባቴ ጋር የማሳልፈው ጊዜ የሳቅ፣የደስታና፡ የትምህርት ነበር።





## -2-

ጊዜው፣ ጠርነት እንደ ደራሽ ውሃ የሰሜኑን ግዛት አጥለቅልቆ፣ ወደ ተረው የኢትዮጵያ ግዛቶች ለመዛመት ማአበሉን ወድሮ የሚገሰግስበት ወቅት ነበር። የበጋ ወራቶች በደመና ጠለው ከተለዩን ትንሽ ጊዜ አልፏል። አዲስ አበባም ክረምት ክረምት መሽተት ጀምራች። የበቆሎ እሸትና የትኩስ ቆሎ ነገድ ደርቷል። ሊስትሮዎችም የክረምት ጭቃ ያበላሸውን ጫማ ለመጥረግ ሣጥናቸውን እያንቋቁ የሰውን እግር በዓይናቸው ይከታለሉ። ክረምቱ ለከተማዪቱ ዝናብ ብቻ ሳይሆን ልዩ ቀለምና ሽታን ጨምሮ ነው የመጣው። በየጥጉ የሚጠበሰው የበቆሎ ሽታ አፍንጫን ሰንፍጦ ኪስ ያስዳብሳል። ለወትሮ በአቧራ የተሸፈኑ መንገዶች በዝናብ ታጥበው ያብረቀርቃሉ። የአላፊ አግዳሚው ፊት በክረምት ጨገግታ ገና አልተሞላም። የክረምት መጀመሪያ ፍካትንና ጥድፊያን ይዞ ነው ብቅ ያለው። ጥድፊያው ደግሞ የድካም ሳይሆን ደስ የሚያሰኝ የሥራ ጥድፊያ ይመስላል።

ዛሩ አዲስ አበባ ቀይቼ ክረምቱን ለማጣጣም አልነበረም ዓላማዬ። ወደ አስመራ ሄጄ አባቴን ለማየት ካሰብኩ ብዙ ጊዜ ሆኖኛል። 12ኛ ክፍልን ጨርሼ ጊዚያዊ ስራ ከጀመርኩ ብዙ ወራት አልሆኑም። በምን ምክንያት

ልሄድ እንደምችል ሳሰላስል አንድ ነገር ተፈጠረ። በምሠራበት የተባበሩት መንግሥታት የዓለም ምግብ ድርጅት /ወርልድ ፉድ ፕሮግራም/ መ/ቤት፤ የአስመራ ቅርንጫፍ ክፍል፣ አዲስ የሬዲዮ ሠራተኛ ቀጠረ። እንዲሁም በቅርቡ መ/ቤቱ ያስመጣው አዲስ የቴሌ ፕሪንተር መሣሪያ ግልፅ ባልሆነ ምክንያት ከቦታው በአንድ ጣሊያናዊ ተነቅሎ ወደ ሌላ ቦታ ተወሰደ። እኔም በዋናው መ/ቤት በአዲስ አባባ የሬድዮ ሠራተኛ ስለነበርኩ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ወደ አስመራ ሄጄ አዲሷን የሬድዮ ሠራተኛ ለማሰልጠንና ቴሌ ፕሪንተሩንም መልሶ ለመትከል ለዋናው የመ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ጥያቄ አቀረብኩ። ሥራ አስኪያጁም ብዙ ሳያቅማማ ጥያቄ ባቀረብኩ በሁለተኛው ቀን በመሥሪያ ቤቱ በኩል አስመራ እንድሄድ ፈቀደልኝ።

ከአዲሷ ሬዲዮ ሠራተኛ ከሊሊ ጋር ብዙ ጊዜ በሬዲዮ ተናጋግረናል። ድምጿን የትንሽ ልጅ ድምፅ ስለሚመስል እየሰማን እንስቅባት ነበር። እስካያት ቸኩያለሁ። አስመራ ለመሄድ እንደተፈቀደልኝ ለእናቴ ስነግራት እሷም ለመሄድ አስባ እንደ ነበርና እንዲያውም በአጋጣሚው በመጠቀም አብረን ለመሄድ እንደምንችል ነገረችኝ። ከተለያዩ ምንጮች በእርዳታ የሚመጣውን ምግብ የሚያመላልስ ሄርኩለስ አውሮፕላን ስለነበረ በሱ ለመሄድ እንድንችል በምንሠራበት መ/ቤት በኩል አስፈቀድኩ። በሶስተኛው ቀን ሻንጣችንንና አንዳች የሚያክል አገልግል ይዘን ከጥዋቱ በስድስት ሰዓት ቦሌ አየር ማረፊያ ተገኘን።





አውሮፕላኖቹ የተባበሩት መንግሥታት  የእርዳታ መስጫ ድርጅት የተከራያቸው የእንግሊዝ እና የቤልጂየም አየር ኃይል ንብረት  ነበሩ። ከአስመራ መቀሌ ይመላለሳሉ። በጣም ግዙፍ ከመሆናቸውም በላይ አስፋልት በለሌለው አየር ማረፊያ በቀላሉ ማረፍና መነሳት ይችላሉ።

የደርግ መንግሥት የድርቁ ሁኔታ አስገድዶት እንጂ እነዚህ ምዕራባዊያን ፓይለቶቹ በሰሜን ኢትዮጵያ እንዲበሩ አይፈልግም። ከጥርጣሬው የተነሳ ፓይለቶች በስለላና ሌሎች መንግሥት የማይፈቅዳቸው ተግባሮች እንዳይሳተፉ ከአውሮፕላኖቹ ጋር የሚዘዋወር የደህንነት አባል በመንግሥት ተመድቧል።

ቦሌ እንደደረስን ሻንጣችንን እየጎተትን ወደ አውሮፕላኑ ተጠጋን። አውሮፕላኑ ላይ ልንሳፈር ስንል እዚያው ቆሞ የነበረው አንድ ሰው ወደ እኛ ተጠግቶ የይለፍ ፈቃድ እንዳለን ጠየቀን። እኔ ምንም ፍቃድ ያልያዝኩ መሆኔን፣ እናቴ ግን ከመለላከያ ሚኒስቴር የዘመቻ ክፍል ከኮ/ተስፋዬ ትርፌ፣ በኋላ ብ/ጀነራል/ የተጻፈ የይለፍ ፈቃድ እንዳላት አስረደቼ ወደ አውሮፕኑ  ጉዞዬን  ሳመራ አንዱ " ወንድም ካለህበት ባትንቀሳቀስ  ይሻልሃል!" ብሎ እጄን ወደ ኋላ ጎኑ ሲያዞር ካለሁበት ደርቄ ቆምኩ። አጠር ያለ ኮሳሳ ብጤ ነው። ሥልጣን እንዳለው ለማሳወቅ ያህል እግሪ እደማያስቀረን ገምቼ ትንሽ ተለማመጥኩት። ከብዙ ጭቅጭቅና ልመና በኋላ እንድገባ ፈቀደልኝ።

አውሮፕላኑ በተጫነው እህል ሞልቶ ስለነበር፣ እኔ ከኋላ እህሉ ላይ ከሁለት ፈረንጆች ጋር፣ እናቴ ደግሞ ከፊት ከፓይለቶቹና ከደህንነቱ ጋር እንድንሆን ተስማማን። ሁለት ሰዓት ከአርባ አምስት ደቂቃ የሚፈጀውን ጉዞ ወደ አስመራ ተያያዝን። መስታወቶቹ በእህል ጆንያዎች ተሸፍነዋል። ምንም የሚታይ ነገር ስለሌለ መፅሐፌን እያነበብኩና አልፎ አልፎ ካጠገቤ እህሉ ላይ ከተንጋለለው ፈረንጅ ጋር እያወራሁ አስመራ ደረስኩ።

አባቴ አስመራ ለሥራ ብሎ ከሄደ ብዙ ወራት ሆኖታል። እናቴ በዛው አስመራ ተመድቦ እንዳይቀር ሰግታለች። ከብዙ ዓመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ ተመድቦ መሥራት ጀምሮ ነበር። በመከላከያ ሚኒስቴር የዘመቻና የትምህርት ዋና መምሪያ ኃላፊ ሆኖ፣ ከሐረር አዲስ አበባ ሲመጣ ከቤተሰቡ ጋር አብሮ የመኖር እድል ያገኘው ከአስራ ሁለት ዓመት በኋላ ነበር። ወዲያው ደግሞ  ዓመት ሳይሞላው ወደ አስመራ ሄደ። አፍአበት የነበረው ጦር ሲደረመስ ነበር ከሌሎች የጦር መሪዎች ጋር ሆኖ የሄደው።

እኔ በበኩሌ ከአባቴ ጋር ሁኔታው የፈቀደውን ያህል ጊዜ ለማሳለፍ የጦርነቱንም ሁኔታ ለመረዳት ችኩያለሁ። የጦር መሪዎች ማታ ማታ ተሰብስበው ሲያወሩ አጠገባቸው ቁጭ ብዬ ማዳመጥ ደስ ይለኝ ነበር።

አስመራ አየር ማረፊያ ስንደርስ፣ የሃምሳ አለቃ ከፈተው አውሮፕላኑ ድረስ መጥተው ተቀበሉን። ከፈተው ረጅም ደልዳላ ሰውነት አላቸው።





ሰድሚያቸው ቢገፋም ንቁና ጠንካራ ወታደር ናቸው። አንድ እጃቸው የኔን ሁለት ይበልጣል። ከቀይ ፊታቸው ፈገግታ አይጠፋም።

በሰሜን ኢትዮጵያ ወደ ሃያ ዓመት የቆዩና ብዙውን ጊዜ በአዛዦች ሹፌርነት ያገለገሉ ናቸው። በወታደር ዓለም ከበታች ሹማምንት መካከል የአዛዥ ሹፌር መሆን ከፍተኛ ቦታ ያለው ነው። ሠላምታ ከተለዋወጥን በኋላ "አባዬ እንዴት ነው?" ብዬ ጠየቅኩ። "ደህና ናቸው፣ አሁን ታገኛቸዋለህ" አሉኝ ፈገግ ብለው። እኔም በደስታ እየፈነደቅሁ ከቆመችው ነጭ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር ተሳፈርኩ።

ከፈተው መኪናዋን እያምዘገዘጉ ወደ ዋናው መንገድ አመሩ። ከመንገድ ዳርና ዳር በተርታ የተተከለው ዘምባባ "እንኳን ደህና መጣችሁ!" የሚል ይመስል ይንዠዋዠዋል። እኛም አስመራ በሰላም በመድረሳችን ፈጣሪን እያመሰገንን፣ "እንኳን ደህና ቆያችሁን" በሚል ፈገግታ ቃኘናቸው። በዘንባባ የተከለለውን መንገድ አልፈን ሌላ መንገድ ገባን። አልፎ አልፎ የውሃ ቦቴዎች ውሃ ሲያድሉ ይታያሉ።

"እንዴት ነው አሁንም የውሃ እጥረት አለ?" አለች እናቴ ሶስተኛውን የውሃ ቦቴ ስናልፍ።
"አስመራ መች ውሃ ጠግቦ ያውቅና? ውሃ አልፎ አልፎ ነው በቧንቧ የሚመጣው" አሉ ሃምሳ አለቃ ከፈተው።

“አቤት እንደዚህ ሕዝብ መቼም ችግር የሚችል ሕዝብ አላየሁም” አለች እናቴ በጥያቄ ሳይሆን በሀዘን ዓይነት አነጋገር ።

እናቴ ወ/ሮ አስቴር አዳሙ፣ የሰውን ችግር የመረዳት ልዩ ተሰጥኦ አላት። ብዙ ጊዜ የምትሰነዝራቸው ሐሳቦች የግለሰብን ሕይወት የተመለከቱ ናቸው። “ጦር ይዝመት” ሲባል የሚታያት ዘምቶ የሚይዘው መሬት ሳይሆን ትቷቸው የሚሄደው ልጆቹ፣ ቤተሰቡ፣ የሚጎዘው ጉዞ፣ የሚቀርብለት መጓጓዣ ፣ ምግብ፣ ውሃ ወደ ቤተሰቡ የመመለስ እድሉ የመሳሰሉት ናቸው። እናም የውሃ ቦቴ ስታይ የሚታያት በውሃ እጥረት ምክንያት በየቤቱ ያለው ችግር ነው። ግልፅ ከሆኑከሌሎች ችግሮች ጋር ተዳምሮ አንድ ላይ ይታያታል።

አስመራ ብዙም የመንገድ ትራፊክ መብራት የላትም። ያሉትንም ጥቂት መብራቶች ሲያስኛቸው እነ ሃምሳ አለቃ ከፊተው እያጣሱ ነው የሚነዱት። ሱቆች ተከፍተዋል። ሰውም በመጠኑ እየተዘዋወረ ነው። ከተማው ጭር ያለ ነገር አለው። ወታደር በየቦታው ይታያል። ለአንድ ጉብኚ የሚሰማው ስሜት ሐረር ወይም አዋሳ ወይም ጐንደር እንደመሄድ ዓይነት አይደለም። የአስመራ ስሜት የተለየ ነው። የነዋሪው አስተያየት የሚያስተላልፈው መልእክት ያለ ይመስላል። ከዚህ በፊት አስመራን ጉብኘቼ ባውቅም አሁን ግን ትንሽ የተለየ ስሜት ተሰማኝ። ምን እንደሆነ ገና ግልፅ አልሆነልኝም።

እየተጠማዘዝን ቃኘው እስቴሽን በመባል ከሚታወቀው የጦር ሰፈር ስንደርስ መኪናዋ ዝግ ብላ በመቆም፣ ከፊት ያለው መኪና ቅጥር ግቢው





ተፈቅዶለት እስኪገባ መጠበቅ ጀመረች። ተራችን ሲደርስ በሩ ላይ ቆሞ የሚያስተናግደው የወታደር ፖሊስ የእጅ ምልክት አሳይቶ አስገባን። በግንብ የተከለለ ግቢ ነው። በግንቡ መሐከል አልፎ አልፎ ቀዳዳ አለ። ከግንቡ በላይም የሚታዩ እንደ ቆጥ ወይም ማማ የመሰሉ ጠባቂ ወታደሮች የሚቆሙባቸው ቤቶች ዙሪያውን ተሠርተዋል። ከግቢው ስፋት የተነሳ የግንቡ መጨረሻ አይታይም።

ግቢው አጥር ላይ አልፎ አልፎ አሸዋ በተሞሉ ጆንያዎች ላይ የተጠመዱ ከባድ መትረየሶች ይታያሉ። በአካባቢው የወታደር ልብስ ያልለበሰ ሰው አይታይም። ዝግታ የሚባል ነገር ጨርሶ የለም። ተላላፊው በፍጥነት ይራመዳል። የቆመ ቢኖር እንኳ አንገቱን በሁሉም አቅጣጫ በጥድፊያ እያዞረ መልከት መልከት ያደርጋል። ዋናውን በር አልፈን ቀጥታ ከተጓዝን በኋላ ወደ ግራ ታጥፈን ከመጀመሪያው ቤት ስንደርስ ቆምን።

“ይሄ ነው ቤታቸው፣ ግቡና እረፍ በሉ እንግዲህ! እኔ ሄጄ ደህና እንደገባችሁ እነግራቸዋለሁ” አሉ ከፊተው፣ ተሰፈንጥረው እየወረዱ። ዕቃችንን አስገብተን፣ ሃምሳ አለቃ ከፊተውን ተሰናበትንና ቤቱን አንድ በአንድ መመርመር ገባን። አራት የመኝታ ክፍሎች ያሉት ሲሆን ሁለቱ ተቆልፈዋል። በተረፈ ትልቅ ሳሎንና ሁለት የመታጠቢያ ቤት እንዲሁም አንድ የወጥ ቤት አለው።

በኋላ እንደ ሰማሁት፣ የቀድሞ ቃኘው ስቴሽን ሃላፊ የነበረው አሜሪካዊ መኮንን ይኖርበት የነበረ ቤት ነው። ሳሎን ውስጥ አንድ ቴሌቪዥን፣ አንድ የድሮ ትልቅ ሬድዮ፣ ሶስት ስልኮች፣ አንድ ግዙፍና ሁለት ትናንሽ ሶፋዎች አሉ። የሳሎኑ ክፊል ምግብ ቤት ነው። የምግብ ጠረጴዛና ወንበሮች ጥግ ይዘው ከኮመዲኖ ጎን ተቀምጠዋል። አንደኛውን መኝታ ቤት ቃኝቼ ወደ ሁለተኛው አመራሁ። ከተዳባይ አልጋ በስተቀር ምንም የለውም። አንደኛው መኝታ ቤት የአባቴ መሆኑን ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም። ድሮ አባቴ ከበረሃ ሲመጣ የምናደርገው አሁንም ትዝ ይለኛል።

ብዙ ጊዜ አባቴ ዛሬ ይመጣል እየተባለ ይነገረን ነበር። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ አንድ ወይ ሁለት ቀን ዘግይቶ ስለሚመጣ ከት/ቤት ስንመለስ መጥቶ መሆኑን ለማወቅ ወደ ትልቁ መኝታ ቤት ሮጠን እንሄዳለን። በተለይ ከታናሽ እህቴ ከሄዋን ጋር ይዞት የመጣውን የተሰቀለ ልብሱን እያሸተትን "አባዬን አባዬን ይሸታል" እያልን መምጣቱን አረጋግጠን ከቢሮ እስኪመለስ በጉጉት እንጠብቀው ነበር።

ምሳ ሰዓት ሲደርስ የተቆለፋትን የሁለት መኝታ ቤቶች ሚስጥር ፈታሁ። ጊዜው የኤርትራ ወንበዴዎች ያየሉበትና አፋአቤት ላይ የነበረውን የናደውን አዝ ጭምሮ ወደ ሃያ ሺህ የሚጠጋ ጦር የናዱበት፣ የከረንን ስትራቴጂካዊ ቦታ ለመያዝ ከፍተኛ ጦር ያሰለፉበት ጊዜ ነበር። ሜ/ጀነራል መርዕድ ንጉሤ"፣ ሜ/ጀነራል ኃይሉ ገ/ማካኤል፣ ሜ/ጀነራል አምሃ ደስታ፣ እንዲሁም ሌሎች ጀነራሎች ለችግሩ መፍትሔ ለመፈለግ ወደ አስመራ ሄደዋል።





የኔም አባት ሜ/ጀነራል ደምሴ ቡልቶ የመከላከያ የዘመቻ ዋና መምሪያ ሃላፊ ስለነበር በዚሁ ችግር ምክንያት ነበር ወደ አስመራ የመጣው።

ይህም ችግር የተፈጠረው ፣ ኮ/ል መንግሥቱ አስመራ ሄደው፣ ብ/ጀ ታሪኩ እንዲገደሉ፣ ብ/ጀ ከበደ ጋሼ ደግሞ ማዕረጋቸው በጦሩ ፊት እንዲገፈፍ ካደረጉ በኋላ፣ እንዲሁም የሰሜን ጦር አዛዥ የነበሩትን ሜ/ጀ ረገሣ ጂማን አንስተው ወደ ሆለታ በማዛወር የጦር ት/ቤት አዛዥ አድርገው፣ በምትካቸው ብ/ጀ ውበቱን በተጠባባቂነት ከሾሙ በኋላ ነበር። ብ/ጀ ታሪኩ ለናደው ዕዝ አዛዥነት የበቁት፣ ከመቶ አለቅነት እስከ ብ/ጀኔራልነት በበረሃ ሲዋጉና ሲያዋጉ ከኖሩ በኋላ ነው። በወታደሮቻቸውም በጣም የተወደዱ የሚሰማቸውን ከመናገር ወደኋላ የማይሉ ብዙ ልምድና ዕውቀት ያላቸው የጦር መሪ እንደነበሩ አሰማ ነበር። ሌ/ኮ መንግሥቱ አስመራ ስብሰባ ጠርተው፣ ከጦር መሪዎች ጋር ከተነጋገሩ በኋላ፣ በግል ሲያነጋግሯቸው የጦርነቱ መፍትሄ ጦርነት ሳይሆን ሰላማዊ አማራጭ መንገድ መሆኑን አለማንገራገር እንደነገሯቸውም ሲወራ ሰምቻለሁ። መንግሥቱ በመልሳቸው ተገርመውና ተደናግጠው ጀ/ከበደ ጋሼን ሲያናግሩ "ታሪኩ የዚህ ዓይነት አመለካከት ሰጠኝ፣ አንተ ምን ይመስልሃል?" ብለው ሲጠይቋቸው ጀኔራል ከበደም የሳቸውም አመለካከት ከዚያው የተለየ እንዳልሆነ ነገሯቸው። ከዚህ በኋላ በጦሩ ውስጥ በእነዚህ ሁለት ጀነራሎች ላይ ካድሬዎች ውንጀላ እንዲያቀርቡ ተደረገ። ከቁጥር በማይገቡ ምክንያቶች ለአገራቸው ሳደረጉት አስተዋጽኦ የሞትና የውርደት ዋጋ ተከፈላቸው።

ከዚህ ግፍ በኋላ በተጠባባቂ አዛዥነት የተተኩት፣ ብ/ጀ ውበቱ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት አፋአቤት ላይ ከፍተኛ የማስተባበር ሥራ መሥራት ነበረባቸው። በቂ ጊዜ አግኝተው ጦሩን ማደራጀት ባለመቻላቸው፣ጦሩ ሞራሉ እንደላሸቀ ሻዕቢያ አጥቅቶት፣ ከሃያ ሺህ በላይ የሚሆነው ያለ የሌለ መሣሪያውን ጥሎ ሸሸ። አፍአቤት በወንበዴ እጅ ሲወድቅ፣ ብ/ጀ ውበቱ ከስድስት ወታደሮች ጋር ሆነው አመለጡ። ሌ/ኮ መንግሥቱ ራሳቸው የሠሩትን ስሕተት ወደ ጎን ትተው ብ/ጀ ውበቱን ወደ ሌላ የመንግሥት ሥራ አዲስ አበባ መደቧቸው። የአፍአቤቱ ጦር ከስምንት ዓመት በላይ በቀበሮ ጉድጓድ መሽጎ መቀመጡ መሮት በአዛዦቹ በኩል ላቀረበው ጥያቄ ያገኘው ምላሽ በቁስሉ ላይ እንጨት እንደ ሰደዱበት ያህል ተሰምቶት ስለነበር ሞራሉ ሞቶ ከጠላት ሳይገጥም ተሸንፎ የተቀመጠ ጦር ነበር።

ምሳ ሰዓት ላይ መጀመሪያ አባቴ ሲመጣ እኔም እናቴም በደስታ ፈንድቀን ተቀበልነው። አባቴ ካለው ትልቅ የተፈጥሮ ጸጋ ውስጥ በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ውሎ፣ ወደ ቤት ሲመጣ ሁሉን ረስቶ የመዝናናት ችሎታው አንዱ ነው። ጠቆር ያለው ፊቱ ድካሙን ይደብቀዋል።በዚህ የ1978 የመጨረሻዎቹ ወራት፣ ዕድሜው ወደ ሃምሳ አራት ዓመት ገደማ ቢሆንም ከሕይወቱ ሰላሳ ስምንቱን ዓመታት በውትድርና ስላሳለፈ ጥሩ የወታደር ቁመና አለው። ከቦርጭ ጋር አይተዋወቁም። አልፎ አልፎ ጧት ራሱን በመስታውት እያየ "እንዴት ነው ቦርጭ ሳወጣ ነው እንዴ?" ይላል። በቀፍጣናነቱ የታወቀ ነው። የውትድርና ዘመኑን ከክቡር ዘበኛ መኮንኖች





ኮርስ በመግባት በመቶ አለቅነት ከተመረቀ በኋላ፤ ዕድሜውን በበረሃ፤ በማስተማር ወይም በትምህርት ላይ ነው ያሳለፈው። በኮርያ ጦርነት በተባበሩት መንግስታት ሥር ኢትዮጵያ ጦር ስትልክ በመዝመት ተዋግቷል። እንደውም የም/መቶ አለቃ ማዕረጉን የወሰደው ወደኮርያ በወሰዳቸው መርከብ ላይ ነበር። ከኮርያ ከተመለሰ በኋላ እስራኤል አገር ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ግዜ ለአየር ወለድ ትምሕርት ጦር ስትልክ፤ የተላከውን ጦሩ ከመሩት ጥቂት መኮንኖች አንዱ ነበር። እስራኤል የሰለጠነው በአለም የመጀመሪያው "ጥቁር" ፓራትሩፐር ጦር ነበር።

ጀ/ደምሴ ከእስራኤል ተመልሶ የመጀመሪያውን የኢትዮጵያን የአየር ወለድ ጦር ከአቋቋሙት መኮንኖች አንዱ በመሆን በደብረዘይት አየር ወለድ ዘመቻ ክፍል ሠርቷል። በአየር ወለድነት ሰባ አንድ ጊዜ በፓራሹት ዘሏል። ከእነዚያ ዝላዮች ውስጥ የመጀመሪያ ጊዜ የአየር ወለድ ጦር የዝላይ ግዳጅ ሲሰጠው በነሐሴ ወር 1953 ዓም፣ ከግዳጅ ላይ የተሰማሩትን የአየር ወለድ አባሎች ከመሩት መኮንኖች ውስጥ አንዱ ነበር። ግዳጁም አንድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዲሲ.3 አውሮፕላን ከአዲስ አበባ አስመራ በጉዞ ላይ እንዳለ ከ19 መንገደኞች ጋር በየረርና ከረዩ አውራጃ ዳለቻ በሚባል ቦታ ሞተሩ ጠፍቶ ይወድቃል። የወደቀበት ቦታ በመኪናም ሆነ በእግር ለመድረስ አልተቻለም። አፋጣኝ የነፍስ አድን እርዳታ ለማድረግ የነበረው ምርጫ የአየር ወለዶችን በፍጥነት ቦታው ላይ በጃንጥላ ማውረድ ነበር። በዚህ ግዳጅ፣ የአየር ወለድ አዛዥ ከነበሩት ሻለቃ መኮንን ሙላት ጋር በመሆን መቶ አለቃ ደምሴ ቡልቶና ሌሎች ሁለት አስልጣኞች፣ በፍጥነት

ወደ ዳለቻ ተጉዘው በጃንጥላ ቦታው ላይ ወርደው፣ የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ በመስጠት የብዙ ተሳፋሪዎችን ህይወት አድነዋል። (ስለዚህ ግዳጅ ቀ.ሠና ጦር ሠ. በሌ/ኮ አበበ ወ/ተንሳይ ገጽ 358 ይመልከቱ)

ጀ/ደምሴ የአየር ወለድ ጦር ዘመቻና የትምህርት ኃላፊ በመሆን አገልግሏል። በ1957 ዓ.ም፣ ሶማሌ፣ የኢትዮጵያን ድንበር በባሌ በኩል ጥሶ፣ ጦርነት በከፈተችበት ጊዜ፣ የአየር ወለድን ጦር መርቶ በመዝመት ለኢትዮጵያ አንድነት ባደረገው አስተዋፅኦ የጀግና ሜዳይ ተሸልሟል። ቀጥሎም በኢትዮጵያ ስታፍ ኮሌጅ በ1957 ገብቶ ከተለያዩ ኃይሎች ከተውጣጡ ተሳታፊ መኮንኖች መካከል በአንደኝነት ስለጨረሰ፣ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እጅ ሽምላ ተሸልሟል። በመቶ አለቃ ማዕረግ ወደ አሜሪካ ፎርት ቤኒንግ ጆርጂያ ተልኮ ለ6 ወር የእግረኛ ጦር አመራር ት/ቤት ገብቶ ተመርቋል። በኋላም፣ ሕንድ አገር፣ ከማድራስ ዩኒቨርስቲ ጋር ሆኖ ከፍተኛ መኮንኖችን ከሚያሰለጥነው ከሕንድ ሚሊተሪ ስታፍ ኮሌጅ የከፍተኛ ጦር አዛዥነት ትምሕርት ተከታትሎ ከተመለሰ በኋላ፣ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የጦር ትምህርት ቤት፣ የትምሕርት ዲሬክተር ሆኗል። በሻለቃ ማእረግ በሓረር ጦር አካዳሚ የትምህርት ዲሬክተር እያለ፣ ለከፍተኛ መኮንኖች በሚሰጥ ፈተና ዉጤት ተመርጦ እንደገና ወደ አሜሪካ በመሄድ በታወቀው አርሚ ጀነራል ስታፍ ኤንድ ኮማንድ ኮሌጅ ገብቶ በከፍተኛ የጦር አመራር ሥልት ትምህርት ተመርቋል። የአሜሪካ ጦር መሪ የነበረው ጄኔራል ኮልን ፓወል በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ፣ ስለዚህ ትምህርት ቤት ሲናገር - የሚሊተሪ ሳይንስ ማስተሰር ዲግሪ ፕሮግራማችን ነው፣ በማለት አንድ የአሜሪካ





መኮንን የጀነራል ማዕረግ ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ትምህርት ቤት መመረቅ እንዳለበት ጠቅሷል።

ከአሜሪካ ከተመለሰ በኋላ ብዙ ምርጥ ኢትዮጵያውያን መኮንኖችን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ አስተምሯል። ከ1966 ዓ.ም በኋላም የምድር ጦር የትምህርት፣ የትጥቅና የዘመቻ ኃላፊ፣ በመሆን ሲሠራ ቆይቷል። በ1969 አስመራ፣ ከዚያም ከ1970 እስከ 1973 ዓ.ም በኢትዮጵያና በሶማሊያ ጦርነት ወቅት የደቡብ ዕዝ አዛዥ በመሆን ሶማሌ በአጭር ጊዜ ከሲዳሞና ከባሌ ተባራ የወጣችበትን ጦርነት መርቷል።

ከደቡብ ዕዝም አዛዥነት በኋላም፣ ወደ ሐረርጌ ክ/ሀገር የምስራቁ ጦር አዛዥ ሆኖ፣ በሐረርጌ ክፍለ ሀገር ዘልቆ የገባው የሶማሌ ጦር ከኢትዮጵያ ድንበር ጨርሶ እስኪወጣ ድረስ ጦሩን መርቷል። ሐረር ለሰባት ዓመት ያህል ከተቀመጠ በኋላ ነበር ወደ አዲስ አበባ የመጣው። እናቴ አዲስ አበባ እኛን እያሳደገች ስትቀመጥ ከአባታችን ጋር ጊዜ የምናሳልፈው፣ ለሥራ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ወይም ባለበት ሄደን ስንጠይቀው ነበር። ረዘም ያለ የትምህርት ቤት እረፍት ሲኖረን እንዲሁም በየክረምቱ አዋሳ ወይም ሐረር ከባታችን ጋር እናሳልፍ ነበር። ከሥራ ውጭ ያለውን ጊዜ በሙሉ ከቤተሰቡ ጋር ነበር የሚያሳልፈው። ከብዙ ጭቅጭቅ ወጥቶ ቤት ሲገባ ሁሉን እንደረሳ ዓይነት በረጋ መንፈስና በደስታ የተገኘችውን አጭር ጊዜ ያሳልፋል።

ጀኔራል ደምሴ ቡልቶ ለድካምና ውጥረት ፊት አይሰጥም። ፊቱ ሁል ጊዜ የፈካ ነበር። እኔም ሳየው አንድ ነገር ሰውነቴን ይወረኛል። እኮራለሁ። በልበ ሙሉነት አብጣለሁ። እናም አሰመራ እንደገባን ለምሳ ሲመጣ ደስታና ኩራት በተቀላቀለበት መንፈስ ነው የተቀበልኩት። እሱም ፈገግ ሲል ፍንጭት ጥርሱ ከልዩ የደስታ ቦታ የመጣ እንጂ፣ ከሚኖርበት ውጥረት፣ ለደቂቃ እፎይታ እንኳ የወጣ አያስመስለውም።

ተሳስመን ከጨረስን በኋላ ለስጤንነቱ እና ሰለአጠቃላይ ሁኔታዎች መጠያየቅ ጀመርን። "ምን ያጨመላልቁ፣ ያጨመላልቁና መውጫ ሲያጡ ይጠሩናል። እንደዚህ የተጨመላለቀ ነገር አጋጥሞኝ አያውቅም።" አለ ሶፋው ላይ መለዮውን አውልቆ እየተደላደለ።
"እንዴት?" እናቴ ጠየቀች።
"ተይኝ እባክሽ ነገሩ ሁሉ ተምታቶባቸዋል። የሚይዙት የሚጨብጡት ጠፍቷቸው ነው እኛ የደረስነው። መጀመሪያውኑ ስንጠይቃቸው -ዝግጁ ነን! - ነበር የሚሉን ከቁጥጥራቸው ሲወጣ ነው እርዳታ የጠየቁት፣ እና እንዴት አድርገን ከእነዚህ ሰዎች ጋር እንደምንሠራ ጨርሶ አይገባኝም። ችግሩ ብዙ ነው" ብሎ በሰፊው ተነፈሰ።

ከጥቂት ጭውውት በኋላ የቤተሰብ ጨዋታ ቀጠልን። እንዲሁ እያወጋን ሳለን ሁለት መኪኖች ተከታትለው ከቤቱ ፊት ለፊት ቆሙ። በመስታወቱ ወደ ውጭ ስመለከት ሜ/ጀኔራል መርዕድና ሜ/ጀ ኃይሉ ወደ በሩ ሲያመሩ ስላየኋቸው ቶሎ ሄጄ በሩን ከፈትኩ።





"አዲስ አበባዎች እንኳን ደህና መጣችሁ። ታዲያስ?" አለ ጋሼ መርዕድ። ሜ/ጀ መርዕድ የመከላከያ ሚኒስቴር የኤታ ማጆር ሹም ነው። ከሚኒስትሩ ተዮሎ የበላይ ጀኔራል እሱ ነበር። ጀ/መርዕድ የአባቴ የቅርብ ጓደኛ ከመሆኑም በላይ አባቴና እናቴ ሶስት ልጆቹን ክርስትና አንስተዋል። በክብር ዘበኛ መኮንኖች ማሠልጠኛ የጦር ት/ቤትም አንድ ኮርስ የነበሩ ከመሆናቸውም በላይ ወላጆቻቸው የቅርብ ግንኙነት ነበራቸው። ጋሽ መርዕድ በት/ቤት በማገኛቸው ጥሩ ውጤቶች የተነሳ "ጸረ ድንቁርና" እያለ ነበር የሚጠራኝ። በጣም ተጫዋች ከመሆኑም በላይ ሰው የማቅረብ ተሰጥኦ ነበረው። ፊቱ ክብ ሆኖ ፍም የመሰለ ቀይ ነው። ቁመናው አጠር ያለ፤ እንደበቱ ረጋ ያለ፤ ሰው ተናግሮ የማያስቀይም ጀኔራል ነበር። በወታደሮች ዘንድ በጣም የተከበረና የተወደደ እንደሆነ እሰማለሁ። ምጽዋን ለመከላከል በተደረገው ጦርነት እሱ እና ኮ/እስጢፋኖስ ገብረመስቀል ያደረጉት ተጋድሎ ከፍተኛ አድናቆትን ከማትረፉም በላይ ጀ/መርዕድ በጦር ሜዳ በከባድ ሙትረየስ ተመትቶ ለኢትዮጵያ አንድነት ደሙን አፍሷል። ጀ/መርዕድ እንደ ልጁ ስለሚያየኝ አገላብጦ ከሳመኝ በኋላ ወደ እናቴ አመራ። ጋሽ መርዕድን እንደ አባቴ ሰለማየው አንተ እያልኩ ነበር የምጠራው።

ከኋላው የተከተሉት፣ ሜ/ጀ ኃይሉ ገ/ሚካኤል ሲሆኑ የምድር ጦር አዛዥ ናቸው። ከዚያን ቀን በፊት በአካል አይቻቸው ባላውቅም በስም አውቃቸዋለሁ። ረዘም ያሉና እዚያ ጠይም ፊታቸው ላይ ፍጹም እርጋታ የሚታይባቸው ሰው ናቸው። ከፊታቸው ላይ የሰፈነው ሰላም ተናደው

የማያውቁ ያስመስላቸዋል። ከእርጋታቸው የተነሳ ሲያወሩም በጣም ቀስ ብለው ነው። ከጊዜ በኋላ ሰው የማይንቁ፤ ተጫዋችና በጣም ቀና ሰው መሆናቸውን አስተዋልኩ። ቅጠልያ የሚባለውን የወታደር የደንብ ልብስ ለብሰዋል። ከኮሌታቸው ላይ በተለጠፈው ቀይ ጨርቅ ላይ የተተከለው የወርቅ ዘንባባ ያብረቀርቃል።

ጋሽ መርዕድ የያዘውን በትረ መኮንንን ካስቀመጠ በኋላ፤ እግሩን ጠረጴዛ ላይ አውጥቶ የቀኑን ድካም እንደማራገፍ ያህል በሰፊው ተነፈሰና፤ "

"አስቴር ታዲያስ እንደምን አለሽ?" አለ፤ እናቴን በፈገግታ እየተመለከተ።

"ይኸው ልንጠይቃችሁ መጣን እንግዲህ የናንተ ዙረት ማለቂያ የለውም።" አለች እናቴ።

"ምን ማለቂያ አለው ብለሽ ነው! ይሻላል ስንል ጭራሽ እየባሰበት መጣ እንጂ..." አለ ጋሽ መርዕድ ትንሽ ፈገግታ ቢጤ እያሳየ። ጀነራል ኃይሉ ከገቡበት ክፍል ወጥተው ወደሳሎን መጡና ተቀመጡ ። ሲራመዱም ረጋ ብለው ነው።

እናቴ የሰነቀችውን የዶሮ አገልግል ካቀረብን በኋላ ለመብል ቀረብን። ምግቡ ቀርቦ ሲያዩ "ይሄማ ልዩ አይደል እንዴ?" አሉ ጀ/ኃይሉ

"ደምሴ እንደዚህ እየፈካ የሚሄደው ለምን መሰለህ?" ብሎ ቀለደ ጋሽ መርዕድ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ቤቱ በሰው ተሞላ። ከአዲስ አበባ፤ ከአባቴ ጋር አብረው የመጡ ረዳት ጀኔራሎችና ኮለኔሎች አንድ ባንድ ይገቡ ጀመር። ምግብ መብላት እንደጀመርን ሜ/ጀ/አማሃ ገቡ። ከርዝመታቸው የተነሳ ሲገቡ በሩ እንዳይመታቸው ጭንቅላታቸውን ዝቅ አድርገው ነበር የገቡት።





በሳሎኑ ከተሰበሰቡት መኮንኖች ጋር ሰላምታ እንደተለዋወጡ አባቴ እናቴንና እኔን ከጀነራል አማሃ ጋር አስተዋወቀን። "አማሃ ባለቤቴን ተዋወቅ" አለ። እናቴና እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር ጀነራል አማሃን በአካል ያገኘናቸው። እኛን ሰላም ብለው እንደጨረሱ፦

"ምነው ቀየህ?" አለ ጋሽ መርዕድ ጀነራል አምሃን እየተመለከተ። ጀ/አማሃ " ሰዎቻችን ትንሽ ዒላማ አግኝተው ሲደበድቡ ነበር" ብለው ለመቀመጥ ሲሞክሩ "ታጠብ፤ ታጠብ" የሚሉ የግብዣ ድምፆች ተቀበሏቸው። ከመቀመጥ ይልቅ ወደ መታጠቢያ ቤት አመሩ።

"እና በደንብ አገኙ ታዲያ? ለመሆኑ የት ላይ ነበር?" አለ ጋሽ መርዕድ ጂ/አምሃ ከመታጠቢያ ቤት እንደተመለሱ።

"ግዝግዛ ግንበር ጀርባ፤ መኪኖች አግኝተን ደበደብን ነው የሚሉት" በማለት መለሱ። የደረሳቸው መረጃ የተረጋገጠ እንዳልሆነ በሚገልጽ ስሜት።

"ጥሩ ነው። ይሄ የቃፊር በረራ መቋረጥ የለበትም። የኤርትራ አየር እስካልዘጋ ድረስ ቀን በቀን ሰማዩን ሞልተነው መዋል አለብን" አለ ጋሽ መርዕድ፤ ምግብ እያነሱ ያሉትን ጀ/አምሃን እየተመለከተ።

"ሰሞኑን ብቻ እንደዛሬው ክፍቶ ቢውል ጥሩ ነበር" አሉ ጀ/አማሃ። ከዶሮው አገልግል እያወጡ። ሜ/ጀ/አማሃ ፊታቸው ቀይ ሆኖ ረዘም ያለ ሲሆን የጥርሶቻቸው ቀለም ሲጋራ ለብዙ ዓመት እንዳጤሱ ይመሰክራሉ። ምግቡን ይዘው ተቀመጡ።

"ተሰፋዬ ቅድም የተነጋገርነውን አስፈፀምክ እንዴ?" አለ አባቴ ወደ ኮ/ተሰፋዬ ትርፌ ዞር ብሎ።

“አስተላልፌያለሁ ጌታዬ። መልሱ እንደ ደረሰህ ደውልልኝ ብዬዋለሁ የዘመቻ መኮንኑን” አለ።

ኮ/ተሰፋዬ ረዘም ያለና ደልዳላ ሰውነት ያለው በወታደራዊ ቁመናው የታወቀ ወጣት ኮሎኔል ነው። ብዙ ጊዜ ከአባቴ ጋር የሠራና በሥራ በጣም የሚግባባ ከመሆኑም በላይ በወታደራዊ ትምህርት ማስተማር ችሎታው ሲመሰገን እሰማለሁ። በእጩ መኮንነት የሰለጠነው እንግሊዝ አገር ሳንድሀረስት በተባለ በሚታወቀው እንግሊዞች በሚኮሩበት የመኮንኖች ማሰልጠኛ ት/ቤት ነው። እዚያ ባገኘው የላቀ ውጤት ከእንግሊዝ ንግሥት የወርቅ ሻምላ የተሸለመ መኮንን ነው። ኮ/ል ተሰፋዬ ትርፌ (በኋላ ብ/ጀ) በአንደኝነት ተሸላሚ ሆኖ ሲቀርብ፣ በሳንድኸርስት ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ሁኔታ እንደነበረ ብዙ ይነገር ነበር። ከዚያም በፊት “ጥቁር” ምሩቅ በዚያ ማዕረግ ተመርቆ አያውቅም። የእንግሊዝም ንግሥትም በአንደኝነት ስትሸልም የኖረችው ነጮችን ስለነበረ የኮ/ተሰፋዬ ልቆ መገኘት ብዙዎችን አስገርሞ ነበር። ኮ/ል ተሰፋዬ በኋላ ብ/ጀነራል ሆኗል። በግንቦት 8 የመፈንቅለ መንግሥት ውስጥ በመሳተፉ ሌ/ኮ መንግስቱ ባቋቋሙት የይስሙላ ጦር ፍርድ ቤት የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው በግፍ ከተገደሉት ውስጥ አንዱ ነበር። መልከ መልካም፤ ሲራመድ የሚነጥርና በወታደርነቱ የሚኮራ መኮንን ነበር። ከመኮንነት ሌላ ምንም ዓይነት ሥራ የሚስማማው አይመስልም። ከልጅነቴ ጀምሮ አውቀዋለሁ። አባቴ የቀደማዊ ኃ/ሥላሴ የሐረር ጦር አካዳሚ የትምህርት ዳይሬክተር እያለ እሱ አስተማሪ ሆኖ





ሠርቷል። የምንኖረውም ባንድ ግቢ ውስጥ ነበር። ከልጆቹም ጋር በጓደኝነት ስንጫወት ነው ያደግነው።

“ተከታትለህ አስፈጽም በጣም አስፈላጊ ነው። እነሱ እንደ ህጻን ልጅ ካልተከታተሏቸው ያልተባሉትን ሲሠሩ ነው የሚውሉት ።” አለ አባቴ ግንባሩን ቋጠር ፈታ እያደረገ።

“እሺ ጌታዬ” አለ ኮ/ተሰፋዬ። ለአባቴ ያለው ክብር ከፍተኛ ነበር። ገና የ1966 ለውጥ ሳይመጣ ሕንድ አገር በታወቀው የህንድ ጦር ሰራዊት ከፍተኛ መኮንኖች ማሰልጠኛ ማእከል አብረው ለአስር ወር ትምህርት ሄደዋል። በዚያ ላይ ለብዙ ጊዜ በቅርብ ስለሰሩ በጣም ይግባባሉ። በመከላከያ ሚ/ር የዘመቻና የትምህርት ዋና መምሪያ ክፍል ውስጥ የዘመቻ ጉዳይ ኃላፊ ሆኖ ነበር ከጀ/ደምሴ ጋር የሚሠራው።

ጀ/ኃይሉ “በሉ እንግዲህ እኔ ወደ ሜንስ ቤት ሄጄ ልመርቅላቸው፤ መርቅልን ብለው ጠርተውኛል።” እያሉ በጣም በረጋ ድምጽ ተናግረው ለመሄድ ተነሱ“። የመኮንኖች መመገቢያ አዳራሽ ሜንስ ቤት ነው የሚባለው።

ድንገት “ጌታዬ ጥያቄ ነበረኝ” አሉና ብድግ አሉ ካኘቴን መርሻ። እስካሁን ዝም ብለው ተቀምጠው ነበር። የታወቁ የባህር ኃይል መኮንን ናቸው። ከቀድሞ አለቆቻቸው ጋር ብዙም የማይስማሙና የተሰማቸውን የሚናገሩ ሰው ስለነበሩ ብዙ ሹመቶች አልፈዋቸዋል። ቀጠን ያሉና መካከለኛ ቁመት ያላቸው ሲሆን ቀጥ ያለው አፍንጫቸው ፊታቸው ላይ ጎልቶ ይታያል። ኮ/መርሻም በመከላከያ ሚኒስቴር የዘመቻና የትምህርት ዋና መምሪያ ውስጥ

የባህር ኃይል ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ ሆነው ነው የሚሠሩት። እንደ ኮ/ተሰፋዬ ከጀ/ደምሴ ጋር በኤርትራ ለተፈጠረው ችግር መፍትሄ ለመፈለግ ነበር የመጡት።

"ሽ ምን ነበር መርሻ?" አሉ ጀ/ ኃይሉ፣ አሁንም ረጋ ባለ ድምጽ ።

"ሽጉጥ ሳልይዝ ነው የመጣሁት። ድንገት ከመንገድ ተጠርቼ ስለመጣሁ ልብሴንና እቃዎቼን እንኳን ለመያዝ አቤት መሄድ ስላልቻልኩ በአውሮኘላን እንዲልኩልኝ ነው ያደረግኩት።" አሉ ካ/መርሻ በተጠንቀቅ ቆመው።

ጀ/ ኃይሉ የምድር ጦር ዋና አዛዥ ስለነበሩ የጦር አዛዥ በሌለበት በሰሜን ኢትዮጵያ፣ ለጊዜው የትጥቅና የድርጅት ኃላፊም ጭምር ሆነው ነበር ከአዲስ አበባ የመጡት። "ሾፌሩን ላክዋ ታዲያ እንዲሰጡት አደርጋለሁ።" ብለው አሁንም በረጋ አካሄድ ወደ ውጭ ወጡ።

"እሺ ጌታዬ! " ብለው ካፒቴን መርሻ ወደ መቀመጫቸው ተመለሱ።

"ይሄን ቦንብ እየጨረሱ እኮ ነው።" አሉ ጀ/አማሃ ሰፍኖ የነበረውን ጸጥታ አቋርጠው።

"ለመሆኑ በደንብ እያገኙ ነው ወይስ እንዲያው ትንሽ እንቅስቃሴ ሲያዩ ነው የሚጥሉት?" አለ ጀ/መርዕድ። "ደብድበን አሳስተናል ትሉና ጠሩ ሲገባ እንዳሉ ነው የሚያገኛቸው። እንዴት ነው ባክህ?" ብሎ ቀጠለ ፈገግ ብሎ፣ የልቡን ነገር ግን ላለማሳወቅ እንደፈለገ ዓይነት።

"ማወቅ አይቻልም እንግዲህ። በተለይ አንድ ሆኖ ከሄደ የሚሰጠንን መረጃ መቀበል አለብን።" አሉ ለጀ/አማሃ።

"አዎ ታዲያ እኮ አሁንም ከመጣው ሃያ አራት ቦንብ ውስጥ አስራ አንዱን በሶስት ቀን ውስጥ ጣሉ። እና ባይሆን አመቺና ተገቢ ሁኔታ ካልሆነ





በስተተር ይሄን ቦንብ ባይጠቀሙ ጥሩ ነው። ተጨማሪ እስከሚመጣ ትንሽ ጊዜ እንደሚወስድ ነው ከላይ የተነገረኝ።" አለ ጀ/መርዕድ ጀ/አማሃን አትኩሮ እየተመለከተ።

"አሆ እኔም ይህንኑ ነው ያልኩት! ፖይለቶቹን ሁሉ ሰብስቤ እነጋግሬአቸዋለሁ።"

ጀኔራል መርዕድ ቀጠለና "ውጊያውን አሁን እኛ መውሰድ አለብን። ከእንግዲህ መቼና የት እንደምንዋጋ ሻዕቢያ ሳይሆን እኛ መወሰን አለብን። ተጨማሪው ጦር በፍጥነት መምጣት አለበት። ከአዲስ አበባ ይመጣል ያሉት አዲስ ጦር እንኳ ወደ ጊንዳ አካባቢ ሄዶ ልምምድ ቢያደርግ እንጂ ለጦርነት የተዘጋጀ አይመስለኝም።" አለ።

"ከሐረር የመጡትና የሚመጡት ታንከኛ ብርጌዶች ግን ደህና ልምድ ያላቸው ናቸው።" አለ ጀ/ደምሴ።

"እረ ውጊያ ላይ ውለዋል?" ጀ/መርድ እንደማጣራት አይነት ጠየቀ፣ የቀረበውን ቡና እየተጎነጨ።

"የቆዩ እኮ ናቸው። ሐረር ብዙ ተዋግተዋል። የመጡት አሁን ምጽዋ የተራራ ውጊያ እየሰለጠኑ ናቸው። እንጨርሳለን ብለዋል፣ ሄጄ አያቸዋለሁ።" ብሎ ተነሳ። ጀኔራል ደምሴ እጁን ታጥቦ ከጨረሰ በኋላ በትረ መኮንኑን /በጎን የሚሸጣትን በትር/ አንስቶ። "እንግዲህ ትንሽ አመሽ ይሆናል ግን ማታ እንገናኛለን" ሲል

"እኛም ወጪዎች ነን" በማለት ጀ/መርዕድም ተነሳ። በቤቱ የነበሩ ሁሉ እየተነሱ አንድ ባንድ እኔና እናቴን ጥለው ወጡ።

## -3-

ከቀኑ ሁለት ሰዓት ገደማ አስመራን ለመጎብኘት ከእናቴ ጋር በመኪና ወጣን። በከተማው የሚያንሸራሽረን ስሙን የረሳሁት መኮንን ወይም ሙሉጌታ ሁለተኛው የአባቴ ሹፌር ነበር። በከተማው ኮርነሮች ላይ ክላሽኒኮቭ መትረየስ ከነሙሉ ትጥቃቸው የያዙ ወታደሮች ቆመዋል። አቋቋማቸው አንደኛው ጥግ ላይ ያለው ወታደር ወደ ምሥራቅ ሲመለከት በኋላው ጥግ ያለው ደግሞ ወደ ምዕራብ እየተመለከተ ነው - ጀርባቸውን ተሰጣጥተው ቆመዋል ።

የአስመራ ሕዝብ ከመሀል አገር የመጣን ሰው ለመለየት ሰኮንድ አይፈጅበትም። የምንንሸራሸርባት ነጭ ፔጆ 504 የግል ታርጋ ቢኖራትም ሰው ሁሉ የሚያውቃት መሰለኝ። ሹፌሩም አስመራ ብዙ የቆየና ባለቤቱም የአስመራ ሰው ስለነበረች ትግርኛውን አቀላጥፎ ነው የሚያወራው። ከተማዋን ዞረን ካዳረስን በኋላ አንዳንድ ሱቆች ውስጥ እቃ ለማየት ከመኪና ወርደን በእግር መዞር ጀመርን። ሰው ሁሉ ስንሄድ መንገድ ይለቅልናል። ግራ ገባኝ፤ የሚያየኝ ሰው ሁሉ የሚፈራኝ ወይም የሚጠላኝ መሰለኝ። ሁሉም ሰው አንድ ዓይነት አስተያየት አለው፣ ትኩር ብሎ አይቶ ወዲያው ቶሎ ብሎ ዐይኑን ይነቅልና ደግሞ ወደ ሌላ ቦታ ይመለከታል።





የሱቅ ባለቤቶች ብቻ መስተንግዶአቸው ለየት ያለ ነበር። ያየነውን ሁሉ የምንገዛ ይመስላቸዋል። ወጣቶች ደግሞ ከመንገድ ባሻገር እየተጠራሩ "አሎራ" ሲሉ ነው የሚውሉት። ጣሊያንኛና ትግርኛን መቀላቀል ጀምረዋቸዋል። የአራድነት ምልክትም ሳይሆን አይቀርም ብዬ ገመትኩ። ዕቃ ለመግዛት ብለን ስላልወጣን ምንም ሳንገዛ ወደ 6 ሰዓት አካባቢ ወደ ቀኛው ስቴሽን ተመለስን። ከከተማው ወደ 150 ኪ.ሜ ርቆ ጦርነት እየተካሄደ ቢሆንም ለአስመራ ሕዝብ ምኑም አልነበረም። ምሳ ሰዓት ላይ በሰማሁት የሰፈረብኝ ጭንቀት ከተማ ወጥቼ ስመለስ ቀለል አለልኝ። አንድን ነገር ካላሰቡት አያስጭንቅ አይደል፣ እንደዚያ ነው የአስመራ ሕዝብ ኑሮ። ያለውን እንደሌለ እየቆጠሩ መኖር።

ቤት ገብተን ትንሽ አረፍ እንዳልን በአስመራ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ የነበረው የአባቴ ታናሽ ወንድም ክበበው ቡልቶ ሊጠይቀን መጣ። ክበበው ግዙፍና ጠንካራ፣ ሰውነቱ ጠቆር ካለው ገጽታው ጋር በሄደበት ጎልቶ የሚታይና ሳያውቁት የሚያከብሩት፣ በመንገድ ፊት ለፊት ቢመጣ ቦታ የሚለቁለት ሰው ነው። ብዙ ጊዜ በሰፊ እጁ አጠንክሮ ነው ሰው የሚጨብጠው። ቀጫጭን እጅ ያላቸውና ከዚህ በፊት እጃቸው ተጨምቆ የሚያውቅ ከሆነ እጁን ላለመጨን እጃቸውን ወደ ኋላ አድርገው በማጎንበስ ሰላምታ ሰጥተው ለማለፍ ይሞክራሉ። ይህ ስልት ግን ሁልጊዜ አይሠራም። እናም ብዙ ሰዎች ገና ሲጨብጡት ይፈሩታል። ነገር ግን እሱ በጣም ገርና ካልደረሱበት ሰው ላይ የማይደርስ ቅን ልቦና ያለው ሰው ነው። ቶዲያ ይህ ያልተናደደ ጊዜ ነው። የተናደደ ቀን ግን አያድርስ ነው። ሲቆጣ

እጆቹን ወደ ላይ ያነሳና ባለ በሌለ ኃይሉ ሁዱን ይመታል። ያን ጊዜ የት ልግባ ነው የሚያስብለው። ግን ቂም አይዝም። ወዲያው ይረሳል። ሰው በስራው ሲገባ የማይፈቅድና እሱም ሰው ጉዳይ ውስጥ ጨርሶ የማይገባ ሰው ነው። አስመራ ከተማ ውስጥ አስር ዓመት በፋብሪካ ሥራ አስኪያጅነት ሠርቷል። አስመራ ከተማው ናት። መግቢያ መውጫዋን ያውቃል። አስመራ ራሷ ሳታውቀው የቀረች አይመስለኝም።

ከክበበው ጋር ስንጫዋወት አመሸን። አባቴ ከሥራ ሲመለስ ወደ ምሽቱ 3 ተኩል ሆኗል። ጊዜው ለአስመራ በጣም መሽቶ ነበር።
“ታዲያስ ባክህ? የት ጠፍተህ ሰነበትክ?” አለ ሲገባ ወንድሙን አይቶ።
“እንደምነህ ጋሽ ደምሴ? ምን ይኼ የፋብሪካ ሥራ ይዞኝ ነዋ! ለናንተ የምንሠራው ልብስ ማድረስ አለ አይደል.. ሃያ አራት ሰዓት ያለማቋረጥኮ ነው የምንሠራው” አለ ክበበው ሠላምታውን እየመለሰ። ለክአባቴ የሶስት ዓመት ብቻ ታናሽ ቢሆንም ጋሼ እያለ ነው የሚጠራው።
“ታዲያ ምን ጋበዛችሁት?” አለ አባቴ ኮፍያውንና የሚይዛትን በትር እያስቀመጠ። አባቴ መጠጥ ስለማይጠጣ ለአጎቴ፣ ለእናቴና ለራሴ መጠጥ ቀድቼ ለእሱ “ማይጋዝ” (የአስመራ አምቦ ውሃ) ሰጠሁት። በቤታችን ልጆች መጠጥ እስከ ተወሰነ ደረጃ መጠጣት ይፈቀድልናል።
“ከረን ውዬ መምጣቴ ነው” አለና አባቴ በሰፊው ተነፈሰ፣ ከላዩ ላይ ድካሙን እንደሚያራግፍ ዐይነት።
“እንዴት ነው?” አለ አጎቴ ለመስማት ጠጋ እያለ።





"አሁን ትንሽ ይሻላል። ከእንግዲህ ከረን አያሰጋንም። እንደምንም ቀሬባርበን አድነናታል። ወንበዴው ያልጠበቀው ነው የደረሰበት። በዚህ ሁሉ ዓመት ውስጥ ይሄን ያህል አደጋ ደርሶበት አያውቅም። ምናልባትም ከእንግዲህ በዚህ ሁኔታ ላይገጥሙን ይችላሉ። አየህ አሁን የነሱ ችግር እንደ ጎሪላ መዋጋት አለመቻላቸው ነው። አንዳንድ ቦታ ላይ ታንክና ብረት ለበስ ይጠቀማሉ። ስለዚህ የጎሬላ ሥልት መሆኑ ይቀርና እንደ መንግሥት ይሆናሉ ማለት ነው። ጎሬላ እየሰፋና እያደገ ሲሄድ ስልቱን መቀየር አለበት። አሁን አፋበትን ከያዙ በኋላ ተጠርተን ስንመጣ ጠሩ ተደናግጠ ነው የጠበቀን። ሰውዬው እዚህ መጥቶ የነበረውን ስትራክቸር አፈራርሶ በምትኩ ምንም ሳይተካ እንዳለ ጥሎ ተመለሰ። እና የዚህ ዐይነቱ ነገር እንደሚደርስ ግልጽ ነበር። ጠሩን አረጋግተን በየትናንሽ ከተሞች ተበታትኖ የነበረውን ሁሉ ከረን ላይ ካሰባሰብን በኋላ ዙሪያውን የመከላከያ ወረዳ አዘጋጀን። እነሱም በታንክና በብረት ለበስ እየታገዙ መጡ። መግደያ ወረዳ እስኪደርሱልን በከባድ መሣሪያ ብቻ እየተከላከልን ቆየንና ምን ልበልህ ከባድ መትረየስ እንደዚህ ተጠቅመን እናውቅም፣ ወደ ሶስት ሺህ ወንበዴ ነው በዛ ጦርነት ያለቀው። ሜዳ ላይ አገኘናቸው። የግድ ሜዳውን ማቋረጥ ነበረባቸው። እነሱም የፈለጉት ቶሎ ሜዳውን አቋርጠው ለማለፍ ነበር። የከረን ስትራቴጂካዊነት እዚህ ላይ ነው። ዙሪያዋን በተራራ የተከበበች ነች።
“እቤት! አቤት!አቤት! ሶስት ሺህ ኸ! ብዙ ነው”
"በተለይ ለሸፍታ ብዙ ነው። ይህን ያህል ሰው ከሞተባቸው ብዙ ጊዜ ነው።”
አለ ጀ/ደምሴ ማይ ጋዙን እየተጎነጨ።
"እና እንዴት ነው አሁን?”

“እሱማ እንግዲህ የኤርትራ ችግር እንደዚህ በቀላል የሚፈታ አይደለም። ጠሩ ተሰላችቷል። አዲስ አበባም የገባቸው አይመስለኝም። ዝም ብለው መዝፈን ብቻ ነው። እኛ የምናቀርብላቸውን ሪፖርት ከማጥናት ይልቅ ለሳምንት መጥተው የሚሰሙትን አሉባልታ ነው የሚቀበሉት። እና እንደዚህ በቀላሉ የሚያልቅ አይደለም። አሁን ማድረግ ያለብንን እያደረግን ነው። ከረንን ማዳን መልሶ አጥቅቶ እስከ አፍአበት መግፋትና እነሱ እንዳይንቀሳቀሱ ማድረግ ነው። ብቻ ምን ያደረጋል መልሰው ያጨመላልቁታል። ለረጅም ጊዜ ተብሎ የሚሰራ ነገር ጨርሶ የለም፣ ዝም ብለው ተቀምጠው ይሰነብቱና አንድ ነገር ሲያጋጥማቸው ይጮኻሉ። ሌላው ቀርቶ ከረን ላይ ይህን ያህል ሲቀመጡ በቂ ምሽግ አልነበራቸውም። የነበረውም አልተጠገነም። ከመጣን ነው እንደገና ያሠራነው።

በየቀኑ ለሚፈጠሩ ችግሮች መልስ ስንፈልግ ከሆነ ጊዜያችንን የምናጠፋው የውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ጨዋታ ሆነ ማለት ነው። እሱን ነው አሁን የተያያዝነው። ያሳዝናል ሥራው በሚገባ ተሠርቶ ቢሆን ኖሮ ትግራይ እንኳን እንደዚህ ዓይነት ደረጃ ላይ ልትደርስ ባልቻለች ነበር። እኔ ራሴ ሄጄ ሁኔታውን ለአንድ ወር ካጠናሁ በኋላ፣ ለብዙ ጊዜ ተወያይተን፣ የሁኔታውን አስጊነትና ያኔውኑ አፋጣኝና ከባድ እርምጃ መውሰድ እንዳለብን በሪፖርት መልክ ባቀርብ “ይህን ያህል እንኳን አይደርሱም ሆኖም ትኩረት እንሰጠዋለን” ነበር የሰውየው መልስ። ታዲያ አሁን መልሶ እኔኑ ይጠይቀኛል ምን እዳደርግለት ነው አሁን? ከእንደዚህ ዐይነቱ ሰዎች ጋር ምን ትሠራለህ? ባለፈው የምንፈልገው ቦታ አስገብተናቸው፤ መፈናፈኛ





አሳጥተናቸው ነበር። ባስቸኩዋይ ወደዚህ ስመጣ እንደገና ነገሩ ተበላሸ። ውሃ ቅዳ፤ ውሃ መልስ ነው።” አለ ከምሩ በንዴት እየተናገረ። ሲያመር ፊቱ ሁሉ ነው አብሮ የሚያመረው። ግንባሮቹ ቋጥር ይሉና ፊቱ ይንቀጠቀጣል። ለሚያው ሳያውቀው አብሮ እንዲያመር የሚያደርግ ፊት አለው።

“የትግራይ ደግሞ በጣም የሚገርም ነው በተለይ የሽሬና የእንዳ ሥላሴውን ለማመን ያስቸግራል። ያ ሁሉ ጦር እንዴት እንደዚያ ሊበተን ይችላል?” አለ ከበበው በእጁ የያዘውን ብርጭቆ እያሻሸ።

“የሚገርምህ ነው ጄኔራል አርአያ ቢሮዬ መጥቶ ነበር። እና ብዙ ተነጋገርን፤ ትልቁ ችግር ወታደር የለም። ያለው ወታደር ከየከተማው ተሰብስቦ ሶስት ወር ባልሞላ ጊዜ የሚላክ ነው። እና እነሱን መሣሪያ ሰጥቶ ቀዋት ማለት በውነቱ ሃጢያት ነው። ድሮ ኤርትራ ውስጥ አንድ ክፍለ ጦር ብሎ ነበር። አንድ ሻለቃ ጦር ወጥቶ አፈር አስግጦ ነበር የሚመለሰው። አሁን ያለው ጦር መሸሽ ለመደ። ጦር ደግሞ ከሸሸ ዋጋ የለውም። ጠሩ አይዋጋም። ሳይተኩስ ነው የሚሸሸው። ከምድር ተነስተው ጀግና፣ ጀግና ብሎ ማለት ነው። በጣም የሚገርምህ ደግሞ ድንገት መጡብን የሚሉት ነገር ነው። ጦርነት ድንገት ሊጀምር ከቻለ ጠሩ ትልቅ ችግር አለው ማለት ነው። በወታደር ድንገት የሚባል ነገር መኖር የለበትም። ሁል ጊዜ ቀዝግጅቶ መጠበቅ አለበት። በተለይ የዚያ ዓይነት ግንባር ላይ። እና ወደ አስራ ስምንት ሺህ ጦር ቦታውን ለቆ ሄደ። ውርደት ነው። ውርደት! ምንም ቢሆን እንኳን አስራ ስምንት ሺህ ጦር ቀርቶ መቶ ሰው ይሸሻል? አንድስ

ሰው ቢሆን እንዴት ሳይተኩስ ይሸሻል? አርአያ ጠሩ ጥሎት ሄደ ከተወሰኑ ወታደሮች ጋር ጥቂት ታንክና መኪናዎች ይዞ ሲሄድ አንድ ከተማ ይገባል። የሚገርማችሁ የዚያ ከተማ ሕዝብ ሽማግሌውና ሴቶች ሳይቀሩ ተኩስ ከፈቱበት። የሚገርማችሁ እኮ ነው። ለማና ለምን እንደምንዋጋ ሰው ገና አልገባውም፤ እኛ ለመንግሥቱ ኃይለማሪያም አይደለም የምንዋጋው፤ ለኢትዮጵያ ነው። እና የዚህ ዓይነቱ ድርጊት በጣም ያሳዝነኛል። በመንገድ ላይ ጥለውት የሄዱ ወታደሮች ሁሉ አሉ። ድሮ እንኳን ወታደር አለቃውን ትቶ ሊሄድ ቀርቶ የአለቃውን ሬሳ እንኳን ትቶ አይሄድም። ጦር የለንም ዝም ብሎ ማግበስበስ አይደለም። አየህ ደንበኛ ጦር ያስፈልግሀል።"

"አ-ቤት አ-ቤት አ-ቤት!...በቃ ደህና ዋል ብለውት ሄዱ ኧ!? አቤት አቤት! አቤት!!"

የመጨረሻዋን "አ-ቤት" የምትለዋን ረገጥ አድርጎ አንደ በረጅሙ አፏጨ። አጎቴ ከበበው የሚያስገርም ነገር ሲየጋጥመው አቤት! አቤት! አቤት! ካለ በኋላ ማፏጨት ልማዱ ነው።

"ትግራይ ደርሼ ነው ወደዚህ የመጣሁት እዚያ ስደርስ ሁሉ ነገር ተመስቃቅሎባቸው ነው ያገኘኋቸው። ምንም ማድረግ አልተቻለም። ጊዜ የለም ነበር። ሌላው ቀርቶ አድዋና አክሱም ያለንን ጦር ለማጠናከር ጊዜ የሚሰጥ አይደለም። አድዋ ደርሼ አነጋግሬያቸው ወደ አክሱም በሄሊኮፕተር ተነስቼ አስር ደቂቃ ሳንበር ጦርነት ተጀመረ። ጀነራል ለገሠን አነጋገርኩት። ጠሩ ምንም ሳይዋጋ ግማሹ መሣሪያውን እየጣለ መሸሸ ሲጀምር ለገሠ





"በኢትዮጵያ!" እያለ ቢጮህ የሚሰማው አጥቶ ራሱን ሊገድል ሲል አንድ ሻምበል አስጣልኩት አለኝ። ሄሊኮፕተር ልላክልህ ስለው "የኔ ታሪክ እዚሁ ቀለህዊ ቦታ ላይ ያልቃል" ብሎ ዘጋ። ለገሠ ጥሩ መኮንን ነበር። ራሱን ገደለ። እንዴት አዘንኩ!" ብሎ ትንሽ ተከዘ። ሁላችንም ዝም አልን። ከጀ/ለገሠ ልጅ ከአያልነህ ጋር ት/ቤት አብረን ተምረናል። የጀ/ለገሠ እሟማት በጣም አሳዘነኝ።

አባቴ ወጉን ቀጠለ። "ታዲያ ያቺ ሻምበል ከአራት ወታደሮች ጋር ጠፍተን ስንሄድ ማነው ስሙ? ስሙ ጠፋኝ- እዎ ሀብተሥላም ነው ያለኝ መሰለኝ- መንገድ ላይ ደከምንና አንድ ቦታ አረፍን አለ። ወታደሮቹ ጋደም እንዳሉ እንቅልፍ ወሰዳቸው፤ ቀን ሌሊት ስለተጓዙ ደክሟቸው ነበር። ሻምበሉ ግን አንድ ከፍታ ላይ ያለ ዛፍ ላይ ወጥቶ ተቀምጧል። ወዲያው ሳያስበው ጥቂት ወንበዴዎቹ እቦታው ደረሱ። ለመንቀሳቀስ አልቻለም። ወንበዴዎቹ 'ወታደር! ወታደር!' ቢሉ ወታደሮቹ ሊነሱ ነው? ዝም። እንቅልፍ ይዟቸው ሄዷል። ደክመዋል። ትንሽ ተነጋገሩና አንደኛው ወንበዴ በመትረየስ ጨረሳቸው። ሻምበሉም ዝም ብዬ ቀይቼ ሲሄዱልኝ ጉዞውዬን ቀጠልኩ አለ። መች በዚህ ያቆምና፤ መንገድ ላይ ሲሄድ ደግሞ አንድ ቤት ያገኝና ይገባል። ውሃ አግኝቶ ጠጣና በር ስር ትንሽ ደገፍ እንዳለ እሱም እንቅልፍ ይዞት ይሄዳል። ትንሽ ቀይቼ ከበደኝና ነቃሁ አለ። ሲነቃ አንድ ሽማግሌ ፊት ለፊቱ ቀመው በእጃቸው 'እይቼሃለሁ ተኛ' የማለት አይነት ምልክት ሰጡት። ትንሽም አልቆየ የመኪኖች ድምጽ ተሰማ፤ ሰውየው ወዲያው ወደ ውጭ ወጥተው ቤቱን ዘጉት። ወንበዴዎቹ ቆም ብለው

‘ወታደሮች ወደዚህ አልፈዋል?’ ብለው ይጠይቋቸዋል። ሽማግሌውም ‘አዎ ትንሽ ቆይተዋል እንጂ አልፈዋል’ ብለው ይመልሳሉ። ‘ውሃ አለ?’ ይላል አንዱ ወንበዴ።
‘ወታደሮቹ ጠጥተው ሄዱ። አሁን ምንም የለም። እኔም ባለቤቴ ቤቴን ዘግታ ሄዳ እየጠበኳት ነው።’
‘እሺ እንመለሳለን’ ብለው ሄዱ ወንበዴዎቹ። ሻምበሉ ከዚያ ወጥቼ የነበረኝን ሰላሰ ብር ለሽማግሌው አመስግኜ ሰጥቼ ወደ አክሱም ጉዞ ቀጠልኩ አለ። አክሱም ሲደርስ ጦርነት እዚያም ተጀምሮ ደረሰ። የሚገርም ሻምበል ነው። ከጄኔራል አርአያ ጋር ነው እዚህ የመጣው።” ብሎ ሲጨርስ እኛም ከህልም እንደባነነ ሰው ነቃን። ጭንቅላታችንን በመገረም እየወዘወዝን ተያየን። እኔም የሰዎች እጣና የኑሮ ውጣውረድ አበዛዝ ለቁጥር የሚታክት መስሎ ተሰማኝ። ተኝተው የተገደሉት ወታደሮች በአእምሮዬ ውስጥ ተመላለሱ። ሞት የሚያስንቅ ድካም።

ራት በልተን እንደ ጨረስን “በል ወንድሜ እኔ ነገ በጥዋት ተነስቼ ወደ ምጽዋ መሄድ አለብኝ” አለ አባቴ የደከሙ ዐይኖቹን ክፍት ከደን አድርጎ ፊቱን በእጁ ከአበሰ በኋላ። አጎቴን እየተሰናበተ ተነሳ።
ክበበውም “አዎ ተኛ እኔም ሰዓት አላፊው ሳይዘኝ ልሄድ” ብሉ ብድግ አለ ። ከሰው ፊት ለፊት ሲቆም፣ ግዙፍ ሰውነቱ የክፍሉን ስፋት የሚቀንስ ይመስላል። ክበበውን ተሰናብተን ወደ መኝታ ቤታችን መሄድ ስንጀምር “አባዬ ምፅዋ አብሬህ መሄድ አችላለሁ? ምፅዋን አይቼ አላውቅም” አልኩ በመማፀን ዓይነት። ብዙ ጊዜ የወታደር ትርዒት ሲኖር ይወስደን ነበር።





በእንደዚህ ባለ አስጊ ጊዜና ቦታ ግን ከዚህ በፊት ማናችንም ወስዶ ስለማያውቅ አይፈቅድልኝ ይሆናል ብዬ አሰብኩ።
“በጠዋት ተነስ። ቁርስ ይዘጋጅልሀ። እኔ ከዚህ በ5 ሰዓት እወጣለሁ። ሹፌሩ በ6 ሰዓት መጥቶ ቢሮ ያመጣሃል። ከዚያ ነው የምንሄድው።” ብሎኝ ወደ መኝታ ቤቱ አመራ።
“እሺ ግድ የለም እነሳለሁ። ደህና እደር።” ብዬ እየፈነደቅኩ ወደ መኝታዬ ሄድኩ።
“ለምን ተነሳህ? ትንሽ መተኛት ትችል ነበር። ገና ነው እኮ” አለኝ በለሆሳስ ድምጽ ሰው ላለመቀስቀስ።
“እንቅልፍ እምቢ አለኝ። አሁን ካንተ ጋር ሄጄ ቢሮ ብቆይ ይሻለኛል አልኩ።
“በል ቶሎ ልበስና ቁርስህን ብላ” አለኝ ጺሙን ለመላጨት ፊቱን የጺም ሳሙና እየተቀባ። ከሱ ጋር የትም ቦታ ከመሄዳችን በፊት ቁርስ መብላታችንን ሳያጣራ አይወስደንም። የወታደር ልጅ ትንሽ የወታደር ባህል ይዞ ነው የሚያድገው።

ከቤት ስንወጣ አንድ ቶዮታ ላንድክሩዘርና መትረየስ የተጠመደበት ግልጹ ቶዮታ ላንድክሩዘር ቆመው ጠበቁን። ወታደሮቹ ሁሉ ባንድ ላይ ሠላምታ ሲሰጡ የቀኑ መጀመር ተሰማኝ። ቢሮው እዚያው ግቢ ውስጥ በጣም በቅርብ ርቀት ቢሆንም በመኪና ነው የሚሄዱት። አንዳንድ ጊዜ ብቻ በጣም ጊዜ ሲያገኝ ከቢሮ በእግር ወደ ቤት ይመጣል። በተረፈ ኑሮ ጥድፊያ ነው። የማያቋርጥ ሽክርክሪት። ቢሮ ስንደርስ ሻምበል ጌታሁን

ቁጭ ብሎ ጠበቀን። ለብዙ ጊዜ ሳላገኘው በመቆየቴ የደምብ ሠላምታ ሰጥቶ እስኪጨርስ እንኳ ጊዜ አልሰጠሁትም ሄጄ አቀፍኩት። ከአባቴ ጋር ከሐረር ጀምሮ አብሮ የነበረና አዲስ አበባም አብሮ የመጣ ከዚያም አስመራ አብሮ የተቀየረ። አባቴ እንደ ልጁ የሚያየው ረዳቱ (ኤ.ዲ.ሲ.) ነው። ቀጭን አጠር ያለ ቀምጫጫ ወጣት ሻምበል ነው። ሲቆጣና ትዕዛዝ ሲሰጥ ድምጹ የሱ አይመስልም። የአዛዥ ኤ.ዲ.ሲ. ወይም የቅርብ ረዳት መሆን የሚያስከብር መሆኑን የሚያውቅ ክብሩንም ለመጠቀም ወደ ኋላ የማይል ሰው ነው። ስለዚህ ማንኛውንም ጉዳይ ያስፈጽማል፤ ልባም ሻምበል ነው። እኔም እንደ ወንድሜ ነው የማየው። በጣም ቀጭን ስለሆነ ሳቅፈው የወፈርኩ ሆኜ ይሰማኛል። ስለዚህ ደጋግሜ አቀፍኩት። ከሻ/ጌታሁን ጋር ትንሽ ካወራሁኝ በኋላ ወደ ዋናው ቢሮ ገባሁ። እዚህ ቢሮ ስገባ የመጀመሪያዬ ጊዜ ነበር። ቢሮው፣ አንድ ዓይነት ስሜት ሰው ላይ ያሳድራል። ገና ከውጭ የሚገባ ሰው፤ ቢሮው ውስጥ በኢትዮጵያ ባንዲራ እና በጦሩ አርማ መሀል የተቀመጠውን ሰው፣ ሳይወድ በግድ እንዲያከብርና እንዲፈራ ያደርገዋል።

በግድግዳው ላይ የተለያዩ ወታደራዊ ነክ ሥዕሎችና ዓርማዎች ተሰቅለዋል። ከተሰቀሉት ውስጥ የሜዳሊያና ኒሻኖች ዓይነትና ትርጉም የተለጠፈበትን ሳይ ስለኒሻንና ሜዳሊያዎች የሰማሁት ትዝ አለኝ።

በኢትዮጵያ የመጨረሻውን የጀግና ሜዳሊያ ያገኙ ሶስት ሰዎች ናቸው። አንደኛው የአየር ወለድ ጦር አዛዥ የነበሩት ብ/ጀነራል ተስፋዬ





ሀ/ማርያም ናቸው። ናቅፋ ላይ የአየር ወለድ ጦር ተከቦ ከወረደበት የመድፍና የሞርታር ጥይት ናዳ ሰብረው ካመለጡት ውስጥ አንዱ ነበሩ። ሁለተኛው ተሸላሚ በሶማልያ ወረራ ወቅት በርካታ የጠላትን አውሮፕላኖች ያወደሙት ብ/ጀነራል ለገሰ ተፈራ ናቸው። ሌላው ተሸላሚ መንግሥቱ ኃ/ማሪያም ሲሆኑ ለምን እንደ ተሸለሙ ራሳቸውም የሚያውቁት አይመስለኝም። በኢትዮጵያ ከፍተኛ የጦር ጀብድ ፈጽመው የህይወት መስዋእትነት ጭምር የከፈሉ፤ ነገር ግን ስማቸው እንኳ የማይታወቅ በርካታ ጀግኖች እንደነበሩ ይታወቃል። ለምሳሌ ሻለቃ ማሞ ተምትሜ የተባሉ ከክብር ዘበኛ ወደ ጦር ሰራዊት ተቀይረው ናቅፋ ላይ የነበረው ጦር አዛዥ የነበሩት አንዱ ናቸው። በውጊያ ላይ ከቆሰሉ በኋላ እስከ መጨረሻው ድረስ እየተዋጉ ቆይተው በመጨረሻ ሌሎች ሰብረው እንዲወጡ ለእሳቸው ግን አንድ ሽጉጥ ብቻ እንዲተውላቸው ካደረጉ በኋላ ራሳቸውን አጠፉ። እኚህን ሰው ወንበዴዎች በክብር ቀብረዋቸዋል። የኢትዮጵያ ጀግና ግን አልተባሉም።

ከጥዋቱ ወደ ስምንት ሰዓት አካባቢ ወደ ምጽዋ ለመሄድ ወደ አስመራ አየር ማረፊያ በረርን። በምንሄድበት ጊዜ የከተማ መብራት አንቀምም ነበር። ከኋላ መትረየስ የተጠመደበት ግልጽ ቶዮታ ይከተለናል። መብረር ነው። አየር ማረፊያ ስንደርስ ሁለት የባሕር ኃይል መኮንኖች እና ሌሎች መኮንኖች ይጠብቁን ነበረ።

ካፒቴን መርሻ አዲሱን ሽጉጣቸውን አገልድመው ከባህር ሃይል መኮንኖች ጋር ይጫወታሉ። ሁሉም በተጠንቀቅ ቆሙና ሠላምታ ሰጡ። ሄሊኮፕተሯ እየተሟሟቀች ስለነበር ለመነጋገር ካልጮኹ አይሰማም። ታዲያስ ተዘጋጅታችኋል እንሂድ አለ ጀ/ደምሴ ወደ ሄሊኮፕተሯ እያመራ" "አዎን ጌታዬ" አሉ መኮንኖቹ። ሄሊኮፕተሯ ላይ ተሳፍረን ቀበቶአችንን አጠብቀን ወደ ውጭ ማየት ጀመርኩ እኔ መዝናናት ነበር የያዝኩት። እነሱ ደግሞ ሥራ ስለያዙ ለውጭው ብዙም ትኩረት አልሰጡትም። ሁሉም የሆነ ወረቀት ከየቦርሳው እያወጣ መመልከት ያዘ። ሄሊኮፕተሯ ትንሽ እንደ መንደርደር ብላ ተነሳች። ዓየር ማረፊያውን እንደ ዞረን ጉዞአችንን ወደ ምጽዋ አቅጣጫ አደረግን።

"ይሄ በ1969 ዓ.ም ካስቆፈርናቸው ምሽጎች አንዱ ነው" አለኝ አባቴ ጨክ ብሎ ጀሮዬ ሥር። ልጆቹን ስለማንኛውም ነገር በቁም ነገር እንደ ትልቅ ሰው ነው የሚያነጋግረው። እንግዶች መጥተው እንኳን ሲነጋገሩ አንድ አንድ ጊዜ እናቴ "ልጆች ሂዱ መኝታ ቤት ተጫወቱ" ያለች እንደሆን "ተያቸው" ይል ነበር። እና እኛም ከልጅነታችን ጀምረን ስለ ሥራውና ስለ አገር ሁኔታ እንጠይቀው ነበር። እያንዳንዷን ነጥብ (አንዳንዴም ካርታ እያሳየ) ዘርዝሮ ስለሚያስረዳን የምንሰማውን በአእምሮአችን ለመቅረጽ ችግር አልነበረብንም። እና ስለእነዚህ ምሽጎች 1969 ዓም ከአዲስ አበባ አስመራ ሄዶ ሲመለስ የነገረንን እያንዳንዷ ነጥብ ሳትቀር አስታውሰው ነበር። በ1969 ዓ.ም ሻዕቢያ እና ጀብሃ የአስመራን ከተማ ለመያዝ 9 ኪ.ሜ ቀርቷቸው ነበር።





በዚያን ጊዜ አባቴ የመከላከያ ሚኒስቴር ሳይቋቋም በፊት የምድር ጦር የዘመቻ የትምህርትና የትጥቅ መምሪያ ኃላፊ ሆኖ እየሰራ እያለ ወደ አስመራ የሁለተኛ ክ/ጦር አዛዥ ሆኖ ሄደ። ይህ 2ኛ ክ/ጦር በአፄ /ሥላሴ ጊዜ በሰሜን የነበረው አንድ ክ/ጦር ነበር።

ጀ/ደምሴ አስመራ ሲገባ የመጀመሪያ ሥራው መከላከያ ወረዳን ማጠናከር ነበር። ስለዚህም አስመራ ዙሪያዋን ሶስት ጊዜ በምሽግ ታጠረች። እነዚህ ሶስት የቀለበት ምሽጎች ለአስመራ ከተማ ዋስትና ቆሙ። በብዙ መሪባሪብና ትግል በሻዕብያና በጀበሀም መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ላቢያ አስመራ ከተማ ደርሶባት ከነበረው የጥፋት ጉም ነፃ ሆነች። ለኢትዮጵያ አንድነት የቆሙትን እነዚህን ምሽጎች ወደ ውጭ ማየቴን ትቼ መለስ አልኩና ከፊቴ ቁጭ ብሎ የነበረውን የባሕር ኃይል መኮንን ቃኘሁት። ካፒቴን ፊሊጶስ ነበር። የምፅዋ ባሕር ኃይል ባለሥልጣን ነበር። በኋላ የምፅዋ ባሕር ኃይል አዛዥ ሆኗል። ፊቱ ቀጭንና ረጅም አፍንጫው አለመጠን ቀጥ ያለና ዓይኖቹ የሚንቦገቦጉ ረዘም ያለ መኮንን ነው። ፊቱ ላይ ዓይኖቹ ጎልተው ይታይሉ። ብዙም አያወራም። ወረቀት ሲያገላብጥ ምሰዋ ገባ።

ሄሊኮፕተሯ ተንዥዋዥዋ ቆመች። ስንገባም ስንወርድም ከላይ ያለው ተሽከርካሪ ስለማይቆም አንገቴን ቆርጦ የሚጥለኝ ይመስለኝ ነበር። በሄሊኮፕተር ብዙ ጊዜ የሄድኩ ቢሆንም አምኘው አላውቅም። ያረፍነው

ባሕር ኃይል ግቢ በትልቁ ከተሳለ ከአፄ ቴዎድሮስ ሥዕል ፊት ለፊት ነበር። ከፓይለቶቹ አንደኛው መጥቶ በሩን ከፍቶ ደረጃ ዘረጋና ወርዶ ቆመ። እኔም አባቴን ተከትዬ ወረድኩ። የምጽዋ ሙቀትም በወላፈኑ ተቀበለን። ሊቀበሉን የመጡት መኮንኖች ፊቅ ብለው ቆመዋል። ጀ/ደምሴ ፈጠን ብሎ አመራና "ወጋየሁ ታዲያስ?" ብሎ በተጠንቀቅ የቆሙትን ግዙፍ ኮለኔል ሠላምታ ሰጥቶ ጨበጣቸው። ሌሎችም ሠላምታ ከሰጡ በኋላ "በሉ እንግዲህ እኛ ወደ ሥራችን እንቀጥላለን" ብለው የባሕር ኃይል መኮንኖቹን ተሰናበቱ። ወዲያው ቆመው ወደ ነበሩት ጂፕ መሳይ ዋዝ መኪኖች አመራን። እኔም ወዳመሩበት አቅጣጫ ሁሉ ፈጠን ብዬ መከተል ብቻ ነው። የሚባለውን ሁሉ እንደማይሰማ ዓይነት በግዴለሽነት ቆሜ ጆሮዬን ተክያለሁ። "ደረጀ" ብሎ ሲጠራኝ ሮጥ ብዬ ከኋላ ተሳፈርኩ። አባቴ ከፊት ገባ። ኮሌኔል ወጋየሁ እኔና የአባቴ ረዳት ሻምበል ጌታሁን ከኋላ ተሳፈርን። ከአባቴ የማይለየው አጃቢም ከበስተጀርባ ካሉት ወንበሮች ካንድ ሌላ ወታደር ጋር ተቀመጠ።

"ታዲያስ እንዴት ነህ ባክህ?" አለ ጀ/ደምሴ ወደ ኋላ ዞር ብሎ ውጋየሁን እየቃኘ። በጣም ረጅም ስለነበረ ወደፊት ትንሽ ጎንበስ ብሎ ነበር የተቀመጠው የመኪናው ጣራው እንዳይነካው።
"በደንብ እንደተዘጋጃችሁ ተሰፋ አለኝ ጊዜው ቢያጥርም ልምድ ስላላቸው የሚያስቸግራቸው አይመስለኝም" አለ ወደፊት ተመልሶ።
"ደህና ይዘዋል ዝግጁ ናቸው" አለ ኮለኔል ውጋየሁ በእርግጠኛነት።





"ልብ አድርግ በሁለት ሣምንት ውስጥ ጠርንት ልንልካቸው ነው። የሚቀራቸው ነገር ካለ አንድ ሣምንት ልሰጥህ እችላለሁ። የሚቀር ነገር መሞር የለበትም" አለ። አሁንም ወደፊት እያየ።

ከባሕር ኃይል ቅጥር ግቢ ወጥተን ከምጽዋ ከተማ ጋር ከሚያገናኘው መንገድ ላይ እየተጓዝን ነው። የምጽዋ ከተማ በስተግራ ትታያለች። በመንገድ ዳርና ዳር የውሃ ግድብ የመሰለ የጨው መሬት ይታያል። አልፎ አልፎ ውሃ ቢኖርበትም አብዛኛው ክፍል ደረቅ ነው።
"ይህ ምንድን ነው" በቀስታ ጎኔ ተቀምጦ የነበረውን ሻምበል ጌታሁንን ስጠይቀው አባቴ ሰምቶ፦
"ይሄ መሬት ለምፅዋ ባለውለታ ነው። ያኔ እነ መርዕድና (ጀ/መርዕድ)፣ ሙ፡ሻ (ካፒቴን) ምፅዋን ሲከላከሉ በጣም የጠቀማቸው ይሄ መሬት ነው። ውሃውን ለቀው ይህን የሚታየውን ክፍል በውሃ ሞሉ። ይሄ የምታየው ግድብ ስር ስር ነበር ወንበዴዎቹ የመሸጉት። እና ውሃው ሲሞላ የግድ መልቀቅ ነበረባቸው። ከግድቡ ሲወጠ ግድቡ ሥራውን ሰራ" አለ በጣቱ ግድቡንና ከግድቡ ጀርባ ያሉትን ዝቅተኛ ቦተዎች እያሳየኝ።

አንድ ጊዜ በእግር ስንጓዝ የጠየቀኝ ጥያቄ በአንጎሌ መጣ። አባቴ ለስብሰባ ወይ ደግሞ ለሌላ የሥራ ጉዳዩ ወደ አዲስ አበባ በሚመጣበት ጊዜ የነበረችውን ጥቂት የመዝናኛ ሰዓት ከቤተሰቡ ጋር ነበር የሚያሳልፈው። በተለይ ከሥራ በጣም ሳይመሽ ወደ ቤት የመጣ ጊዜ ልብሱን ቀይሮ፣ እኔና ዮናስን ታላቅ ወንድሜን አስከተሎ በእግር ሠፈር ውስጥ ዞር ዞር ማለት

ይወድ ነበር። የተለመደው መስመራችን ከቦሌ ድልድይ አካባቢ ከሚገኘው ቤታችን ጀምረን ወደ ቦሌ አየር ማረፊያ ደርሶ መልስ ነበር። በዝግታ እየተራመድን ስለተለያዩ ጉዳዮች እናወጋለን። እነዚህን ጥቂት ደቂቃዎች በጣም ተናፋቂና አስደሳች የሚያደርጓቸው አባቴ የሚሠነዝራቸው የተለያዩ ሐሳቦችና ድንገት የሚጥላቸው ጥያቄዎች ናቸው። አሁን ሳስበው አእምሮአችንን የሚፈትሽበት መንገድ እንደነበር ሆኖም ይሰማኛል። እናም ወደ ቦሌ አየር ማረፊያ በዝግታ ስንጓዝ ነበር አባቴ " ከሁሉ ኘሮፌሽኖች ከባዱ የቱ እንደሆን ታወቃለህ?" ብሎ የጠየቀኝ።

እኔም ዶክተር፣ ጠበቃ ሌሎችንም ዘረዘርኩና አይደለም የሚል መልስ ሳገኝ ወታደር እንድል እንደፈለገ ገባኝና "ወታደርነት?" ብዬ እርግጠኛ ባልሆነ አነጋገር ጥያቄውን በጥያቄና በመልስ መካከል ተውኩት።

"ለምን ይመስለሃል?" አለኝ ረጋ ብሎ።

"ምንአልባት የብዙ ሰው ሕይወት በጦር መሪው ሃላፊነት ስር ስላለ፣ የሚወስደው እርምጃ፣ በሥሩ ያሉትን ብቻ ሳይሆን የራሱንም ሕይወት ሊያጠፋ ስለሚችል ይሆናል..." እያልኩ የመሰለኝን ዘረዘርኩ። ስጨርስ አባቴም ረጋ ብሎ እንደሚከተለው አብራራልኝ።

"ከሁሉም ኘሮፌሽን የጦር አዛዥነት ከባድ ነው። ለምን መሰለህ የጦር አዛዥ እንደ ዶክተር፣ ወይም ጠበቃ፣ወይም መሐንዲስ አንድ መሥመር ተከትሎ ወይም የተማረውን እና የሚያውቀን ብቻ ተከትሎ መሥራት አይችልም። የጦር አዛዥ የሚያውቀውንና ሊሆን የሚችሉትን ሁሉ አሰላስሎ እቋም መውሰድ አለበት። የሱ ችሎታ የጠላት ጦር አዛዥ ጭንቃላት ውስጥ ያለውን ሃሳብ ማወቅ ላይ ነው። ያን ካወቀ ያሸንፋል። ከተሳሳተ የብዙ ሰው





ሕይወት ሊጠፋ ይችላል። ስለዚህ ጦርነቱ የሚደረገው በሁለቱ አዛዦች ጭንቅላት መካከል ነው። ጠላትህ ምን ለማድረግ እንዳሰበና እንዴት እንዲያደርገው መገመት ከቻልክ ድል የማድረግ ዕድልህ በጣም ሰፊ ይሆናል ማለት ነው።" አለኝ ከዚህ በፊት አስቤበት የማላውቀው ጽንስ ሃሳብ የነበረ ለብዙ ጊዜ አወጥቼ አወረድኩት። የአባቴ ኃላፊነት ከመቼውም ጊዜ ከብዶ ተሰማኝ።

የምጽዋ ዋና መንገድ ላይ ወጥተናል ከጎንና ከጎን ያሉት መደዳ ቤቶች ተቀማጥ ከመንገዱ ስፋት በስተቀር በምሥራቅ ኢትዮጵያ ያሉትን ትናንሽ ከተሞች ይመስላል። ጥምዝ ጨቤ ያገለደሙ አፋሮችና በቀጭን ገመድ የሚጎትቷቸውን ግመሎች አየሁ።ይህ ብዙ ጊዜ ወደ ሐረር ስሄድ ካየሁት ጋር ስለተመሳሰለ ከዚህ በፊት ምጽዋን የማውቃት መሰለኝ።

ሆኖም ምጽዋን በደንብ ለማየት አልቻልኩም። የምንጓዘው በፍጥነት ነው። ትንሽ ተጉዘን ከአንድ ሆቴል መሰል ግቢ ገባን። በቅጥር ግቢው ብዙ ወታደሮች ከነሙሉ ትጥቃቸው እና መትረየሳቸው ቆመዋል። ጥቂት መኮንኖችም እጅብ ብለው ቆመው የመኪናችንን መቆም ይጠብቃሉ። አባቴ ከመኪና ወርዶ ሠላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ሁሉም ወደ አንድ ክፍል ገብተው በሩን ዘጉት። እኔ ግቢው ውስጥ ዞር ዞር ማለት ጀመርኩ። ግቢው በፊት ሆቴል የነበረና አሁን ወደ ጦር ሠፈር የተለወጠ መሆኑን ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም። በግቢው መሃል ትንሽ ክብ የሆነች ድሮ የአበባ ቦታ የነበረች የምትመስል ቦታ አለች። ቤቶቹ እንደ ሆቴል ቤት መደዳ ክፍሎች ናቸው። ወዲያው አንድ ከዚህ በፊት የማውቀው ፊት አየሁና የት

እንደማውቀው ማሰብ ጀመርኩ። እንደገና ትኩር ብዬ አየሁት። ሰውየው የሻምበል ማዕረግ ለብሷል። ትዝ አለኝ። ሐረር ከተማ ነበር የማውቀው። ሐረር መኮንኖች ክበብ ያን ጊዜ ም/መ/አለቃ ነበር። አባቴ የምሥራቅ ዕዝ (አንደኛ አብዮታዊ ሠራዊት በመባል የሚታወቀው) አዛዥ በነበረበት ጊዜ ለእረፍት እየሄድኩ ሐረር ስቆይ ጊዜዬን የማጠፋው በጦር ሠፈሮችና መኮንኖች ክበብ ነበር። መኮንኖች ክበብ እየሄድኩ የጠረጴዛ ቴኒስ ከመኮንኖች ጋር እጫወት ነበር። እና ከዚህ ሻምበል ጋርም ብዙ ጊዜ ተጫውተናል። ወደሱ ሳመራ ወዲያው አስታወሰኝና በመገረም እየተመለከተኝ እቅፎ ሰላምታ ሰጠኝ።

“አንቺ ደህና ነሽ?” አለኝ በማቀላመጥ።
“ደህና ነኝ። ታዲያስ እንደምነህ?” አልኩት የማውቀው ሰው ምጽዋ ውስጥ በማግኘቴ እየተደሰትኩ።
“አለሁ፣ ይኸው እዚህ ደግሞ መጥተናል” አለኝ። ልጅ ቢሆንም ሽበት ጣል ጣል አድርጎበታል። ፊቱም በረሃ ያጠቀረው ይመስላል።
“ነይ ቁጭ በይ!” ብሎ ባንዲራ ከሚውለበለብበት ትንሽ ክብ ዙሪያ ላይ ካለው ደረጃ ላይ አረፍ አለ። ሠላምታ ከጨረስን በኋላ “ሙቀቱ ታዲያ እንዴት ነው?” አልኩት።
“ምን እባክህ ገና ከመድረሳችን እስራ ሁለት ሰዎች በሙቀት ምክንያት ሞቱብን። ሙቀቱን አልቻሉትም” አለኝ። አሁንም ፈገግ እንዳለ በጣም ደነገጥኩ እኔንም ሙቀት የሚገድለኝ መሰለኝ። እሱ ከሞት ጋር የሚኖር





ይመስላል- ምንም አልመሰለውም። ምናልባትም አብሮ ይኖራል ማለት ይቻል ይሆናል። ከሌሎቻችን በበለጠ ተቀራርቦ።
"የውሃ እጥረት ደግሞ አለ። በቂ ምግብና ውሃ ካላገኘህ ይሄ ሙቀት ይገልሀል” አለኝ።
“ለመሆኑ አንተ የት ክፍል ነህ?” አልኩት
"ከ.ታንከኛው ብርጌድ ነኝ!ከሐረር ነው ብርጌዱን ይዘን የመጣነው” አለኝ።
"ኦ አባቴ ትርኢት ስለሚያሳዩ እንሄዳለን ብሎኛል” አልኩት።
"እሦ ከሰዓት በኋላ ነው ትርኢቱ። በቃ አብረሽ ትዞሪያለሽ” አለና እቀፍ አደረገኝ፣ የማያቋርጥ ፈገግታው ሳያቆም።
“እሦ ቤት ከመቀመጥ ይሻላል። ታዲያ ምንድነው የምትሠራው ታንከኛ ነህ?” አልኩ ለጥናት የሄድኩ ዓይነት ሁሉንም ለማወቅ ፈልጌ ነበር።
“የብርጌዱ የፖለቲካ ኃላፊ ነኝ” አለኝ። ከዚያ በፊት የፖለቲካ መምሪያ እባል ወይም ካድሬ መሆኑን አላውቅም ነበር።
“በፊትም ፖለቲካ መምሪያ ነበር እንዴ የምትሠራው?”
“አሁን ነው የተዛወርኩት ግን ታንከኛ ነበርኩ”
“የብርጌድ አዛዡ ማነው?”
“ሻለቃው ነው” አለኝ ቀደም ብሎ ቆመው ከነበሩት መኮንኖች መሀል ዥንጉርጉር ሬንጀር ልብስ ለብሶ የነበረውን ሻለቃ እንደሚጠቁም ዓይነት፣ ሻለቃው ቆሞ የነበረበትን ቦታ በጣቱ አመልክቶ።
“ሐረር ነበር አይደል እሱም? አረፍ ሰውዬ ነው” አልኩት የሻለቃውን አለባበስና ወታደራዊ አቋም በማድነቅ። ስሙ ሻለቃ አርጋው ባንተይለኩ ይባላል። አስታወስኩት።

"ሐረር አብረን ነበርን። እዚህም አብረን መጥተናል" አለ። ከአነጋገሩ ሻለቃውን ይህን ያህል የሚወደው አይመልስም።
"እሱ ነው ማለት ነው አለቃህ?" አልኩት ለማረጋገጥ።
"የብርጌዱ አዛዥ እሱ ነው። ግን በኔ ሥራ አይገባም። እኔም ለክፍለ ጦሩ የፖለቲካ ኃላፊ እጽፋለሁ፤ እሱም ለአዛዡ ይጽፋል" አለኝ። ይሄ እንግዲህ በጦሩ መሀል የተፈጠረው መከፋፈል በሥራ ላይ ሲታይ ነው። ነገሩን ወደ ጎን ለመተው ፈለግኩና "ታዲያ እንዴት ነው የጦሩ ሁኔታ?" አልኩት
"እስኪ እንግዲህ አሁን እነ ጄ/ደምሴ መጥተዋል፤ ትንሽ የጦሩን ሞራል ይገነቡታል። አሁን ትንሽ ድል እየቀመሰ ነው። እየሀ ወታደሩ አለቆች እንደዚህ እየዞሩ ካላነጋገሩት ሞራሉ እየሞተ ነው የሚሄደው። አባትህን ደግሞ ጦሩ ይወዳቸዋል። የሚያውቁት ጦር ነው። ችሎታም አላቸው" አለኝ።
ቀጠለና "ጦሩ ሰሜን ሲመጣ ለሞት የመጣ ይመስለዋል። ለምሳሌ ከሱማሌ ጋር ተዋጋ ብትለው እንደሚያሸንፍ እርግጠኛ ሆኖ ነው የሚሄደው። እዚህ ሲመጣ ግን  ለሞት የመጣ ነው የሚመስለው። ትንሽ ድል ሲያሸት ደግሞ ሞራሉ ይገነባል። አሁን ከአፋቤት በኋላ የሞተው ሞራሉ በከረኑ ድል እየተጠናከረ ነው። አሁን ደግሞ ሰሞኑን በምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ትልቅ ድል እንጠብቃለን" አለኝና "እየወጡ ነው ብሎ" ተነሳ። እኔም አብሬ ተነሳሁ። ከመደዳ ክፍሎች የአንዱ በር ተከፍቶ ብዙ መኮንኖች በየተራ መውጣት ጀመሩ።





ጄ/ደምሴ ከፊት ፊት ወደ መኪናው ሲያመራ ስላየን "እ ደህና ነህ ?" አለው ሻምበሉን። ሻምበሉም አባቴን የወታደራዊ ሠላምታ ሰጥቶ ሸኘው። ትንሽ አነጋገረውና "ታዲያስ እንሂዳ!" እያለ መኪና ውስጥ ገባ። እኛም እየዘለልን ገባን። ሻምበሉን በመስኮት የእጅ ሠላምታ ሰጥቼ ተለየሁት። ከዚያን ቀን በኋላ አላገኘሁትም።

ሰዓቱ ወደ ስድስት ሰዓት ገደማ ደርሷል። በጂፑ መስተዋት ወደ ውጭ አሥመራ ዙሪያ ገባውን በፀጥታ እየቃኘሁ ተጓዝኩ። ወደ ባሕር ኃይል ቅጥር ግቢ እየተመለስን ነበር። በመንገዳችን ላይ አንድ የተጋጨ የወታደር መኪና አየንና ቆምን። ወዲያውኑ ከኋላ ተቀምጦ የነበረው የወታደር ፖሊስ ከመኪናው ተስፈንጥሮ ወረደና ቆመ፡
"ጥራው እዚያ የቆመውን!" አለ ጄ/ደምሴ በመስታወቱ ውጭ የቆሙትን እየተመለከተ። ሰውየው ከመጠራቱ በፊት ሮጥ ብሎ መጣ።
"ምንድነው የሆናችሁት?" አለው።
"ትንሽ ግጭት ነው የተጎዳ ሰው የለም" አለ በተጠንቀቅ ቆሞ።
"እሺ. ደህና እንሂድ!" አለ።
አጃቢው ወታደር ፖሊስ ከመቼውም እንደ ተሳፈረ ግራ ገባኝ። መንገድ ከጀመርን በኋላ ወደኋላ ዞር ብዬ ሳየው ነው ተመልሶ መኪና ውስጥ መግባቱ የታወቀኝ።

ባሕር ሃይል ስንደርስ በር ላይ ማንነታችንን አሳውቀን ገባን። በሄሊኮፕተር ያረፍንበትን ሜዳ አልፈን በግቢው ትንሽ ተጓዝንና አንድ ለዓይን በጣም ማራኪ ከሆነ ስፍራ ቆምን።

ለምሳ ነበር የተመለስነው። ቤቱ የተሰራው ልክ ከቀይ ባህር ዳርቻ ላይ ስለነበር የባህሩ ሞገድ ከብረቱ ግድግዳ ጋር እየተንደረደረ መጥቶ ሲጋጭ የሚፈናጠቁት የቀይ ባህር ውሃ ፍንጣቂዎች በገላ ላይ ሲያርፉ ልዩ ስሜት ይሰጣሉ። ተሀድሶ ዓይነት። ማራኪ ቦታ ነው። የባህሩ አረንጓዲያማ ሰማያዊ ቀለም፣ ከፀሐዩ ጨረር ጋር እያብረቀረቀ ሲታይ አንድ ዓይነት የደስታ ስሜት ይሰጣል። ቤቱ ባለ ትልቅ በረንዳ ሆኖ በረንዳው ራሱ ሁለት ክፍል አለው። አንደኛው በረንዳ ላይ አንድ ትልቅ ጠረጴዛ ከብዙ ወንበሮች ጋር ሆኖ ሰማያዊ ክፈፍ ያለው የጠረጴዛ ጨርቅ ለብሶ ይታያል። ከሱ በደረጃ ወረድ ብሎ ደግሞ የባህሩ ሞገድ የሚገርፈው ዝቅ ያለ በረንዳ አለ። ይሀኛው ዙሪያውን ክብ ሆኖ የተሠራ መናፈሻ ነው። ዙሪያውን ከግንቡ ጋር ተያይዞ የተሠራ መቀመጫ አለው። መቀመጫው ነጭ ጨርቅ ለብሶ ሰማያዊ መከዳዎች ተደርድረውበት ለቦታው ልዩ ድምቀት ሰጥተውታል። በእውነት በኢትዮጵያ ካየኋቸው ዓይን የሚማርኩ ቦታዎች አንዱ ነው። ቦታው ራሱ ከቀይ ባህር ሞገድ ጋር ባንድ ላይ ልዩ ጣዕመ ሙዚቃ ያሰማል። ትንሽ ቆሜ አዳመጥኩት። የቀይ ባህርን ፍንጣቂዎች በደስታ እየተቀበልኩ።

የባህር ኃይል አዛዥ የነበሩት ሪር አድሚራል ተስፋዬ ብርሃኑ ወደ ምፅዋ መጥተው ኖሮ ምሳ የጋበዙን እሳቸው መሆናቸውን ተረዳሁ። እሳቸው ወዲያው መጥተው የሞቀ ሠላምታ ሰጡን። ክቧ መናፈሻ ላይ ተቀምጠው





ከአባቴ ጋር ትንሽ አወሩና "ምሳ እንብላ" ብለው ተነሱ፣ ምሳ ቀርቦ ነበር። ቀይ ባህርን እያየን ተመገብን። እዚያ ተቀምጦ ሙሉ ቀን ሲበሉ መዋል ይጮኻል - የባህሩን ሞገድ እየሰሙ።

በምሳው ሥነ ሥርዓት ላይ የባህር ኃይል መኮንኖችና ያካባቢው ጦር አዛዦችም ተገኝተዋል። ስለአንዳንድ ሁኔታዎች እየተወያዩ ምሳችንን በላን።

ነጭ ጨርቅ የለበሰው ጠረጴዛ ላይ የተለያዩ የአበሻና የፈረንጅ ምግብ የያዙ ሳህኖች ተደርድረዋል። ከአንዱ ወደ ሌላው በየተራ እየተዘዋወረ ሁሉም ከየዓይነቱ ያወጣል። በቀይ ባሕር ወደ ክቧ መናፈሻ የሚነፍሰው ነፋስ ሙቀቱን ቀንሶልናል። አሳላፊዎች እየመጡ የጎደለውን ይሞላሉ። የተቀመጠው ተፈጥሮን እያደነቀ ይመገባል።

ከምሳ በኋላ እንደገና ወደ ክቧ መናፈሻ ተመልሰን ለአስራ አምስት ደቂቃ ያህል እንደተቀመጥን "በሉ እንግዲህ ወደ ታንክ ትርኢት እንሂድ" ብሎ ተነሳ ጀ/ደምሴ። ተነስተን መኪኖቻችን ላይ ተሳፈርንና የባሕር ሃይልን ቅጥር ግቢ ለቀን ጉዞአችንን ወደ ምፅዋ በረሃ ቀጠልን። ከከተማዋ ራቅ ብለን መጓዝ ጀምረናል። መንገዳችን ላይ የታንክና የብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች በተሠራላቸው የተቆፈረ ምሽግ ውስጥ፣ እንደ ሐረግ በተተጣጠለ ጨርቅ ተሸፍነው ቆመው ይታያሉ። በቅርቡ ሻዕቢያ ምፅዋን ለማጥቃት ሊሞክር ይችላል በማለት የተደረገ ዝግጅት ነበር። ቢ.ኤም21 የተባሉትና የሮኬት መተኮሻ የተሸከሙ ከባድ መኪኖች፣ (ወታደሮች "ማሪያም" እያሉ ይጠሯቸዋል- 21 የቅድስት ማሪያም የምትውልበት ቀን ስለሆነ)። መድፎችም እንዲሁ ለሩቅ ተመልካች ተሰውረው ተቀምጠዋል።

አንድ አርባ አምስት ደቂቃ ያህል ተጉዘን አንድ መለስተኛ የጦር ሰፈር ደረስን። የተለመደው አቀባበል ተደረገልንና አሁንም የተቀበሉን መኮንኖችና አባቴ ለመነጋገር ወደ አንድ ክፍል ገቡ። እኔም ውጭ መዘዋወር ጀመርኩ።

አየሩ በጣም ይሞቅ ነበር። ዞር ዞር እያልኩ ስቃኝ አልጋ የተደረደረባቸው ክፍሎች አየሁ። የወታደሮች መኖሪያ ናቸው። የወታደሮቹን ክፍል ገባ እያልኩ መቃኘት ጀመርኩ። ስድስት ያህል የሚሆኑ ፍራሾች በአንድ አነስተኛ ክፍል ተነጥፈዋል። በመካከላቸው ለእግር ማቆሚያ ያህል ቦታ የለም። ይሄ የመኮንኖች ክፍል መሆን አለበት ብዬ አሰብኩ። ሌላው ክፍል እህል በያዙ ጆንያዎች ተሞልቷል። በመቃኘት ላይ ሳለሁ ድንገት አንድ ሻምበል "ና ማነህ!" ብሎ ጠራኝ። እኔም ለምን እንደሚፈልገኝ ግራ ገብቶኝ ወደሱ ስጠጋ በአኳኋኔ ተገርሞ፣
"ለሸርሸር የመጣህ መሰለህ እንዴ? በል ቶሎ የደንብ ልብስህን ልበስና ና!" አለኝና ቀጥሎ "ደግሞ ገና ትቀጣለህ!" አለኝ።
ግራ ገብቶኝ "እይ እኔ ከዚህ አይደለሁም ከአስመራ ነው የመጣሁት?" አልኩት በመገረም ዓይኑን እያየሁ።
"ኦ አሁን ነው የመጣኸው፣ የት ክፍል ነህ? ዩኒፎርም የለህም እንዴ ታዲያ?" አለኝ እሱም ከኔ በባሰ ተገርሞ።
"አይ ወታደር አይደለሁም፣ እንዲሁ ነው የመጣሁት" አልኩት። በመልሴ የበለጠ ተገርሞ ይመለከተኛል። ማስረዳት ልጀምር ስል የአባቴ አጃቢ ጠጋ ብሎ "ከኛ ጋር ነው ጌታዬ የአዛዡ ልጅ ነው!" ብሎ ገላገለኝ።





"ኦ! ገባኝ" ብሎ ፈገግ አለና፣ "እንዳንተ ዓይነት እዚህ ከብሔራዊ ውትድርና የመጡ አሉ። የሲቪል ልብሳቸውን እየለበሱ የሚዞሩ፣ ከነሱ አንዱ መስለኸኝ ነው።" ብሎ ወደ አንዱ ክፍል ገባ።

ስብሰባውን እንደ ጨረሱ የታንክ ልምምዱን ውጤት ለማየት ጉዞ ጀመርን። አንድ ወጣ ገባ ተራራማ ቦታ ላይ ስንደርስ መኪኖቹ ቆሙና ሁላችንም ወረድን። ወዲያው አምስት ታንኮች ድንገት መብራታቸውን አብርተው ከአንዱ ረባዳ ቦታ ብቅ አሉ።
"አሁን በስተቀኝ ያሉት ሁለት ታንኮች በፍጥነት እየተጓዙ ያንን ኢላማ ይመቱታሉ" አለ ኮሎኔል ውጋየሁ ወደ ጄ/ደምሴ ጆሮ ጠጋ ብሎ።

ታንኮች ምልክት ሲሰጣቸው በፍጥነት አቧራውን እያቧነኑ ዳገቱን ቀያያዙት። ድንገት ሳላስበው አንደኛው ታንክ መትረየሱን አርከፈከፈው።
ዷ! ዷ! ዷ!
የመጀመሪያውን የመትረየስ ተኩስ ስሰማ በዱላ አናቱን እንደተመታ ሰው በድንጋጤ ጭንቅላቴን ያዝኩ። አጠገቤ የበሩት ሁሉ ግድም ሳይሰጣቸው የታንኮቹን እንቅስቃሴ በጥሞና ይመለከታሉ። ቀስ ብዬ እጄን ከአናቴ አነሳሁ። ሁኔታዬን ያየ ሰው እንዳለ ለማጣራት ዞር ብዬ አየሁ። ማንም የለም። ከዚያ በኋላ የነበሩት ተኩሶች አላስደነገጡኝም። የታንኮቹ ሰንሰለቶች እያነሱ የሚከምሩብን አቧራ ሰውነታችንን ሸፍኖታል። ገሚሶቹ የተመደበላቸውን ዒላማ በፍጥነት እየተጓዙ ሲመቱ የቀሩት እንደልብ መዘዋወር አላስቻገራቸውም። ይተራመሳሉ።

"ወጋየሁ እነዚህ ሰዎች አሁንም ይቀራቸዋል። የአንድ ወር ጊዜ እጨምርልሃለሁ። ከዚያ በላይ ግን ጊዜ የለንም። ሰሞኑን የምናደርገው እንቅስቃሴ ለወደፊት ጠቅላላ እንቅስቃሴአችን በጣም ወሳኝ ነው። ስለዚህ ዝግጁ ሆናችሁ መጠበቅ አለባችሁ። ከአሁን በኋላ በማንኛውም ጊዜ ለጦርነት ልትላኩ ትችላላችሁ። ግን ሆኖም እዚህ እስካላችሁ ድረስ ልምምዱን ቀጥሉ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ወሳኝ ፍልሚያ እናደርጋለን። እና በእናንተ በኩል የሚመጣ ጥቃት ሊኖር ስለሚችል ዝግጁ ሆነህ ጠብቅ። አሁን የመትረየሶችን ቦታ ማየት እፈልጋለሁ ወደዚያ እንሂድ!" ብሎ ወደ መኪናዎቹ አመራ ጀ/ደምሴ።

መንገዳችን ላይ የአባቴን አቧራ የለበሱ እጆች እየሁና የራሴን ተመለከትኩ። ሁለመናዬ አቧራ ነው። ከጎኔ የተቀመጠውም እንደዛው እንዲሁ አቧራ ለብሷል። መትረየሶቹ የተጠመዱበት ቦታ ደርሰን ገና መውረዳችን ነው።

"እነዚህ ሁለት ከፍት ቦታዎች ላይ የተጠመዱ አሉ?" ብሎ ጠየቀ ጀ/ደምሴ።

"የለም ጌታዬ እዚህና እዚያ ነው የጠመድነው!" አሉ ኮሎኔሉ ቦታዎቹን በእጃቸው እያመለከቱ።

"ምነው? ምነው? ተዘጋጅተናል ማለት እንዲህ ነው እንዴ?" አለ ኮሎኔሉን ዞሮ ካየ በኋላ።

"በሉ አሁን እነዚህ ሁለት ቦታዎች ላይ ከባድ መትረየሶች እንዲጠመዱ አድርግ። ያኛውን አንሳና ወዲያኛውን ከዚህኛው ከፍተኛ ቦታዎች ላይ





አድርግ። የቀረው እንዳለ መሆን ይችላል።" አለው ቅሬታ ፊቱ ላይ እየታየ።

"እየሀ ሁለት መትረየስ ጎን ለጎን አስቀምጠህ ሰፊ ወረዳ መሸፈን አትችልም። የፊት ለፊቱን ብቻ ነው የምታገኘው ከጎን የሚመጣው ያመልጥሃል። አራርቀህ ሁለት ከፍተኛ ቦታዎች ላይ ያስቀመጥክ እንደሆነ ሁለቱም በአርባ አምስት ዲግሪ በሚተኩሱበት ጊዜ በመሃል ያለውን ብቻ ሳይሆን በጎን የሚመጣውን ጭምር አጨዳ ተኩስ ማድረግ ትችላለህ" አለው፤ ሁለት እጁን ከደረቱ ፊት ለፊት እያስተሳለፈ የሁለቱን መትረየሶች የተኩስ አሩምታ አቅጣጫ በመግለፅ።

ኮሌኔሉ "እሺ ጌታዬ!" ከማለት ሌላ አልተናገሩም።

"በሉ እንግዲህ ለማንኛውም ዝግጁ ሆናችሁ ጠብቁ። የሚያስፈልግ ነገር ካለ ብዙ ውጥረት ውስጥ ሳንገባ አሁኑኑ አጠናቁ" በማለት ሰውየውን ጨበጣቸውና እጁን ሳይመልስ ለጥቂት ሰኮንዶች "አይዞህ አጠገብህ ነኝ" በሚል አከዋኋን ተመለከታቸው።

"ብዙ ሥራ ይጠብቀናል። ብዙ ብዙ..." እያለ ወደ መኪናቹ አመራ።

"ወደ ክ/ጦሩ እንሂድ። እዚህ ጨርሰናል!" አለ መኪና ውስጥ ከገባን በኋላ። በቅርቡ ከሐረር የምፅዋን መከላከያ ጦር ለማጠናከር የመጣ ጦር ነበር። ጀ/ደምሴ ሐረር የምስራቅ የነበረው ጦር አዛዥ በነበረበት ጊዜ እዚያው የነበረ ጦር ስለነበረ በደንብ ያውቀዋል። ሻዕቢያ ምፅዋን ለማጥቃት እንደሚዘጋጅ መረጃ ደርሶ ስለነበረ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነበር። ወደዚሁ ክ/ጦር አመራን።

አንድ የጦር ሰፈር የሚመስል ቦታ ስንደርስ ቆምን። አንድ ኮሎኔል ይጠብቁን ነበር። ኮሎኔል ረጋሳ ይባላሉ። አጠር ብለው ጠቆር ያሉና ትንሽ ቦርጭ የሚታይባቸው ኮሎኔል ናቸው። የታጠቁት የአሜሪካ 45 ሽጉጥ ከርዝመቱ የተነሳ መሬት የሚነካ ይመስላል። ሽሮ መልክ ያለው ከኪዩባ የመጣ የወታደር የደምብ ልብስ ነው የለበሱት። ያደረጉት ቆብም መልኩና ጨርቁ የልብሱ ዓይነት ሆኖ የኪሻ ኮፍያ ዓይነት ዙሪያውን ፀሐይ መከላከያ ከፈፍ አለው። ኬሎኔሉ እኛ የነበርንበት ጂፕ ውስጥ ገብተው ወደ አንድ ቦታ ይመሩን ጀመር። አባቴ ከ ኮ/ረጋሣ ጋር አስተዋወቀኝ።

መኪና ውስጥ ገብተው ትንሽ እንደሄድን ጀ/ደምሴ ዞር አለና "ረጋሣ ብሎ" ኮለኔሉን እያየ ፈገግ አለ። ፈገግ ሲል ፍንጭቱ ፈገግታውን ያሳምረዋል። ኮ/ረጋሣም "አቤት ጌታዬ!" ብለው ፈገግ አሉ። ከዚያ የቀጠለ ንግግር ግን አልነበረም። "እዚህ ደግሞ ተገናኘን?" የሚባባሉ ይመስላል።

በጦር አመራር ችሎታቸው አባቴ ከሚተማመንባቸው መኮንኖች ውስጥ አንዱ ነበሩ። "ረጋሣ ጀግና ነው!" ይል ነበር። ፈገግታቸው እንደወተት የነጡትን ጥርሶቻቸውን በጥቁር ፊታቸው ላይ አድምቆ ያሳያል። መልካቸው የደግ ሰው መልክ ነው። (ኮ/ረጋሳ እንደ ብዙ ጓደኞቻቸው ከአንድ ዓመት በኋላ በውጊያ ላይ ሕይወታቸው አልፏል። በሰሜን ኢትዮጵያ በረሃ ካረፉት ጀግና ኢትዮጵያውያን አንዱ ነበሩ።)

ዋናው ጦር ሠፈር በወታደር ተሞልቶ ከፍተኛ ግርግር ይታይበት ነበር። ክ/ጦሩ ገና መድረሱ ስለነበር ወታደሮቹ ዕቃ በማውረድና ማረፍያ ቦታቸውን በማስተካከል ላይ ነበሩ። ከአንድ ነፋሻማ ጥላ ስር ወንበሮች ተደርድረው





ይጠብቁን ስለነበር እዚያ ተቀመጥን። የጦር መኮንኖችም አንድ በአንድ ጀ/ደምሴን እያነጋገሩ ተቀመጡ። ስለ ጠቅላላ ሁኔታዎች እየተወያዩ ሳለ ጥቂት ወታደሮች በትላላቅ ትሪዎች የሃብሃብ ፍሬ (ወተር ሜሎን) ይዘው መጥተው ለሁሉም አደሉ። ወዲያው ሻይ በጋቢጣ (የወታደር የብረት ኩባያ) ቀረበልን። በልጅነት ጦር ሰፈር እየሄድኩ ሻይ በጋቢጣ መጠጣት እወድ ስለነበር ሻይ ሲመጣ የቀኑ ድካም ለቀቀኝ። ሀሳቤን በሻይ እያወራረድኩ አባቴ ሰሞኑን ይደረጋል ስላለው ጦርነት ማሰብ ጀመርኩ። የሰሞኑ ጦርነት ወሳኝነት እምኑ ላይ እንደሆነ እያወጣሁ አወረድኩ። በምን ዓይነት አብሬው መዘሩን እንደምቀጥል እቅዱን እያወጣሁ የወታደሮቹን ትርምስ እመለከታለሁ። ጊዜው እየመሸ በመሄዱ አየሩ ትንሽ መቀዝቀዝ ጀምሮ ነበር። አባቴና ኮ/ረጋሣ ጎን ለጎን ተቀምጠው በለሆሳስ ያወራሉ።

ወታደሮች አሁንም ከግራ ወደ ቀኝ ይጣደፋሉ። እቃቸውን ከቀሙት መኪናዎች እያወረዱ በየድንኳኑና ዘርዘር ብለው ከተሰሩት ቤቶች ያጉራሉ። ስለቶች በየቦታው ትዕዛዝ ጬክ እያሉ አንዳንዴም እየተቆጡ ይሰጣሉ። የዛፎች እንቅስቃሴ ከወታደሮቹ ትርምስ ጋር ለመወዳደር ይመስል እያየለ መጣ። የቀኑ ሙቀት ጠፍቶ የጊዜውን አስፈሪነት የሚዘክር ይመስል ቅዝቃዜ ወረረን። ትንሽም አልቆየን ጀ/ደምሴ ተነስቶ ቆመና "ጥሩ ነው አንግዲህ ፈጋሣ ቶሎ ቶሎ ብላችሁ የሚያስፈልገውን ሁሉ አድርጉና ዝግጁ ሆናችሁ ጠብቁ። ጊዜ የለንም። የሚያስፈልግህ ነገር ካለ ጠይቀኝ!" ብሎ ወደ መኪናቹ አመራ። ሁላችንም ተከተልን። መኪኖቹ ጋር ስንደርስ እንደገና ወደ ኮ/ረጋሳ ዞር በማለት "ረጋሣ!" ብሎ ፈገግ አለ ጀ/ደምሴ። ትንሽ ትኩር ብሎ ካየው በኋላ በወንድማዊ ስሜት ጨበጠውና መኪና ውስጥ ገባ።

ዋዞቹ ባላቸው ፍጥነት እየተንደረደሩ ወደ ምፅዋ ማምራት ጀምረዋል። ምፅዋ ባሕር ኃይል ክፍል ስንደርስ መሸቶ ነበር። ዋናውን በር አልፈን ማረፊያ ቤታችን እንደ ደረስን የባሕር ኃይል አዛዥ አድሚራል ተስፋዬ ለራት እንደሚጠብቁን ተነገረን። መልዕክቱን ተቀበልንና አቧራችንን አራግፈን ለራት ለመዘጋጀት ወደ ማረፊያ ክፈላችን አመራን። ቤት ውስጥ እንደገባሁ ፊት ለፊት ያለው መስተዋት ውስጥ ራሴን ስመለከት አስደነገጠኝ። ሰውነቴ ሁሉ ቅንድቦቼ ሳይቀሩ በአቧራ ተሸፍነው የወፍጮ ቤት ሠራተኛ አስመሰለውኛል። እኔስ ገብቼ ልተጣጠብ ነው። እዚህ ዘጠኝና አስር ዓመት ከበረሃ ሳይወጡ የሚከርሙት ... ወግኖቻችን እያወጣሁና እያወረድኩ ወደ መታጠቢያ ቤት ገባሁ።

እራት የተዘጋጀው በዚያ ህይወት በምታድሰዋ በረንዳ ላይ ነበር። በማታማ ገነት እንጂ በምድር ላይ ያለች ቦታ አትመስልም። ንፋሱ ቀይ ባሕርን ፀጥታ ነፍጎ ያተራምሰዋል፤ ባሕሩም የንዴት ዓይነት እየተንደረደረ በሞገድ የበረንዳውን ግድግዳ ሲመታ አሁንም የውሃ ፍንጣቂዎች ፊታችን ላይ መደነሱን ቀጠሉ። ነፍሴም ከሰውነቴ ወጥታ ከፍንጣቂዎቹ ጋር በስሜት የምትደንስ መሰለኝ፤ የቀኑ ውዝግብ ከአእምሮዬ ጠፍቶ ደስ በሚል ስሜት ብቻ ተሞላሁ። የባሕር ኃይል መኮንኖችና የጦር ከፍተኛ ሹማምንት በበረንዳዋ ግማሽ ክብ ዙሪያ ተቀምጠዋል። ሁሉም ሪር አድሚራል ተስፋዬና ጀ/ደምሴ የሚያወሩትን በጥሞና ያዳምጣሉ።

"ዝግጅቱ እንዴት ነው በናንተ በኩል?" አሉ ጀ/ደምሴ ዞር ብለው ሪር አድሚራል ተስፋዬን እየተመለከቱ።





"እጶዚቹሀ እኛ ዝግጁ ነን። አሁን የሚቀረን ከናንተ ኃይሎች ጋር ቀነጋግረን ሁኔታዎችን ማስተባበር ብቻ ነው።" አሉ ሪር አድሚራል ቀስፋዬ። በጥቅሉ ስለነበረው ዝግጅት ከተወያዩ በኋላ ከሁለት ደረጃዎች ከፍ ብሎ ከነበረው ጠረጴዛ ላይ ተቀምጠን እራት ተመገብን። በተጫዋችነት የቀውቁት የምፅዋ የባሕር ኃይል አዛዥ፤ ኮሞደር ጌታቸው እራት ላይ እየቀለዱ የተሰበሰበውን ሁሉ ያስቁ ነበር። አጠር ያሉ ጠቅላላ አቋማቸው የወታደር የማይመስል፤ ሕይወትን በቀልድ የሚያደንቁ ግድ የለሽ መሳይ ሃሣው። ወፈር ያሉ ሲሆኑ የደፈረሱት ዓይኖቻቸው በጥቁር ፊታቸው ላይ ደምቀው ይታያሉ። የማያቋርጠው ፈገግታቸው ያለማቋረጥ ከሚያጨሱት ሲጋራ ጋር በአንድ ላይ ተደምሮ ተመልካችን የማያስለች ገፅታ ሰጠቶአቸዋል። በምስራብት መ/ቤት የአስመራ ራዲዮ ሠራተኛ የነበረችው ባልደረባዬ አባት መሆናቸውን ስለሰማሁ ስለልጃቸው ጤንነትና ሥራ ሁኔታ ዛለጽኩላቸው። በጣም ስላ ተግባባኋቸው ከራት በኋላ ስንሰነባባት የመ/ቤታችን ዓርማ ያለበትን "የስዊዝ አርሚ ኦፊሰርስ ናይፍ" (ውስጧ ሰንጢ፤ መቀስ፤ መከፈቻ...ወዘተ ያላት) ለማስታወሻነት በስጦታ ሰጠኋቸው። (ኮሞዶር ጌታቸው ወደ አሜሪካ ከመጣሁ በኋላ እዚያው ምፅዋ በሻዕቢያ ሲያዝ ዉጊያ ላይ ማረፋቸውን ሰማሁ)። መኮንኖቹ ሁሉ ተሰናብተው፤ ከሄዱ በኋላ ጀ/ደምሴና ሪር አድሚራል ተስፋዬ በቆይታ ለመነጋገር ሪር አድሚራል ተስፋዬ መኝታ ቤት ሲገቡ እኔም ከዚያች የበረንዳ ጫፍ ላይ ቀሚ ፍንጣቂዎችን ስቀበል ከቆየሁ በኋላ ወደ መኝታ ቤቴ ገብቼ ተጋደምኩ።

-4-

ጥዋት ስነሳ በቤቱ ውስጥ ሰው አልነበረም። በኔ ቤት ማልጄ መነሳቴ ነበር። ነገር ግን በወታደር ቤት ከጥዋቱ ሁለት ሰዓት ማለት ወደ ረፋዱ ገደማ ነው። ልብሴን ለብሼ ስወጣ የአባቴን አጃቢ የአስር ዓለቃ ጌታቸውን ውጭ ከባሕር ዳሩ አካባቢ ቆሞ አየሁት። ወደሱ ተጠግቼ ባሕሩን እያየን ስናወራ ትንሽ ከቆየን በኋላ ልብሴን አውልቄ ለመዋኘት ገባሁ። ባሕሩ ከውስጥ አረንጓዴ እንጂ ቀይ አይደለም። ቀይ ባሕር የተባለው ከአውሮፕላን ወደታች ሲታይ ደም የሚመስል ቀይ ቀለም ከሥሩ ስለሚታይ ነው ሲሉ ሰምቻለሁ። ከውስጥ ግን የፈካ አረንጓዴ ነው። ትናንሽ ዓሳዎች ከባሕሩ ገባ ብሎ በተሰራው ግንብ ላይ ይተራመሳሉ። ውስጥ ለውስጥ አረንጓዴውን ቀለም እየጣስኩ ዋኘሁ። የማያልቅ አረንጎዴ ነው። ውሃው ይቀዘቅዝ ስለነበር ብዙም ሳልቆይ ወጣው። በጣም ጨዋማ በመሆኑም ወደ ክፍሌ ተመልሼ ታጠብኩና ልብሴን ለብሼ ተመለስኩ።

አባቴ በጠዋት ሳይቀሰቅሰኝ ወደ ሥራ ሄዶ ስለነበር አካባቢውን ለማየት መዘዋወር ጀመርኩ። በግቢው አውላላ ሜዳ መሃል ላይ ያለውን የአፄ ቴዎድሮስን ምስል እያየሁ ከፊት ለፊቱ ወዳለው ፎቅ አመራሁ። ከቤቱ ጋር ስደርስ አንድ የማሪን ኮማንዶ ልብስ የለበሰ ወጣት ወታደር " ቁም!"





የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶኝ፣ ወዴት እንደምሄድና ማን እንደሆንኩ ጠየቀኝ። እኔም ግቢው ውስጥ ለማየት እንደምዘዋወርና ከአስመራ የመጣሁ እንግዳ መሆኔን አስረዳሁት። ግራ በተጋባ ሁኔታ ይመለከተኝ ጀመር። ከሱ ጋር ቆሜ እንዳለሁ ኮሞደር ጌታቸው ከቢሮአቸወ ወጥተው ቆሞ ወደሚጠብቃቸው ዋዝ መኪና ሲያመሩ ስላዩኝ ጠሩኝና ገላገሉኝ።

"ታዲያስ? ሙቀቱን እንዴት አገኘኸው?" አሉኝ በቀልድ ዓይነት ንግግር ወደ መኪናቸው እየገቡ።

"ተስማምቶኛል" ብዬ መለስኩ።

"እረ ባክህ? እኔ ወደ ጀ/ደምሴ ጋር እየሄድኩ ነው። ትንሽ ሳንቀይ አንቀርም። አንተ እስከዚያው ለምን በጀልባ ትንሽ ዞር ዞር ብለህ አገር አይቶይም?። መርከቦችንም ጎብኝ ከዚህ በፊት በጀልባ ሄደህ ታውቃለህ?" አሉኝ። በደስታ ፈንደቄ "እረ አላውቅም። ግን መሄድ እፈልጋለሁ!" ብዬ መለስኩ በተጣደፈ ዓይነት ሃሳባቸውን እንዳይቀይሩ እየፈራሁ።

"ጥሩ ነዋ" አሉና ቀደም ብሎ ሲያጋግረኝ ወደነበረው ኮማንዶ ዞር ብለው "ለኮማንደር በጀልባ ዞር ዞር አድርገው አካባቢውን እንዲያሳዩት ንገረው!" አሉት። እሱም በተጠንቀቅ ሠላምታ ሰጥቶ ትዕዛዙን እንደተቀበለ ገለጸ። በእጋጣሚው እየተደሰትኩ ተሰናብቼአቸው ኮማንዶውን ተከትልኩት። ከቀድሞው በተለየ ሁኔታ በሰላም እየተነጋገርን ሁለት ትልልቅ መርከቦች ከቆሙበት ቦታ ደረስን። ትንንሽ ጀልባዎች ጥግጥጉ ላይ ቆመዋል። አንድ አምስት የሚሆኑ ኦክስጂን የተሸከሙ ጠላቂ ዋናተኞች ወደ ውሃው እየጠለቁ ነበረ። የተባሉት ኮማንደር ከአምስቶቹ አንደኛው ኖረው ኮማንደሩ ከውሃው

ውስጥ ሳይገቡ ኮማንደው ደርሶባቸው መልክቱን አስተላለፈ። እሳቸውም ዞር ብለው ካዩኝ በኋላ ጥግ ላይ ቆመው የነበሩትን ሁለት የባሕር ኃይል ወታደሮች ጠርተው አነጋገሯቸውና ሁለቱ ወደኔ አቅጣጫ ማምራት ጀመሩ። ኮማንደሩ ያደረጉትን የመቅዘፍያ መጫሚያ በእግራቸው እያነሱና መልሰው ከመሬቱ እያስቀመጡ ተጉዘው ከውሃው ውስጥ ገብተው ጠፉ።

ከሁለቱ ባሕር ኃይሎች ጋር ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ልብሴን ማውለቅና በውስጥ ሱሪ ብቻ መሆን እንዳለብኝ ነግረውኝ ከቆሙት ጀልባዎች ወደ አንዱ አመሩ። ከኮንማደው ጋር ተሰነባብቼ ተከተልኳቸው። በትንሽ ዕቃ ቤንዚን ያዝንና የጀልባዋን ሞተር አስነስተው በዝግታ በቀይ ባሕር ላይ ተንሳፈፍን። ልዩ ስሜት ተሰማኝ።

አልፎ አልፎ ጭንቅላታቸው ላይ ጥምጣም የጠመጠሙ ዓሣ አጥማጆች ትንሽ ጀልባ እየቀዘፉ ሲጓዙ ይታያሉ። ሁለቱ ባሕር ኃይሎችም አንዳንዴም ጀልባዋን እያቆሙ፣ አንዳንዴም ሠላምታ ይሰጧቸዋል፣ አንዳንዴም ጥያቄ ይጠይቋቸዋል። ትንሽ እንደተዘዋወርን “ጉርጉስም ሄደህ ታውቃለህ?” አሉኝ ። ሄጄ እንደማላውቅና ለመሄድም እንደምፈልግ ገለጽኩላቸው። ጀልባዋ ከሞገዱ ተቃራኒ አቅጣጫ ስትጓዝ በጣም ስለምትነጥር በእጄ ከጎን ያለውን ገመድ ግጥም አድርጌ ይዤ አብሬ እየነጠርኩ ተጓዝኩ። ወደ መሃል ስንደርስ የባሕሩ አረንጓዴያማ ቀለም ፍንትው ብላ በወጣችው ፀሐይ ወደ ቢጫ ቀለም ተቀይሯል።





ከሩቅ የእሸዋ መሬት ብቅ ብሏል። እየቀረብን ስንሄድ ትላልቅ ዣንጥላዎችና አንድ ቤት ታዩን። ጉርጉሱም ስንደርስ ከዳርቻው ላይ ጀልባዋን አቁመን ወረድን። ከባሕሩ ዳርቻ ላይ የተሠራ የመንግሥት ሆቴል በፀሐይ መከላከያ ጃንጥላዎች ተከቦአል። ጀልባው ውስጥ ካለው ሣጥን ውስጥ ሱሪዬን አውጥቼ ታጠቅኩና ከባሕረኞቹ ጋር ወደ ሆቴሏ አመራን።

ከአንዷ ጥላ ሥር እንደ ተቀመጥን አስተናጋጇ መጣች። ቁርስ ለለመብላቴ የታወሰኝ ያን ጊዜ ነበር። ቀኑ ያመጣቸው እንግዶችና አስደሳች ሁኔታዎች ራቤን አስረስተውኝ ነበር። ሰዓቱ ሄዷል። “ልጋብዛችሁ፤ ምን ትበላላችሁ?” ብዬ ብጠይቃቸው እንደ መገረም ብለው “ኧረ ምንም አንፈልግም። እዚያ ከበባችን ምን የመሰለ ምግብ ነው የምንበላው። ቁርስ ደግሞ በልተን ነው የመጣነው” አለኝ አንደኛው። ሌላኛው ደግሞ የሚመገቡትን ምግብ ጥራት አድንቆ ደገመልኝ። ለራሴ ቁርስ አዘዝኩና።
“የሚጠጣስ አትይዙም? ቢራ ጠጡ!” አልኩኝ።
“አይ እኛማ ሥራ ላይ ነን” አለ አንደኛው።
“ቀሙ ግድ የለም አንዳንድ እንያዝ” ብዬ ተጨቃጭቀን አንዳንድ ቢራ አዘዝን።
“ባሕር ኃይል ደግሞ ምን ችግር አለ ብለህ ነው። የፈለግነው ሁሉ ሞልቷል። ውጭ ምግብ ቤት ሄደን በልተን አናውቅም። ከቡብ የሚዘጋጀው ምግብ በጣም አሪፍ ነው። የምንፈልገው ሁሉ አለ።” አለ አንደኛው። ሌላኛው ቀጠል አድርጎ፣ “አሁን እኛ የምንፈልገው ከጠሩ ጋር በጦርነቱ ለመሳተፍ ነው።” ሲል በጣም ገረመኝ። ጦርነት መሄድ እፈልጋለሁ የሚል

ሰው ሰሰማ የመጀመሪያዬ ጊዜ ነበር። ትኩር ብዬ ከተመለከትኩት በኋላ "ለምን? ልለው ትንሽ ቃትቶኝ ነበር፤ በምትኩ "እንዴት?" አልኩት።
"በቃ መዝመት አንፈልጋለን። ብዙ ልጆች ከኛ ጋር ያሉ አዝምቱን ብው ጸፈዋል። እኛ ከዓመት ዓመት ሥልጠና ሰልችቶናል አሁን በዚህ ዘመቻ መሳተፍ አፈልጋለን" አለኝ። ገርሞኝ እንደገና ተመለከትኩትና "ይኸው ዘመቻችሁ አይደልም እንዴ? ጦርነት እዚህም በማንኛውም ጊዜ ሊነሳ ይችላል።"

"አይ እዚህማ መች ይደርሳሉ ብለህ፣ ባሕር ኃይሎች ዝግጁ ነን። ነገር ግን አሁን ከጠሩ ጋር ተሰልፈን መዋጋት እንፈልጋለን። በቃ እዚህ ባሕር ላይ ሻዕቢያን መጠበቅ ሰልችቶናል። የኛ ጓደኞችም ብዙዎቹ እየጠየቁ ነው" አለ። ሲናገር በሱ ውስጥ ያለውን ወኔ ወደ ሰሚው ያስተላልፋል። አደነቅኩት። ከቃሉ በላይ አነጋገሩ እውተኛነቱን ይመሰክራል። አተኩሬ እያየኋቸው አንዳንዴም ባሕሩን እያቃኘሁ ቢራዬን መጎንጨት ጀመርኩ። ሰዓቱ እየሄደ ስለነበር ወደ ባሕር ኃይል ግቢ እነ አባቴ ከመመለሳቸው በፊት ለመድረስ ቶሎ ተነሳን። እንደገና ከቀይ ባሕር ሞገድ ጋር እየጨፈርንና እየደነስን ከተነሳንበት ቦታ ተመለስን። ሁለቱን ባሕረኞች አመስግኜና ዳግመኛ ብመለስ ሳልጠይቃቸው እንደማልሄድ ቃል ገብቼ ተሰናበትኳቸው። ስለ ወታደሮች ከታዘብኩት አንዱ ሰውን በግለሰብ ደረጃ ሲቀርቡ የማይረሳ ገርነትታቸውና ትዝታ የመተው ተሰጥዎአቸውን ነው።





ጀ/ደምሴና ካፕቴን መርሻ እስኪመጡ ባሕሩ ዳር ሄጄ ተቀምጬ ጠበቅኩ። ወደ አስመራ መመለስ ስለነበረብኝ ዕቃዬን ሁሉ አሰናድቼ ነበር። ከሰዓት በኋላ ጊንዳአ ወደተባለች፣ ምፅዋ አካባቢ ወዳለች ቦታ ተጉዘን የአንድን ጦር ሁኔታ ለአጭር ጊዜ ካየን በኋላ፣ ወደ ምፅዋ ተመለስን። ባሕር ኃይል ግቢ ስንገባ ሄሊኮፕተሯ ቀድሞ የተወችን ቦታ ላይ አርፋ እየጠበቀችን ነበር። ብዙም ጊዜ ሳናጠፋ ወደ አስመራ ጉዞአችንን ጀመርን። አስመራ የደረስነው ወደ አመሻሹ ላይ ነበር። ተሳፋሪው ላይ ድካም አይታይም - ከኔ ላይ በቀር። ከሄሊኮፕተሯ እንደወረድን ወደ ሚጠብቀን ቶዮታ ላንድ ክሩዘር በፍጥነት ያለምንም ንግግር ተሳፍረን ወደ ቤት ጉዞ ቀጠልን። ከኋላ የሚከተለን መትረየስ የተጠመደበት ግልፅ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር፣ ሶስት ወታደሮች ጭኖ አብሮን ይከንፋል። አስመራ ከተማ ወደ አመሻሹ ላይ ብዙም ትርምስ አይታይባትም። የአስመራ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት፣ የአዲስ አበባን ከምሽቱ ስድስት ሰዓት ያስታውሰኛል። ሰው ሁሉ በቤቱ ከቶ ነው የሚቀመጠው። በአንዳንድ የታወቁ ቡና ቤቶች ከሚታዩ ጥቂት ሰዎች በቀር ቀኑን ሙሉ ሲተራመስ የሚውለው ሲቪል ነዋሪና ወታደር ጭምር በየፊናው በጊዜ ገብቶ ተቀርቅሯል።

እቤት እንደ ደረስን እኔን ጥለውኝ አባቴና አብረውት የነበሩት መኮንኖች ወደ ቢሮ ተጓዙ። ወደ አስመራ ለጊዜያዊ ሥራ ተብሎ የተላከበት ምክንያት ከመቼውም ይበልጥ አሁን ግልፅ ሆኖልኛል። በተለያዩ ቦታዎች በተደረጉት ውይይቶች እንደ ተረዳሁት በጦሩ ውስጥ የተፈጠረው ብጥብጥ እየበረታ በመሄዱ፣ ሻዕቢያም ይህን ዕድል በመጠቀም የጥቃት እርምጃ

ለመውሰድ ዝግጅት ላይ እንዳለ አዲስ አበባ በደረሰው መረጃ መሠረት የዕዝ ጠገጉን (ሚሊተሪ ሃየርአርኪ)፣ የመምሪያ ሰንሰለቱን ለማጠናከር ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ሻዕቢያ በተለይ በከረንና በምፅዋ ጥቃ እንዳይፈጸም ለማድረግ ነው። ጥቃት ከተቃጣም አጸፋውን ለመመለስ ለመቋቋም እንዲቻል ለማድግ ነው። እንደሱ አመለካከት ዋናው ጥያቄ ግ የጊዜ ጥያቄ ነበር። መንግሥት በየቦታው ጦር በማሰልጠን ላይ ስለነበ አሁን የሚደረጉት ጠሩን የማጠናከር እንቅስቃሴዎች የሰለጠነው ጦር ዝግጁ ሆኖ ቦታውን እስኪይዝ በኢትዮጵያ ጦር ሥር ያሉትን ቦታዎች ለመከላከ የታቀዱ ነበር። የብ/ጀ ታሪኩ መገደል፣ የብ/ጀ ከበደ ጋሼ ማዕረግ ተገፎ ከሥራ መወገድ፣ ከዚያም አልፎ የሠራዊቱ አዛዥ ሜ/ጀ ረጋሣ ጂማ መዛወር ላይ ለደረሰው ውርደት ዋነኞቹ ምክንያቶች ነበሩ። በአለቆቹ ላይ ያለውን እምነት እንዲያጣ ከማድረጋቸውም በላይ ጠሩ ለአለቆቹ ያለውን ክብርም እንዲቀንስ አድርጎታል። ይህ ከወታደር ሕግም ሆነ ከሰብአዊ መብት ሕጎች ውጭ የሆነው ለመንግሥቱ ኃ/ማሪያም ለጊዜው ጥሩ መስሎ ቢታያቸውም የኋላ ኋላ ግን የራሳቸውም መጥፊያ ሆኗል።

በጠሩ ውስጥ ክፍፍልን በመፍጠርና የአለቆችን ሥልጣን በመድፈር ለራሳቸው ተወዳጅነትንና ተራና አልባሌ እንዲሁም የአጉል ጀብደኝነት ስምን ለማትረፍ ብለው በግልፍተኝነት የወሰዷቸው እርምጃዎች፣ ድርጊቱ በቀጥታ የተመለከታቸውን ሰዎች ብቻ ሳይሆን፣ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት አጥፍቷል። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የሞቱለትን ዓላማ መና እንዲቀር አድርጓል።





ወታደር አለቆቹን ማክበር በመጠኑም መፍራት በትንሹም መውደድ አለበት። የወታደር ሥነሥርዓት ደንብም ይህንኑ ይጠይቃል። በቀውጢ ሰዓት በአዛዦች የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ተቀብሎ ያለምንም ጥያቄ ሕይወቱን ለአደጋ አጋልጦ ግዳጁን መፈፀም አለበት። የቀድሞ የኢትዮጵያ ወታደር ቀብሎ የሚታወቀው ጦር በዚህ ሥርዓት ታንጾ የሠለጠነ ነበር። ደርግ ከየቦታው በግድ እያግበሰበሰ እንደመሣሪያ ተደርጎ በተቀረፀ እንጨት ለአንድ ወይ ሁለት ወር ሰልጥኖ፤ ትነሽ ተኩስ ተለማምዶ፤ ወደ ጦር ሜዳ የሚላከው ጦር ግን ውትድርናን እንደሙያ ሳይሆን እንደ እርግማን ነበር የሚያየው። ሌት ተቀን ጆሮን የሚያደነቁረው የ/ሌ/ኮ መንግሥቱ ትልቅነት እየተለፈፈለትና መፈክር እያሰማ ነው የሚውለው። የሚሰጠው የፖለቲካ ትምህርት ከወታደራዊ ትምህርቱ ይበዛል። እፊቱ ቆሞ የሚለፍፈው መ/አለቃ ካድሬ በማዕረግ የሚልቁትን መኮንኖች በንቀት ሲመለከት ያያል። የአንድ ብርጌድ የወታደራዊ ደህንነት ኃላፊና የፖለቲካ ኃላፊ ከብርጌዱ አዛዥ ጋር እኩል ቤት ሰፍረው ሲከራከሩ ያያል። ሥራቸው የጦር መሪዎችንና ሌሎችን መሰለልና ጠሩን የመንግሥቱ ኃ/ማርያም አገልጋይ ማድረግ የሆነ አንዳንድ የበታች መኮንኖች በልምድና በእውቀት በብዙ ዓመታት የሚበልጧቸውን የጦር መሪዎች አለአግባብ ሲከሱ ተራው ወታደር የጦር መሪዎችን እንዲያከብር ይጠበቃል?

ማምሻዬን ወደራሴ መሥሪያ ቤት ደውዬ ሰዎች ሳነጋግር የሬዲዮ ሠራተኛዋ ወደ አሰብ እንድሄድ ትዕዛዝ መተላለፉን ነገረችኝ። በሁለተኛው

ቀን ወደ አሰብ መሄድ ስለነበረብኝ ማምሻውን ከአባቴ ጋር ስለ አንዳንድ ነገሮች ለመነጋገር ነቅቼ ጠበቅኩት። በመጠበቅ ላይ እያለሁ ጀነራል ኃይሉ መጡ። ዘለግ ያለው ሰውነታቸውን አሁንም በዝግታ እያንቀሳቀሱ ገቡ። ሠላምታ ከሰጧኋቸው በኋላ ወደ መኝታ ክፍላቸው ገብተው ልብሳቸውን ለውጠው ተመለሱ። በአነጋገራቸው ዝግታ እና በሚናገሯቸው በጥንቃቄ የተመረጡ ቃላት ሰውዬው ከዚህ በፊት ሰውን በንግግር አስቀይመው እንደማያውቁ ገመትኩ። በአዛዥ መኮንኖች መሀል ባልተለመደ ሁኔታ የሰው ስሜት ላለመጉዳት በጣም ይጠነቃቀሉ። ከጊዜ በኋላ የመጣ ሳይሆን የተፈጥሯቸው ይመስላል። ከአዲስ አበባ ካመጣነው ቀሎ በሳህን አውጥቼ ከሻይ ጋር ጋበዝኳቸውና ከኔ ጋር በአንድ ትምህርት ቤት ይማር ስለነበረው ልጃቸው፤ ስለጠሩም ሁኔታ ተነጋገርን። ለሳቸውም እንዲሁ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ ለኮሞደር ጌታቸው የሰጣኋቸውን ዓይነት "የስዊዝ አርሚ ኦፊሰርስ ናይፍ" በስጦታ መልክ አበረከትኩላቸው። ከጀ/ል ኃይሉ ጋር ስንጨዋወት የአባቴ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር ከቤቱ ፊለት ለፊት መጥታ ቆመች። በር ከፍቼ ተቀበልኩት። ኮፍያውንና በትረ መኮንኑን አቀብሎኝ ፀጉሬን እያሻሸ ሳሎን ገባ።

ስንጫወት ትንሽ ካመሸን በኋላ ስለ አሰብ ጉዞዬ ነገርኩት። በነጋታው ወደ ግንባር እንደሚሄድና የምንተያየው በሚቀጥለው ቀን ማታ ብቻ መሆኑን ገለጸልኝ። አብሬው ግንባር ብሄድ ደስ ይለኝ ነበር። ነገር ግን ወደ አሰብ ከመሄዴ በፊት ሥራዬን መጨረስ ነበረብኝ።





"ነገ እንኳን መሥሪያ ቤት ሄጄ ሥራዬን መጨረስ አለብኝ። ግን እዚህ የምትቆይ ከሆነ ተመልሼ መምጣቴ አይቀርም። አብሬህ አንዳንድ ቦታዎች መዘዋወር እፈልጋለሁ" አልኩት።

"እዚህማ መቆየቴ የማይቀር ነው። ቢያንስ አንድ ሁለት ወር ያህል እቆያለሁ። አዛዥ እስኪሾም ድረስ። ምን ይታወቃል እኔንም ቆይ ሊሉኝ ይችላሉ።"

"መምጣቴ አይቀርም። ስመጣ ግን አብሬህ መዘዋወር ነው የምፈልገው" አልኩኝ።

"ትችላለህ" አለኝ። ሲያነጋግረኝ በድካም የተነሳ ዓይኖቹ አንዳንዴ እየተከደኑ ይከፈቱ ነበር።

"በል አንተኛ ወንድሜ" ብሎ ተነሳ፤ሁል ጊዜ አዲስ አበባ ሲመጣ እንደሚያደርገው ድንገት ከመቀጫው ብድግ ብሎ ወደ መኝታ ቤቱ እየሄደ።

"ደህና እደር" አለኝ። እኔም ተከትየው መኝታ ቤት ድረስ ከሸኘሁት በኋላ "ደህና እደር" ብዬው ተመለስኩ።

ቀኑን ሙሉ ከሚያሳልፈው ውጣ ውረድ እና ብስጭት በኋላ ፈገግ ለማለት መቻሉ ያስደንቀኛል፤ እኔ በሱ ቦታ ብሆን ራሴን ሳልስት አልቀረም። ወደ መኝታ ቤቴ ስመለስ ስልክ ሲጮህ ተሰማኝ። ከዚያም አባቴ ሲያወራ ሰማሁት። በሌሊት ቢያንስ ከአምስት ጊዜ በላይ ስልክ ይጮኻል። እናም አለመበሳጨቱ ይገርማል። ከጥሪው ሰባ ከመቶ የሚሆነው ደግሞ ችግርን እንጂ ሌላ አያበስርም። ብዙ ትዕግስት ይጠይቃል። መጥፎ ዜና የማዳመጥ ትዕግስት። በጥሩ ዜና መምጣት ወይ ጥሩ ዜና በመጠበቅ

የሚታደስ ትዕግስት። ለአባቴ አዘኔታ እየተሰማኝ ወደ መኝታ ቤቴ ገብቼ ተንጋለልኩ። አለ ሀሳብ መተኛት መቻልን ያህል ዕድል የት ይገኛል? አለሃሳብ ተኝቶ አለሃሳብ መንቃት ትልቅ እድል ነው። የሃላፊነቱ ክብደት ብቻ እንቅልፍ ይነሳል። ብዙ ሺህ ሰው በሕይወት እና ሞት መሃል የቆመበት ሃላፊነት።

ጧት ተነስቼ ወደምሠራበት መ/ቤት የአስመራ ቅርንጫፍ ቢሮ ተጓዝኩ። ያ ተወሰደ የተባለው የቴሌ ፕሪነተር መሣሪያ ተመልሶ ስለነበር ሥራዬ በጣም ቀሎ ጠብቆኛል። እሱን ገጣጥመን ከጨረሰን በኋላ የቀሩትን ሥራዎች በዚያኑ ቀን ጨረስኩ። የአስመራ ከተማን ደግሞ ለመቃኘት በእግሬ ከተማዋ ውስጥ እየተዘዋወርኩ አንዳንድ ዕቃዎችን ገዝቼ ወደ አባቴ ቢሮ አመራሁ። ቃኘው ስቴሽን ከውጭ ሲታይ ያስፈራል። የወታደር ትርምስ በየኮርነሩ የተጠመዱት መትረየሶች ከየመንገዱ የሚያርቁ እንጂ የሚጋብዙ አይደሉም። ከዋናው በር ስደርስ ከራስ ፀጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ ድረስ ተፈተሽኩ። አንድ ክፍል ውስጥ እንድቀመጥ ተደረግኩና በስልክ ማንነቴን ማጣራት ቀጠሉ። ከዚህ በፊት በመኪና ስለነበር የገባሁት የዚህ ዓይነቱ ፍተሻ አልገጠመኝም። የሚያስፈልገው ማጣራት ከተደረገ በኋላ እንድገባ ተፈቀደልኝ።

ዋናውን በር እልፌ ትንሽ እንደ ተጓዝኩ ወደ ቤት ደርሼ መንገዱን ላቋርጥ ስል ከጨለማ ውስጥ "ቁም!" የሚል የሚያስተጋባ ድምፅ ቀልቤን ገፈፈኝ። " ቁም ማነህ?" ግራ ከተጋባሁ በኋላ "ወደ ቤት ነው የምሄደው የጀ/ደምሴ ልጅ ነኝ" ብዬ መለስኩ።





"ቀጥል!" አለኝ ወታደሩ። "ቀልብ የሚገፍ ነገር ይግፈፈውና!! አሁን እንደዚህ በጭለማ ማባረቅ ምን ያስፈልጋል?" እያልኩ በልቤ ረግሜው መንገዴን ቀጠልኩ። ቤት ስደርስ ማንም አልነበረም። አምሽቼ ጠቀበኩ፤ የመጣ የለም። ሌሊት ወደ ዘጠኝ ሰዓት ላይ እንቅልፍ ይዞኝ ሄደ። ጠዋት ስነሳ ሰው የለም። ለባብሼ ወደ አባቴ ቢሮ ሄደኩ- ጥድፊያ ላይ ነበር።ብዙ ማውራት አልቻልንም።

ተሰናብቼው ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ተጓዝኩ። የምበርበት አውሮፕላን አሁንም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተከራየውና ዕቃ የሚያመላልሰው ሄርኩልስ አውሮፕላን ነበር። በመጀመሪያ መቀሌ እንደምናርፍና እህል አራግፈን እንደገና እህል ለመጫን ወደ አሰብ እንደ ምንሄድ ነገሩኝ። መቀሌ ሄጄ ስለማላውቅ በአጋጣሚው እየተደሰትኩ የአውሮፕላኑን ደረጃ ወጣሁ።

የተሳፈርኩት የፓይለቶች ክፍል ውስጥ በስተጀርባቸው ከኋላቸው ካለው መቀመጫ ከአየር በረራ ኢንጂነሩ ጎን ነበር። አውሮፕላኑ በሙሉ በጆንያ ተሞልቷል። በመንገዳችን ላይ አንዳንድ ቦታዎችን እየተጠቋቆሙ ያያሉ። የደህንነቱ ሠራተኛ እህሉ ላይ ከኋላ ተኝቷል። መንግሥት ለምን እንዳስቀመጠው ገባኝ። እነዚህ ሰዎች በጣም ወሬ የሚወዱ ይመስላሉ። ሰሙየው ግን ጆንያው ላይ እየተንከባለለ ሲያንኮራፋ ነው መቀሌ የደረስነው።

መቀሌ ሰንደርስ፣ በሰኮንዶች ውስጥ፣ እህል የሚያወርዱ ሰዎች ተዘጋጅተው ኖሮ፣ አውሮፕላኑ ውስጥ ገብተው፣ ጆንያው ላይ ተረባረቡበት። የሚጫኑት መኪኖችም ፊታቸውን አዙረው ተጠግተው ቀመዋል። ፈንጠር ብዬ ዙሪያ ገባውን ቃኘሁት። የአውሮፕላን ማረፊያው ዙሪያ ምሽግ ነው። የማረፊያው ሜዳ አሰፋልት አይደለም። እንደውም አውሮፕላን ማረፊያም አይመስልም። በአካባቢው የሰፈነው የስጋት አየር፣ ችግርን ወደ አፍንጫ እያነፈሰ የሚያመጣ ይመስላል። ቦታው ከበደኝ። መቀሌን ተዘዋውሮ ለማየት የነበረኝ አቅዴም በነበረው ጥድፊያና በሰፈነው ሰጋት ከሰመ። እዚያው እየተዘዋወርኩ የነበረኝን ጊዜ የትግራይን አየር እየሳብኩ ጨረስኩት። ሌላው ቢቀር ከአየሩ ደርሶኛል። ክብደት ያለውን ሰሜናዊ አየር ረጋ ብዬ ሳብኩት። መቀሌ ብዙም ሳንቆይ ጉዞ ወደ አሰብ ቀጠልን። ከጥቂት ሰዓታት በረራ በኋላ አሰብ ሰንደርስ ከቀይ ባሕር ላይ መሽከርከር ጀመርን። ቀይ ባህርን በመስታወቱ እየተመለከትኩ ቀዩን ቀለም ፈለግኩት። ከላይ ሲታይ ደም የሚመስል ቀይ ቀለም ከባሕሩ ስር ረግቶ ይታያል ስላሉኝ እሱኑ ለማየት ፈለግሁት። ለሌሎች የታየው ቀለም ከእኔ ተሸሸጓል።

በአሰብ ጥርጊያ አየር ማረፊያ እንዳረፍን ከመ/ቤት መኪና መጥቶ እንደሆን ለማየት እህል ማስቀመጫ ወደሚመስል የመንገደኞች መሳፈሪያ ጣቢያ አመራሁ። ሞቃቱ አየር ፊት ይገርፋል። ገልመጥ ገልመጥ ብዬ ካየሁ በኋላ፣ የማውቀው ፊት ስለጣሁ፣ ሻንጣዬን ይዤ ከውጭ በኩል ካለች ሻይ ቤት ገባሁ። ሻይ ቤቷ በውሃ ሰማያዊ ቀለም ደምቃ፣ መስኮቶቿ ተከፍተው፣ ነፋሻ አየርን ትለግሳለች። ባግዳሚ ወንበሮችና በረዣዥም ጠረጴዛዎች





ተጨናንቃለች። የአየር ማረፊያው ሠራተኞች ለስላሳ መጠጦችን ይዘው ያወካሉ። ምን እንደሚሉ ግን ማወቅ አልቻልኩም። የሚነጋገሩት በአፋርኛ ነው። አብዛኞቹ ቢጫ ጥምጣም በጭንቅላታቸው ላይ ጠምጥመው ሰፋ ያለ ዥርያ ለብሰዋል። በሙቀቱ ፊፅሞ የተረበሹ አይመስሉም። የአሰብ ሙቀት እቶን እንጂ ሙቀት አይደለም። ሁለት ዓይነት ሙቀት ነው። አንደኛው አየር የሌለው ሙቀት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ እንደ እሳት የሚፋጅ አየር ያለው ሙቀት ነው። ስለ አፋሮቹ ጠረኝነት አንዱ ሲናገር የሰማሁት ትዝ አለኝ። "እየሀ" ብሎ ጀመረ። "አፋርን መዋጋት ዘበት ነው፣ እሱ ሰባት ቀን በባዶ እግሩ በዛ ሙቀት በጥቂት ወሃ መጓዝ ይችላል። ሊዋጋ የሚሄደው ጦር ግን በመኪና እንኳን ቢጓዝ በሙቀትና ውሃ ጥም ዝሎ ጥይት ሳይተኩስ ነው የሚፈታው" አለ።

እውነትም የዚህ ዓይነት ሙቀት ውስጥ እንኳን መዋጋት መተንፈስ እንኳን ይከብዳል። የሻይ ቤቱን ግርግር ስመለከት፣ ከመ/ቤት የተላከው መኪና ደረሰ። ሊቀበለኝ ከመጣው ልጅ ጋር አዲስ አበባ ተዋውቀን ስነበር እየተጫወትን ወደ አሰብ ከተማ ገሰገስን። አሰብ ሰቂርን አልፈን አሰብ ከተማ ከመድረሳችን በፊት ወደ ግራ ተገንጠልንና አንድ በተንቀሳቃሽ ቤቶች የተሰራ የመኖሪያ ሥፍራ ቀምን። ቦታው ታይቶ የማይጠገብ የተፈጥሮ ውበትና መስእብ ያለው ነው። ቤቶቹ የቆሙት ከባሕር አጠገብ ለለነበረ ገና ለማረፍ የሚጣባበቁ መርከቦችና የአሰብ ወደብ ከሩቅ ይታያሉ። የባሕር ሞገድ እየተንደረደረ ይመጣና ተመልሶ ይሻሻል። ዕቃዬን አውርጄ ወደ ተያዘልኝ ክፍል እየተመራሁ ገባሁ። ውስጥ ገብቼ አየር ማቀዝቀዣ

እንዳለው ሳይ ከፈትኩትና የአሰብን ሙቀት ለጥቂት ሰዓታት ደህና ዋል ብዬ ትንሽ ጋደም አልኩ።

ከእንቅልፍ ስነቃ ቀኑ ተጋምሶ ነበር። የቀረውን ቀን መ/ቤት በመሄድ እንዲሁም የአሰብን ከከተማ በመ/ቤት መኪና እየተሽፈርኩ ሳስስ ቆየሁ። ማምሻዬን ወደ ወደብ ከመሥሪያ ቤት ጓደኞቼ ጋር፣ ከጠርሙሱ ላይ በረዶ የሚቀረፍለትን የአሰብን ቢራ እየተጎነጨን አምሽተን ወደ ሰፈር ተመለስን። ሰዓቱ ከለሊቱ ሰምንት ሰዓት ገደማ ነበር። የቀኑ ድካም ከሙቀቱና ከቢራው ጋር ተደምሮ ለሽ ያ እንቅልፍ ላይ ነኝ። ድንገት የሚሰነጥቅ ድምፅ ከነበርኩት የፀጥታ ዓለም አስደንብሮ አስነሳኝ። ድምፁ አላቆመም ቀጠለ። ሁለት- ሶስት- - አምስት.... አካባቢው ድብልቅልቁ ወጣ። እንደምንም ሱሪዬን አጥልቄ ከቤቴ ተፈትልኬ ወጣሁ። ድምጹ ወደ ሚመጣበት አቅጣጫ ስመለከት፣ ከባሕሩ ላይ እየተስፈነጠሩ የሚወጡ ብልጭታዎች አብሯቸው ከሚነጉደው ጩኸት ጋር ሲምዘገዘጉ ታዩኝ። "ዛሬ አለቅን" አልኩ። ከክፍሌ እንደምንም ብዬ ለመራቅ ስሞክር እንደኔ ከየክፍሎቻቸው የወጡ ሌሎች ሰዎች "ና ወዲህ!" ብለው ሲጠሩኝ ወደነሱ ተጠጋሁ። ጩኸቱ ብዙም አልቆየም፣ ግን ያቺ አምስት ደቂቃ አንድ ሰዓት ሆናብኝ ነበር። ምሽቱን ምን እንደተፈጠረ እየተወያየን አነጋን። ጠዋት ሻዕቢያ በፈጣን ጀልባዎች ወደ ወደቡ በመቅረብ የአሰብን ነዳጅ ማጣሪያ ለማቃጠል ያደረገው ሙከራ መሆኑን ሰማሁ። ምንም እንኳን የሞርተርና ሌሎች መሣሪያ ጥይቶች በማጣሪያ አካባቢ ባይወድቁም፣ ዒላማቸውን ሳይሆን የአስራ አንድ ሰዎችን ህይወት ያጠፉ መሆናቸውን ሰማን። አሰብና እኔ እንግዲህ እዚህ ላይ ይበቃናል አልኩ። ዒላማቸውን የሳቱ የሌሎች





ጥይቶች እራት ከመሆኔ በፊት ወደ አገሬ ልነሳ- ጎመን በጤና በማለት፣ ይብላኝ ለአሰቤዎች ብዬ በሰው ልጅ ዕጣ እየተገረምኩ ቀኗን አንዳንድ የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን ገዝቼ፣ በሚቀጥለው ቀን ወደ ደገኛነቴ ለመመለስ ወሰንኩ።

ወደ ከሰዓት በኋላ ከአሰብ ወጣ ብላ ወደምትገኘው ድችአቶ ወደተባለችው ከተማ ቀጥሎም ከድችአቶ አለፍ ብላ ካለችው ከመንዲ አንዳንድ ዕቃዎችን በርካሽ ገዝቼ በነጋታው አዲስ አበባ ለመመለስ ወደ አውሮፕላን ማቢያው አመራሁ። ከአሰብ የምመለሰው በአየር መንገድ የመንገደኞች አውሮፕላን ስለነበረ የሲቪል መንገደኞች ተሰብስበው ጠበቁኝ። ከመንገደኞች ውስጥ የወታደር ልብስ የለበሱ አንድ ሰው ነበሩ። የአሰብ ባሕር ኃይል አዛዥ ናቸው። ረዥም ቀይና ለስለስ ያሉ ሰው ናቸው። ወደ አዲስ አባባ ተጠርተው እንደሚሄዱ ገመትኩ። እርስዎን አያድርገኝ አልኩ በሆዴ። ከወራት በኋላ አባቴ አሰብ በተደበደበ በነጋታው ለሁለት ሰዓት ያህል ወደ አሰብ መጥቶ እንደነበር ስሰማ የእኚህን ሰው እጣም ተረዳሁ።

"ምን እየሠራህ ነበር አፍንጫህ ድረስ መጥተው እስኪተኩሱብህ? ብለው ምንም መልስ አልሰጠኝም። የሃያ አራት ሰዓት ጥበቃውን እንኳን ጨርሶ አይቆጣጠርም" ካለ በኋላ፣ "ወንበዴዎች ተደምስሰዋል" በማለት ከአዲስ አበባ የተላለፈው ዜና የመንግሥት ፈጠራ እና ውሸት መሆኑን አጫወተን። በቴሌቪዥን ተማረከ ተብሎ የታየው መሣሪያም፣ ከዚያው ከባሕር ኃሀል የወጣ መሆኑን ነገረን። ለነገሩ የወንበዴው ጀልባ ተደምስሶ

ከሰመጠ መሣሪያው ሳይጎዳ፤ ሳይሰምጥ እንዴት ሊያዝ ይችላል? እንዲ ከጊዜ በኋላ ደግሞ ጀልባዎቹ ለሻዕቢያ በኢራቅ የተሰጡ ፈጣን ጀልባዎ እንደነበሩ ታወቀ። አውሮፕላኑ የአሰብ ባሕር ኃይል አዛዥን ከሲሺ ተንኸ ጋር ይዞ ወደ አዲስ አበባ በረረ። እኔም ከባሕር ኃይል አዛዡ ኋ ተቀምጬ "ከመሓላችን ቢያንስ አንድ ሰው በጉዞው መጨረ የሚጠብቀውን አያውቅም" ብዬ አሰብኩ።





-5-

## "የመሪ እንጂ የተመሪ ፈሪ የለውም"

አባቴ ወደ አስመራ በአስቸኳይ ተጠርቶ ከመሄዱ በፊቱ እንዲሁ ለአስቸኳይ ሥራ ወደ ትግራይ ሄዶ ነበር። ትግራይ ውስጥ በአዛዥነት ሠርቶ ባያውቅም የመከላከያ የዘመቻ ኃላፊ በነበረበት በ1979-1980 ውስጥ በተለያየ ጊዜ ወደ ትግራይ እየሄደ ሁኔታዎችን ይከታተል ነበር። ከእነዚህ አጭር የሥራ ጉብኝቶች በተለያዩ ጊዜ የተለያዩ መኮንንኖች እንዲሁም በአባቴም ጭምር፣ ብዙ ጊዜ ሲነሳ የምሰማው ግን፣ በየካቲት 1980 መቀሌ የሚገኘው ጦር ውጥረት ላይ ወድቋል ተብሎ በአስቸኳይ ሁኔታው "ከቁጥጥር ውጭ እንዳይወጣ" እርዳታ ለመስጠት ወደዚያ የሄደበትን ጊዜ ነበር። በጊዜው የወያኔ ጦር ከመቀሌ በስተሰሜን በሚገኘው ክልተ አውላሎ አውራጃ በአዲግራትና በመቀሌ መካከል ያለውን ወረዳ አጥቅቶ የውቅሮን ከተማ ለመቆጣጠር እየተጓዘ ነበር። ከውቅሮ በፊት የምትገኘው ሰንቃጣ

የተባለች ቦታ ላይ 128 ብርጌድ እና ከ32ኛ ብርጌድ ተቀንሶ የሄደ አንድ ሻምበል ጦር በጥቅሉ ከሁለት ሺ በላይ የማይሆን ጦር ነበር።

የተፋፋመ ጦርነት ሲጀመር ሰንቃጣ የነበረው ጦር ስለጠላት ኃይል የነበረው መረጃ በቂ እንዳልነበረ ግልጽ ሆነ። ወያኔ ከተገመተው በላይ ኃይል ይዞ ማጥቃቱን ቀጠለ። የ128ኛ ብርጌድ አዛዥ ኮ/ል ደጀኔ ቢቂላ ቀሰለው ምክትል አዛዣቸው ተተክቶ መከላከሉን ቢቀጥልም የወያኔን ጦር መቋቋም አልቻለም። ብዙ ጉዳት ከደረሰበት በኋላ ጦሩ ሰንቃጣን ለቆ ወደ ውቅሮ አፈገፈገ።

ቀጥሎም የወያኔ ጦር በመከታተል የውቅሮን ከተማ ከቦ አዲስ ጥቃት ሰነዘረ። ውቅሮ ላይ ከፍተኛ ውጊያ ተካሂዶ አሁንም የወያኔ ጦር አይሎ የኢትዮጵያ ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰ። ውቅሮ ላይ የነበረው ብርጌድ አዛዥ፤ የኢሠፓ ተጠሪ፤ የብርጌዱ የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊ፤ የአውራጃ አስተዳዳሪ ሁሉ በጦርነቱ መሐል ሕይወታቸው አለፈ።

አባቴ ወደ መቀሌ ለመሄድ አውሮፕላን ውስጥ ሲገባ ስለጦርነቱ መጨረሻ መረጃ አልደረሰውም ነበር። አባቴንና ጀ/መርዕድ ንጉሤን እንዲሁም አባቴ ሥር የሚሠሩ የመከላከያ ዘመቻ መምሪያ መኮንኖችን የያዘችው አውሮፕላን መቀሌ ስትደርስ መቀሌ የነበረው ጦር በድንጋጤ ተውጦ ጠበቃቸው። ከአውሮፕላኑ እንደወረዱ ትግራይ ውስጥ የነበረውን ጦር የሚመሩት የ604ኛ ኮር አዛዥ ጀ/አዲስ አገላቸው ተቀበሏቸው።





"ምን አዲስ ነገር አለ?" አሉ ጀኔራል መርዕድ ጀነራል አዲስን።
"ውቅሮ ተለቀቀ!" አሉ ጀኔራል አዲሱ ጀ/መርዕድንና ጀ/ደምሴን አንድ በአንድ እየተመለከቱ።
"በነሱ እጅ ነው ያለው?" ጀኔራል ደምሴ ጠየቀ።
"አዎ!" ጀኔራል አዲስ መለሱ። ከዚህ በኋላ ጀኔራል መርዕድ በጦሩ ዋና መመሪያ ሆኖ የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማቀነባበር ጀነራል ደምሴ ደግሞ በጦሩ ውስጥ እየተዘዋወረ የሚቀጥሉትን ዘመቻዎች እንዲመራ ተወስኖ ሁሉም ወደ 604ኛ ኮር ዋና መምሪያ አመሩ።

604ኛ ኮር ዋና መምሪያ መቀሌ ከተማ ውስጥ ቢሆንም የኮሩ ኃይል በትግራይ ክፍለ ሀገር ተበታትኖ ነበር። መቀሌ አካባቢ የሚገኘው ከአንበሳው 3ኛ ክፍለ ጦር ተነጥሎ የቀመው የ10ኛው ብርጌድ እና የ12ኛ ክፍለ ጦር ልዩ ልዩ ክፍሎች ብቻ ነበሩ። በጀነራል አርዓያ የሚመራው የ17ኛው ክፍለጦር ሽሬ እና አክሱም አካባቢ ስለነበር መቀሌን ለመከላከል አይችልም። በተረፈ የነበረው በየቦታው የተበታተነው የ16ኛ ክፍለ ጦር ብቻ ነበር።

ወደ ዋና መመሪያ ከገቡ በኋላ ጀኔራል ደምሴ በየመምሪያው መዘዋወር ጀመረ። በተፈጠረው ሁኔታ በጣም ተናዷል። ስለጦሩ ሁኔታ ለሚጠይቀው ጥያቄ የሚያገኘው መልስ ምንም አጥጋቢ ሆኖ አላገኘውም። የሚያገኘው መልስ እንዲያውም ንዴቱን እየጨመረው መጣ። ትግራይ ስላጋጠመው ሲያስረዳ ያደመጠ ሰው በንዴትና በሳቅ መካከል በስሜት ዥዋዥዌ ይጫወታል። በቦታው የነበሩ መኮንኖች የተፈጠረውን ሲያስታውሱም

እንዲሁ አንዳንዱ እየተንከተከቱ ሲስቁ አንዳንዱም በሐዘን ሲዋጡ አንዱም በወኔ ሲንቀጠቀጡ ነበር ጨዋታውን የሚጨርሱት።

በቦታው ከነበሩ መኮንኖች አንዱ ሻለቃ ካሳዬ ማዘንጊያ ነበሩ። ሻለቃ ካሳዬ አሁን በአሜሪካ ነዋሪ ሲሆኑ አባቴ መቀሌ ሲገባ ከተቀበሉት እና በተለያዩ ቦታዎች አብረው ከተዘዋወሩ መኮንኖች ውስጥ አንዱ ነበሩ። ሻለቃ ካሳዬ በጊዜው የሽምበል ማዕረግ የነበራቸውና በፖለቲካ መምሪያ ውስጥ የሚሠሩ መኮንን ነበሩ። "በጦሩ ውስጥ የነበረውን ስሜት ተዘዋውረህ መረጃ ሰብስብና ሪፖርት አቅርብ!" ተብለው በታዘዙት መሠረት ሪፖርት ይዘው ተመልሰዋል። ሻ/ካሳዬ ያቀረቡት ሪፖርት በሁለት ቃላት የሚጠቃለል ነበር- "ጦሩ ፈርቷል!!"

ጀነራል ደምሴ ይህን ሪፖርት ሲሰማ ደሙ ፈላ። በቀጥታ ወደ ዘመቻ መምሪያ ኃላፊው ቢሮ ሄደ። በሩ ክፍት ስለነበር ዘው ብሎ ገባ። ቢሮው ውስጥ የዘመቻ መምሪያው ኃላፊውና ሁለት መኮንኖች ነበሩ። የዘመቻ መምሪያ ኃላፊው ተር ብሎ በመነሳት በተጠንቀቅ ወታደራዊ ሰላምታ ሰጡ። ሻለቃ ካሳዬም ሻምበል አንደለም ከሚባሉ አንድ መኮንን ጋር ስለጦሩ ሁናቴ ተጨማሪ መረጃ ለመጠየቅ ነበር እዚያ ቢሮ የተገኙት። ሻለቃው በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ በሰጡኝ ሰፊ ቃለ-መጠይቅ ገልጸውልኛል። እዚያች ቢሮ ውስጥ ያኔ የተፈጠረውን ትናንት ካዩት የበለጠ ነው የሚያስታውሱት።
"ጀነራል ደምሴ ገና ሲገቡ ወደኛ ዞር ብለው እናንተ ምድንናችሁ?" አሉን።
"ከፖለቲካ መመሪያ ነን ጌታዬ!" ብለን ደርቀን ቆምን።
ወደ ዘመቻ መምሪያው ኃላፊው ኮሎኔል ዞር ብለው "32ኛ ሜካናይዝድ የት ነው ያለው?" ብለው ጠየቁት።





"አገሬ ሰላም ነገው ጌታዬ!" ብሎ ይመልሳል።
"እንዴ የኮር ዘመቻ ኃላፊ እንዲህ ነው ገለጻ የሚያደርገው?"
ዓይኖቻቸው ገንፍሎ ሊወጣ ሲታገል ይታያል።
"በካርታ አሳየኝ! የት ነው 32ኛ ያለው?"
ግድግዳው ላይ ትልቅ ካርታ አለ። ኮሎኔሉ ወደ ካርታው ሄዶ ካርታውን ማየት ጀመረ። ቦታውን ግን ጥቂት ሰከንዶች ቢያልፍም አላሳየም።
"የአንድ ኮር ዘመቻ ኃላፊ ሆነህ እዚህ ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጠህ ጦርህ የት እንዳለ አታውቅም?"
ጥቂት ዝምታ ሆነ።
"በ24 ሰዓት ውስጥ ዕዙን ለቀህ ወደ ምድር ጦር ሂድ!"

ሻለቃ ካሣዬ ይህን ትዕይንት ሲናገር የሐዘን ስሜትም እየተሰማው የሳቅ ፈገግታም እየቃጣው ነበር። "ጀነራል ደምሴ ቢሮውን ለቀው ሲወጡ እላቸውን ተከትሎ ወደገባው ሻምበል ገናናው የሚባል ምክትል የዘመቻ መኮንን ዞር ብለው "አንተ ከዚህ በኋላ ዘመቻውን ምራ!" ብለው ወጡ። ከዚያ በኋላ አዲስ የዘመቻ ኃላፊ እስኪመደብ ዘመቻውን ከጀኔራል ደምሴ ጋር የመጡት መምሪያ መኮንኖች ጋር ይሠራ የነበረው ሻ/ገናናው ነበር። ጀነራል ደምሴ በየመምሪያው እየገቡ ገለጻ ማዳመጥ፣ ብቁ ሆኖ ያላገኙትን ማባረር ሲቀጥሉ መምሪያዎች ቀውጢ ሆኑ" አለ ሻለቃ ካሣዬ አሁን ደግሞ ከት ብሎ እየሳቀ።

ዘለግ ብሎ ቀጠን ያለ ጠይም ቀምጫጫ መኮንን ነው። አሁንም አሳሳቁ አንድ ትዝ ያለው ሌላ የሚያስቅ ሁኔታ እንዳለ ያስረዳል።

“ከሰዓት በኋላ መኪናዬን አስነስቼ ከግቢው ልወጣ ስል አንድ ሻምበል እቃውን አንጠልጥሎ የመተኛ ከረጢቱን ጀርባው ላይ ይዞ እየሮጠ ከመምሪያው ፅህፈት ቤት ሲወጣ አየሁትና መኪናዬን አቁሜ “ምን ሆንክ ምን ነካህ? ብዬ ጠየቅኩት።”

ሰውዬው ጨርቁን ጥሎ ያበደ ነው የሚመስለው።በዚህ አካኺኑ አይቸው ስላማላውቅ ግራ ገባኝ።
‘ኸረ አንድ የተለከፈ ጀነራል መጥቷል። ሳይገድለኝ ከዚህ ቦታ አውጣኝ ። እቃህን ጠቅልለህ ጥፋ። እዚህ መምሪያ ሁለተኛ እንዳላያህ ብሎ አባረረኝ።’ ብሎ እየተርበተበተ መኪናው ውስጥ ዘሎ ገባ። አረጋግቼ ሸኘሁት።

ጀኔራል ደምሴ በየቢሮው ኮሪደር ሲዘዋወሩ ኮሪደር ላይ ሲያዩት ‘ምንድነህ?’ ብለው ሲጠይቁት ያለ ሥራ ሲዘዋወር ነበር ያገኙት። ‘ይኼ ሁሉ መኮንን እዚህ መምሪያ ያለ ሥራ ለምንድነው የሚዘዋወረው እዚያ ጦሩ የሚመራው መኮንን አጥቶ አምሳ አለቃና አስር አለቃ ጦር ሲመራ ሻምበልና ሻለቃ ያለሥራ እዚህ መመሪያ ተቀምጦ ለምንድነው የሚዘዋወረው’ ብለው እንዳባረሩት ሰማሁ።

ጀኔራል ደምሴ ቀጥለው ወደ ድርጅት መመሪያ ሄደው ስለኮሩ ድርጅት አቋም ገለጻ ጠየቁ። የድርጅቱ መመሪያ ኃላፊ ኮ/ል...ነበሩ። እሳቸውም እንዲሁ ለሚጎርፍላቸው ጥያቄ በቂ መለስ ማቅረብ አልቻሉም። እንደ ዘመቻ መምሪያ ኃላፊው በ24 ሰዓት ጦሩን ለቀው ወደ አዲስ አበባ ምድር





ጦር ሪፖርት እንዲያደርጉ ታዘዙ። በምትካቸው ሻ/ አበበ ገ/መድህን ለጊዜው ተመደበ።

አባቱ መቀሌ ዋና መመሪያ ሄደ ስላሳለፉቸው ጥቂት ቀናት ሲናገር "የመምሪያ ኃላፊዎች የጠራቸውን ኃይልና የጦር አቅማቸውን እንኳን በቅነነል መናገር አልቻሉም።” ብሎ ያለው በሻ/ካሣዬ ገለጻ ተብራራልኝ።
"ዋና መምሪያውን በአንድ እግሩ ካስቆሙት በኋላ ጀ/መርዕድንና ጀ/አዲሱን ቀቀው ጀ/ደምሴ ሞሶቦ ወደሚባል ቦታ ሄዱ።
ሻለቃ ካሣዬ ሲናገር ፊቱ ላይ የነበረው የምፀት ፈገግታ ቁም ነገር ካዘለው ድምፅ ጋር ጠፋ።

ሞሰቦ ከመቀሌ ወደ ሰሜን አቅጣጫ የምትገኝ የጦሩ መከላከያ ወረዳ አድርጎ የመሸገባት ቦታ ነበረች። የወያኔ ጦር ውቅሮን ተቆጣጥሮ መቀሌን ለመያዝ ተቃርቧል። መቀሌ የሚገኘው ጦር መቀሌን ለቆ ለመውጣት ምንም አልቀረውም። ሰንቃጣ እና ውቅሮ ላይ በደረሰው ከባድ ሽንፈት ሞራሉ ላሽቆ ወኔው ሸሽቶት በፍርሐት ተውጦ ተፍረክርኳል።

ጀኔራል ደምሴ ሞሰቦ ሲገቡ የጦር አዛዥ የነበሩት የጦር አዛዥ ኮ/በየነ ረዳ ተቀበሏቸው።
“አሁን ጠላት የት ነው ያለው?” አሉ ገና ሰላምታ እንደተለዋወጡ። ኮ/ል በየነ ቅፅል ስማቸው “አባ ሐዊ” ነበር። በአነጋገራቸው እና በኃይለኝነታቸው ምክንያት ያገሩ ሰው “አባ እሳት” ነበር የሚላቸው።
ፊት ለፊታቸው ከነበረው ጋራ ጎን ያለውን የሞተ መሬት እያመለከቱ “እዚያ!” በማለት መለሱ።
ጀነራል ደምሴ ዞር ብለው ተመለከቷቸውና

"አሁን ውጊያ ላይ አይደላችሁም። ግጭት አልፈጠርክም። እዚያ መሆናቸውን እንዴት አወቅክ?"

"አይ ይታዩናል ጌታዬ!" ብለው መለሱ።

"አምጣ እሱን መነፅር" ብለው ወደ ከፍታ መሬት አመሩና በጦር ሜዳ መነፅር ይታዩናል የተባሉትን ወያኔዎች ለማየት ገሠገሡ።

ሻ/ካሣዬና ሌሎች መኮንኖች ሲከተሉ ኮ/በየነ በመረበሽ "ጌታዬ ኧረ ጌታዬ ይተኩሱብዎታል!" አሉ።

"ጀኔራል ደምሴ ዞር አሉና "ፈሪ! እናንተ ፈርታችሁ ሠራዊቱን ታስፈራላችሁ። ይህን መምሪያ ካላጸዳሁ እኔ ደምሴ አይደለሁም" አሉ።

ሁሉም ፀጥ አለ።

በመነፀር ካዩ በኋላ "የቱ ጦር ነው በተወርዋሪነት የተመደበው?" ብለው ጠየቁ።

"10ኛ ብርጌድ ነው።" ኮሎኔሉ መለሱ። 10ኛ ብርጌድ ከክፍሉ ከሶስተኛ ክፍለ ጦር ተነጥሎ መቀሌ ላይ ይገኝ ነበር።

"10ኛ ብርጌድ የታለ?" አሉ ጀ/ደምሴ።

"መቀሌ ነው ጌታዬ!"

"እዚህ ይምጣ አሁኑኑ!"

"መድፋችሁ የታለ?"

"መድፍ እዚህ የለም ጌታዬ"

"የት ነው?"

"ጠቅላይ ጦር ሠፈር ነው" ብለው እንዳየሉስ እየተባለ በሚጠራው የኮሩ ጠቅላይ ሠፈር እንዳለ ገለጹላቸው።





ጀኔራል ደምሴ አዛዡን በንዴት ሲመለከቱ "ጉድ ፈላ!" ብለን እናያለን።

"ጠላት እዚህ ሆኖ መድፉ ውሽሞቻችሁን እንዲጠበቅ ነው ጠቅላይ ሠፈር የሚቀመጠው?"

ሳቃችን ገንፍሎ እንዳይወጣ እየተናነቀን በፈገግታ ብቻ ውጠን አስቀረነው።

መድፍ፤ ቢ.ኤም ሮኬት፤ከያለበት እንዲመጣ አዘዙ።

የ10ኛ ብርጌድ አዛዥ ሻ/ግርማ ተፈሪ የሚባል ነበር ተጠርቶ ቀረበ።

"አንተ ነህ የብርጌዱ አዛዥ?"

"አዎን ነኝ ጌታዬ!"

"በል አሁን የአንድ ብርጌድ ኮማንደር ምን መሥራት እንደሚችል ታሳየኛለህ። ጦርህን ከጓድ ጀምረህ አደራጅተህ ያንን ጋራ አጥቃ!"

ሻምበል ግርማ በሞራል ሰላምታ ሰጥቶ ወደ ግዳጁ አመራ።

"የመድፍ አዛዡ የታለ ጥሩት!"

የመድፈኛ አዛዥ ኮ/...መጡ። ገና ተጠርተው ሲቀርቡ መጥፎ ነገር እንደሚገጥማቸው የገባቸው ይመስላል።

"አንተ ነህ እንዴ የመድፈኛ አዛዥ? ከምሥራቅ አባርሬህ እዚህ ጠበቅከኝ። በል አሁኑኑ ጓዝህን ጠቅልለህ ዕዙን ለቀህ ሂድ!" (እኚህ ኮነሬል ከመፈንቅለ መንግስት ሙከራ በኋላ ጀነራል ሆነው ነበር)።

ወደ እኛ ዞር ብለው "እዚህ የመድፈኛ መኮንን አለ ከናንተ ውስጥ?" አሉ ጀ/ደምሴ።

ሻምበል ወርቁ ባንቲ ቀረበ።

"አንተ መድፈኛ ነህ?"

"አዎን ጌታዬ!"

“በል አሁን ያንተን መድፈኛነት ማየት እፈልጋለሁ። እውነት አንተ መድ ከሆንክ ታሳየኛለህ። በአስቸኳይ መድፍህን አስተካክለህ ትዕዛዝ ጠብቅ።

ሻምበሉ ሰላምታ ሰጥቶ በሞራል እየነጠረ ትዕዛዙን ለመፈጸም በረረ።

የ10ኛ ብርጌድ በጓድ፣ በመቶ፣ በሻምበል ተደራጅቶ ከተባለው ጋራ ደ ትንሽ እንደተጠጋ ተኩስ ተከፈተበት።

“ጥሩ ነው ቦታህን ሳትለቅ እዚያው ይዘህ ጠብቅ በሉ” አሉ ጀኔራል ደምሴ የመድፉን አሰላለፍ ከተቆጣጠሩ በኋላ የተኩስ ትዕዛዝ ሰጡ። ያለ የሌ መድፍ ጥይት ይነጉድ ጀመር። የቢ ኤም ጥይት መድፉን ተከት ይዥጎደጎዳል። ከባሕር ዳር ጀቶች እንዲነሱ ታዞ ስለነበር ያች ጋራ አካባቢዋ በመድፍ በቢ.ኤም በሒሊኮፕተርና በጀት ቦምቦች ድብልቅል፡ ወጣ።

“የመድፍ ድብደባው እንዳያቋርጥ ተጨማሪ ጦር እንዲጠጋ” ጀ/ደምሰ ትዕዛዝ ሰጡ።

የመገናኛ ሠራተኞች የወያኔን ሬድዮ እንዲጠልፉ ታዘው ስለነበር ሬዲዮኖቻቸውን ይዘው ጀ/ደምሴ ትዕዛዝ ከሚሰጡበት ቦታ ተቀምጠው የወያኔን የሬዲዮ መልዕክት እየተከታተሉ ሪፖርት ያቀርባሉ። የመድፉ ድበደባ ያለማቋረጥ ቀጥሏል።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ከወያኔ ረዲዮ የጩኸት መልዕክት ተሰማ።

“እታ ተቃጺልና፣ እታ ተቃጺልና፣ እታ ተቃጺልና...”

“ምንድነው የሚለው?”

“ተቃጠልን ነው የሚለው”

“በለው፣ በለው”





ድብደባው ቀጠለ።

ሌላ ጠለፋ።

“ውጣ! ውጣ! ውጣ!” የወያኔ የበላይ አካል ለቆ እንዲወጣ ያስተላለፈው ትዕዛዝ ነበር።

“የመድፍ ተኩስ አቁም። ጦሩን ውጣና አጥቃ ብለህ ትዕዛዝ አስተላልፍ።”

ይህን ትዕዛዝ ከሰጡ በኋላ የጦር ሜዳ መነጽራቸውን እየተጠቀሙ አሻግረው መመልከት ጀመሩ።

ሻለቃ ካሣዬ በቦታው ሆኖ ያየውን ሲናገር አሁን እንደሆነ ዓይነት በስሜት ተሞልቶ ነበር።

“በፍርሐት ተይዞ የነበረው ጦር ከየምሽጉ እየወጣ ማጥቃት ጀመረ። ሞራሉ ተገንብቶ ካላጠቃሁ ካልተዋጋሁ ማለት ጀመረ።

ጀ/ደምሴ ወደኛ ዞር አሉና

“ይሄ ተራ ሽፍታ ነበር ሠራዊቱን አስጨንቆ የነበረው። ወንበዴው አይደለም። እናንተ ናችሁ ሠራዊቱን ፈሪ ያደረጋችሁት። የመሪ እንጂ የተመሪ ፈሪ የለውም!” አሉ።

ከሞሰቦ አካባቢ ማጥቃቱ ቀጥሎ በተከታታይ ያለሟቋረጥ እያጠቃ የኢትዮጵያ ጦር ውቅሮን ተቆጣጠረ። እንደገና በመቀጠል የወያኔን ጦር ማጥቃት ቀጠለ።

አባቴ ሁልጊዜ የሚቃወመው የጦር ስልት ቢኖር ከተማ መቆጣጠር ላይ የተመሠረተ ስልትን ነበር።

“አንድ ጦር ወንበዴ ባለበት እየተከታተለ መዋጋት እንጂ የተያዙ ከተሞችን እያስለቀቀ ብቻ መቀመጥ የለበትም። ጦሩን በየከተማው በትኖ ገጠሩን

ለወንበዴ አስረክቦ ራሱን የከተማ እስረኛ አድርጎ የተቀመጠ ጦር ክፍ ሐገሩን ተቆጣጥሬአለሁ ማለት አይችልም" ይል ነበር። ይህን አመለካከ ትግራይ በቆየበት ጥቂት ቀናት ውስጥ ሥራ ላይ አውሎት ነበር። ውቅ ድረስ ገፍቶ ሄዶ ከተማዋን የተቆጣጠረው ጦር ባገኘው ድል ተዝናን ከመቀመጥ ይልቅ የሚሸሸውን የወያኔ ጦር እንዲከታተልና በአዲስ አቅ ጦርነቱን እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጠ።

የመቀሌ ከአደጋ መውጣት ሲረጋገጥ ጀ/መርዕድ ጀ/ደምሴን ትተው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።" ካለኝ በኋላ ሻለቃ ካሣዬ ቀጥሎ የተካሄደውን የጦር እንቅስቃሴ አብራርቶ ገለጸልኝ።

"ጀ/ደምሴ ጦርነቱን በአዲስ መልክ ለመቀጠል ተጨማሪ ጦር ከተለያየ ቦታ አሰባሰቡ። 3ኛ ክ/ጦር ከ ኤርትራ ከአድዋ በውቅሮ አድርጎ መቀሌ ገባ። የ17ኛ ክፍለ ጦር በኮ/ አሳምነው በዳኔ መሪነት ተሰለፈ። 32ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ እና 6ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ በአገረ ሰላም ወደ ሐውዜን አመራ።" ሐውዜን ላይ ሃየሎም አርአያ የሚባል የወያኔ ጦር መሪ የሚታዘዝ 5 ብርጌድ ጦር እንደነበር ተደርሶበታል። ይህን ጦር ከተለያየ አቅጣጫ ለመክበብ ነበር የወጣው ዕቅድ።"

"ጀ/ደምሴ ካላቸው ጠባይ" ብሎ ትረካውን ሲቀጥል የማላውቀው የአባቴ ጠባይ እንዳለ ለመስማማት ጓጓሁ። "እዎ አንድ ትዕዛዝ ይሰጡና ከጥቂት ጊዜ በኋላ መፈጸሙን ይከታተላሉ። ካልተፈጸመ ጉድ ይፈላል። አንድ ጦር የተሰጠውን ቦታ እንደያዘ ሪፖርት ማቅረብ አለበት። 'እዚያ ነህ?' ይሉና መጣሁ ብለው በሒሊኮፕተር ሄደው ያጣራሉ። መያዝ ያለባቸውን እዚያው





ቀኘተው ትዕዛዝ ይሰጣሉ። መያዛቸውን ያጣራሉ።" ካለ በኋላ፣ በመሃል ሌላ አንድ ነገር ትዝ ያለው ይመስል ትረካውን ቀየረው።

"ጦርነቱ ሲካሄድ ኤርፖርት ላይ ቁስለኞች በአፋጣኝ እንዲነሱ የሚያስተባብሩ ሁለት ሻምበሎች ተመድበው ነበር። ሻምበል መስፍን አማረ እና ሻምበል አበበ ገ/መድህን ይባላሉ። የአንቶኖቭ አውሮፕላኑ እንደደረሰ ወንበሮቹ ታጥፈው ቁስለኞቹን በአፋጣኝ ለማጓጓዝ ዝግጁ ሆኖ እንዲቆይ አዘው ነበር። ቁስለኞቹ ወደ አየር ማረፊያው ሲጓዙ ጀ/ደምሴ ቀድመው ደረሱ። ከመምጣታቸው በፊት ሻምበል አበበን በስልክ አግኝተው ሁሉ ነገር እንደተዘጋጀ አረጋግጠላቸዋል። ሲደርሱ ሻ/መስፍን ቀርቦ ተቀበላቸው።

"እሺ. ተዘጋጅታችኋል? ምን የቀረ ነገር አለ?"

" እዎ ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል ብቻ ወንበሮቹ ቢታጠፉ ጥሩ ነው..." ሲል። "ና" ብለው አውሮፕላኑ ላይ አወጡት።

"የቱ ወንበር ነው ያልታጠፈው?"

ሲያየው አውሮፕላኑ ተዘጋጅቷል።

"አንተ አንድ መኮንንን ነህ። የሥራዊቱ መሪ ሆነህ እንዴት አንድ ነገር ሳታጣራ ትናገራለህ? እርግጠኛ ሳትሆን እንዴት ሪፖርት ታቀርባለህ?" ብለው ተቆጡት። ሻምበሉ በነጋታው ወደ አየር ማረፊያው አልተመለሰም። "ይሄ ሰውዬ አይለቀኝም" ብሎ በስንት ማባባል ነው ወደሥራው የተመለሰው።" ብማለት ሳቅ አለና ወደዋናው ርእስ ሲመለስ አባቴና ጋሽ መርዕድ አስመራ ሲጫወቱ የሰማሁትን እያስታወሰኝ በጉጉት ማደመጤን ቀጠልኩ።

በጥቂት ቀናት ውስጥ ሐውዜን የነበረው የወያኔ ጦር ከተለያዩ አቅጣጫዎ ሳይዘጋጅ ተከበበ። ከበባው ከመጠናቀቁ በፊት ለመውጣት አልቻለም። ወያ ያልጠበቀው እንቅስቃሴ ነበር። ከ 5 ብርጌድ በላይ የሚሆነው የወያኔ ጦ በዚያን ጊዜ ወያኔ የነበረው ዋናው ኃይሉ ነበር። የወያኔ ጦር አዛዥ ከ ከሚባል ቦታ ወልቃይት ውስጥ ወደሚገኘው ዋናው የህወሓት አመራር ክፍል ጋር በሬዲዮ እየተገናኘ መከበቡን ይገልጽ ጀመር።

"ተከብቤያለሁ"

"አንተ ካልወጣህ ተስፋ የለንም። እንደምንም ብለህ ውጣ!"

ዋናው የወያኔ ጦር መከበቡ ሲታወቅ የሻዕቢያ ጦር በከረን አቅጣጫ የነበረውን የ18ኛ ክ/ጦርን አጠቃ።

የሻዕቢያን እንቅስቃሴ ምክንያት በዚህ መልኩ ሲገልጽ የሰማሁት ከሻለቃ ካሣዬ ብቻ አልነበረም። በተለያየ ጊዜ ሕወሓት ውጥረት ላይ ሲወድቅ ሻዕቢያ በበኩሉ ኤርትራ የሚገኘውን ጦር ውጥረት ላይ በመጣል የተቻለውን እርዳታ ለመስጠት እንደሚሞክርና ሻእቢያም በወያኔም ጦር በዚሁ ሁኔታ እንደሚረዳ ብዙ ጊዜ ይነገራል። ምክንያቱ ይህ ይሁንም አይሁን ሻዕቢያ በከፈተው ጦርነት ምክንያት ወደ ትግራይ የተዛወረው ጦር ሁሉ የከበባው መጨረሻ ድረስ ትግራይ ውስጥ ለመቆየት አልቻለም።

ከበባው በተጠናቀቀ በኋላ ጀ/ደምሴ የክፍሉን አዛዦች፣ ም/አዛዦች የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊዎች፣ የዘመቻና የወታደራዊ ደህንነት መምሪያ ኃላፊዎች በጠቅላላው ሰብስበው ስለጠሩ ጠቅላላ ሁኔታ ገለጻ አደረጉ።

ሻለቃ ካሣዬ ትረካውን ቀጠለ። "እኔ የስበሰባው ቃለ ጉባዔ ያዥ ሆኜ ከሻምበል ገናናው ቸኮል ጋር ስለተመደብኩ የሚናገሩትን ሁሉ ቃል በቃል





እመዘግበው ነበር።" አለኝ በጣቱ አመዘገባቡን እያመለከተ። "ከ5 ብርጌድ በላይ የትግራይ ወንበዴ ሐውዜን ውስጥ ተከቧል። እና ይሄን ጠላት እዚሁ መምታት ከተቻለ የትግራይ ጦርነት አለቀ።" አሉ ጀኔራል ደምሴ ተሰብሳቢውን በትኩረት እየተመለከቱ። የወንበዴው ኃይል ተከቦ መውጫ አጥቶ እየተንፈራገጠ ነው። ተከበናል መውጫ አጥተናል እያሉ ተስፋ የቆረጠ መልዕክት እያስተላለፉ ነው።" ካሉ በኋላ ትንሽ ሰኮንዶች በፀጥታ ከቆዩ በኋላ "አንድ የታፈነ ኃይል መውጫ ይፈልጋል። እንደ ጭስ ቀዳዳ ፈልጎ ለመውጣት ይሞክራል። ልል የሆነ ቦታ እስኪያገኝ ሁሉንም አቅጣጫ ይፈትሻል። ልል ቦት አግኝቶ እንዳይወጣ ሠራዊቱ ጠንክሮ መዋጋት አለበት። ይህን ካደረገ የትግራይ ሁኔታ እዚሁ አለቀ ማለት ነው። ከወጣ ግን ችግሩ ይቀጥላል። ይህ እንዳይሆን እያንዳንዳችሁ ጠንካራችሁ መሥራት አለባችሁ።

በመሃል ስልክ ይደወላል።

አንድ መቶ አለቃ ይገባና

"ጌታዬ የመከላከያ ሚኒስትሩ ይፈልጉዎታል!"

ጄኔራል ደምሴ አንዴ መጣሁ ይሉና ይወጣሉ።

ተመልሰው ሲመጡ ፊታቸው ላይ ንዴት ይታይ ነበር።

ማብራሪያውን እንደቀጠሉ ወዲያው መቶ አለቃ ይገባል።

"ጌታዬ ፕሬዚዳንቱ ይፈልጉዎታል?"

እንደገና መጣሁ ብለው ይወጣሉ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ተመልሰው መጡና "ከረን አደጋ ላይ ስለወደቀ ወደ ኤርትራ መሄድ አለብኝ። ይህ ቀለበት ላይ የገባውን የጠላት ጦር ከእጃችሁ እንዳያመልጥ በርቱ!" ብለው ተሰናበቱን።

ጀ/ደምሴ ወደ ኤርትራ በሄዱ በሶስተኛው ቀን ሐውዜን ተከቦ የነበረወ የወያኔ ጦር የ22ኛ ብርጌድ በነበረበት መስመር ወደ ተንቤን አቅጣጫ የሞት ሽረት ተጋድሎ አድርጎ ከበባውን በጥሶ ወጣ። በወርአ. ወንዝ በኩል አድርጎ ወደ ተከዜ ገባ።

ከጥቂት ወራት በኋላ የሶስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት የሚባል ትግራይ ውስጥ ሲቋቋም የጦሩ አዛዥ ጀነራል ሙላቱ ነጋሽ የትግራይ ክ/ሀገር እና የጦሩ የበላይ አስተዳዳሪ ደግሞ የአምሳ አለቃ ለገሠ ሆኖ ተሾመ። ሃምሳ አለቃ ለገሠ ከተማ በመቆጣጠር ላይ የተመሠረተ ታክቲክ ተከትሎ የተለያዩ የትግራይ ከተሞችን “ማፅዳት” ዘመቻ ጀመረ።

ጀ/ሙላቱ ይህን ታክቲክ እንደተቃወሙ ግልጽ ነበር። ለመከላከያ ሚኒስትሩ በጻፉት ሪፖርት ከዚያ በፊት በጀ/ደምሴ የቀረበውን ወንበዴውን እንጂ መሬትን ግብ ያለማድረግ እቅድ ጠቅሰው ዘመቻው በዚያ መልክ መካሄድ እንዳለበት ገልጸዋል። የጀነራሉ ፕላን በአምሳ አለቃው ተሽሮ ጦሩ በትግራይ ከተሞች ተበተነ። ከተማ የመቆጣጠር ታክቲክ ተከተሉ። ጦሩ በየትናንሹ ከተማ ከተበተነ በኋላ አንዱ ላንዱ እርዳታ መስጠት በማይችልበት ሁኔታ ሲገኝ ለወያኔ ጦር አመቺ ሆነለት። በተጨማሪ ከተሞችን በቦንብ ጣይ አውሮፕላን እየደበደቡ ሕዝቡን የበለጠ አስቆጡት። ሐውዜን ከተማ ላይ አውሮፕላን ድብደባ የተደረገው ያን ጊዜ ነበር።





# -6-

አዲስ አበባ ከደረስኩበት ደቂቃ ጀምሮ አስመራ የምመለስበትን ምክንያትና ቀን ማሰብ አላቋረጥኩም:: አስመራ ከሄድኩኝ ወራቶች አልፈዋል። የተቀየረ ነገር ቢኖር አባቴ ኤርትራ የሚገኘው የሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ ሆኖ አስመራ ሲቀር፣ አብረውት ሄደው የነበሩት ጀ/መርዕድ፣ ጀ/ኃይሉ፣ ጀ/አምሃ፣ እና ሊሎች የጦር መኮንኖች ወደ አዲስ አበባ መመለሳቸው ነው። ሜ/ጀ ቁምላቸው ደጀኔ (የዘመቻ)፣ ሜ/ጀ ሁሴን አህመድ (የድርጅት)፣ እና ሜ/ጀ ወርቁ ቸርነት (የፖለቲካ) ምክትል አዛዦች ሆነው ተሹመው ነበር። አባቴ የሹመቱ ደብዳቤ ሲደርሰው ሌ/ኮ/መንግሥቱ ጋር ለመነጋገር ቀጠሮ ይዞ ከቀረበ በኋላ በጦሩ ውስጥ ያለው መከፋፈል መቆም እንዳለበት እና አንድ ዓይነት ውጤት ለማምጣት አስፈላጊ ከሆኑት ውስጥ አንዱ በጦሩ ያለው የዕዝ ጠገግ መሻሻል መሆኑን አስረድቶ በኤርትራ እንዲሰራ ከተደረገ የአንድ ሰው ትዕዛዝ ደንብ መከበር እንዳለበት አለበለዚያ ግን የሱ እዚያ መመደብ ለውጥ እንደማያመጣ ገለፀላቸው። ሌ/ኮ/መንግሥቱም የዚህ ዓይነቱ አሰራር በሥልጣናቸው ላይ የሚያመጣውን አደጋ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ የዚህ ዓይነቱ አሠራር ደግሞ በሰሜን ከተጀመረ ወደ ሌሎች ክፍሎችም መዛመቱ ስለማይቀር ከብዙ ማቅማማትና ሙቅሙቅ በኋላ በጊዜው ሁኔታ ተገደው ተስማሙ። በዚህ ሕግ መሠረት